# አዲስ ዘመን

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 065 ኅዳር 5 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# የናይሮቢው ውይይት በሰላም ስምምነቱ አተገባበር ላይ የጋራ መግባባት የተደረሰበት እንደሆነ ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ገለጹ

## - በውይይቱ ላይ የተሳተፈው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በአዲስ አበባ አቀባበል ተደርጎለታል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ አፍሪካ የተደረገውን የሰላም ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ የተካሄደው የናይሮቢው ውይይት በሰላም ስምምነቱ አተገባበር ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዲደረስ ያስቻለ መሆኑን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ኤታማዥር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ አስታወቁ፡፡ በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ሲካሄድ በነበረው ውይይት ላይ የተሳተፈው የልዑካን ቡድን ትናንት ወደሃገሩ ተመልሷል፡፡

በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት እና በሕወሓት ታጣቂዎች አዛዦች መካከል በናይሮቢ ሲካሄድ የነበረው ውይይት ከትናንት በስቲያ የተጠናቀቀ ሲሆን በውይይቱ የተሳተፈው የኢትዮጵያ ተወካዮች ቡድንንም ትናንት ከሰዓት በኋላ አዲስ አበባ ሲገባ በቦሌ ዓለምአቀፍ አየር ማረፊያ ደማቅ አቀባበል ተደርጎለታል፡፡

የኢፌዲሪ መከላከያ ሠራዊት ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣ በኬንያ ናይሮቢ የተደረገውን ውይይት አስመልክቶ በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በሰጡት መግለጫም በደቡብ አፍሪካ የተጀመረውን የሰላም ንግግር ማሳረጊያ የሚሆን የተግባራዊነት ዕቅድ ላይ ጥልቅ ውይይት ማድረጋቸውን

የናይሮቢው ውይይት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ



# ‹‹የሰላም ስምምነቱ የኢትዮጵያን ቁርጠኝነትና የአፍሪካን የመፍትሔ ምንጭነት ችሎታ ያመላከተ ነው››

አቶ አባተ ኪሾ

- የቀድሞ የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተካሄደው የሰላም ስምምነት የኢትዮጵያን ቁርጠኝነትና የአፍሪካን መፍትሔ አምጭነት ችሎታ ያመላከተ ነው ሲሉ የቀድሞው የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አባተ ኪሾ አስታወቁ። በሕዝብ ልብ ውስጥ የጦርነቱ መቆም የፈጠረው የእፎይታ ስሜት በፖለቲከኞቹና በአክቲቪስቶቹ አካባቢም ቢፈጠር ሰላሙን በአግባቡ ማጣጣም ይቻላል ብለዋል።

‹‹የሰላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











# የቱሉ ዲምቱ-ቃሊቲ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት እስከ ሰኔ 30 ይጠናቀቃል

## - ለግንባታው ማጠናቀቂያ መንግሥት 2 ቢሊዮን ብር መድቧል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በነዋሪዎች ዕለታዊ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጫና ሲያሳድር የቆየውና የግንባታ ሂደቱ የተጓተተው የቱሉ ዲምቱ-ቃሊቲ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በተያዘው በጀት ዓመት ተጠናቆ ለትራፊክ ክፍት እንደሚሆን የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን አስታወቀ። ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ መንግሥት ሁለት ቢሊዮን ብር መድቦ ሥራው እየተከናወነ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ እያሱ ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ የቱሉ ዲምቱ-ቃሊቲ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 11 ኪሎ ሜትር ርዝመትና 50 ሜትር የጐን ስፋት ያለው ሲሆን ግንባታው በ2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር

የቱሉ ዲምቱ-ቃሊቲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ዜና



ዶክተር አብዮት ባዩ

## ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ በኢትዮጵያ ሊካሄድ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ በያዝነው ወር መጨረሻ ላይ በኢትዮጵያ እንደሚካሄድ የኢኖቬሽንና የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም አስታወቀ።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም ኃላፊ ዶክተር አብዮት ባዩ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ጉባኤው በኢትዮጵያ መካሄዱ የአፍሪካውያን የኢንተርኔት አጠቃቀምና የተደራሽነት ችግር እንዲሁም የባህል ወረራ ላይ በመወያየት መፍትሔ ለማበጀት ዕድል የሚፈጥር ነው።

እንደ ዶክተር አብዮት ገለፃ፣ ኢንተርኔት በዓለም ላይ የብዙ ኔትዎርኮች ጥርቅም በመሆኑ በባለቤትነት የሚያስተዳድረው አካል የለም። ስለዚህ በጉባኤው የአፍሪካውያን የኢንተርኔት አጠቃቀምና የተደራሽነት ችግር እንዲሁም የባህል ወረራን ለመከላከል የሚያስችል ውይይት ይደረጋል።

በዚህም በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ለውጥ እያመጣና በሰዎች ላይ የሚያመጣውም ተጽዕኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ችግሩን ለመቅረፍ ጉባኤው ሲካሄድ በኢትዮጵያ ለአስራ ሰባተኛ ጊዜ ነው ብለዋል።

የኢንተርኔት አስተዳደር ጉዳይ አጠያያቂ እየሆነና የአደረጃጀት ክፍተት እየታየበት በመምጣቱ ተጽዕኖው እንዳይባባስና ጠቀሜታው እንዲጨምር የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ አሳልፎ በየሀገራቱ እየተካሄደ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ዶክተር አብዮት ገለፃ፤ በጉባኤው ኢንተርኔት በአፍሪካ ሀገራት የሚገኙ ዜጎች ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል አቅጣጫ ይቀመጣል። ይህም ዜጎች ሕይወታቸውን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲኖሩ ከማድረግ ባለፈ ጉዳቱ ያለበት ደረጃ እንዲታወቅ ያስችላል።

የኢንተርኔት አስተዳደር ጉባኤ በኢትዮጵያ መካሄዱ አፍሪካውያን ለጉዳዩ ትኩረት እንዲኖራቸው ያደርጋል ያሉት ዶክተር አብዮት፤ በውይይቱ የሚነሱ አምስት ጉዳዮች አሉ። እነሱም ከአፍሪካ ችግሮችና ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር የሚያያዙ ናቸው ብለዋል።

አምስት የቴማቲክ ጉዳዮች ከሚባሉት ውስጥ አንደኛው ኢንተርኔት ለሁሉም ተደራሽ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። በዚህም ለኢንተርኔት አገልግሎት የሚረዱ ግብዓቶችን በየአካባቢው ተደራሽ ማድረግ ቀዳሚ ትኩረት ይደረጋል።

ሁለተኛው ደግሞ የኢንተርኔት መቆራረጥ ጋር የሚያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረግ ሲሆን በዚህም ክፍት የዓለማችን ኔትዎርክ ሆኖ ለእያንዳንዱ ሰው ተደራሽ የሚሆነው ኢንተርኔት ጉዳት እንዳያመጣ የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር ይሞከራል።

የባህል ወረራ እንዳይኖርና የሕፃናት ደህንነት ለመጠበቅ ደግሞ የሴፍቲና የሴኪዩሪቲ ሥርዓት መዘርጋት ሶስተኛው ቴማቲክ ጉዳይ ነው። አራተኛው ጉዳይ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን የሚመለከትና ኢንተርኔትን እንደላብራቶሪ ለመጠቀም የሚያስችል ሁኔታን መፍጠር ነው። በዚህም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በኢንተርኔት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ በጉባኤው ይዳሰሳል ብለዋል።

አምስተኛው ደግሞ ዳታ እንዴት እየተመራ እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችል ሲሆን መንግሥት ዳታ ተጠቃሚ፣ አመንጪና ተቆጣጣሪ እንደመሆኑ መጠን እንዴት መምራት እንዳለበት በጉባኤው ይነሳል። ይህ የሆነበት ደግሞ የእያንዳንዱ መንግሥታት እንቅስቃሴ በዓለም ላይ ያለውን የዳታ እንቅስቃሴ እንዲያስተካክል ይደረጋል ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ ጉባኤው እንደ ሀገር ያለውን ችግር ለማስረዳትና መፍትሔውን ለማግኘት እድል እንደሚፈጥር ተናግረው፤ በጉባኤው ከ2 ሺህ 500 በላይ እንግዶች ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል ሲሉም ተናግረዋል።

# ወጣቶች ወርቃማ የዕድሜ ዘመናቸውን የተሻለች ሀገርና አህጉር ለመፍጠር ማዋል እንደሚገባቸው ተገለጸ

## - የኢትዮጵያ ወጣቶች ወር በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ መከበር ጀምሯል

እያሱ መስሰ



አዲስ አበባ፡- ወጣቶች ከሱስና ከአልባሌ ተግባራት በመራቅ ወርቃማ የዕድሜ ዘመናቸውን የተሻለች ሀገርና አህጉር ለመፍጠር ማዋል እንደሚገባቸው ተገለጸ። በተለያዩ ከተሞች እና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ለአንድ ወር እየተከበረ የሚቆየው 16ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች ቀን በሴቶችና ማኅበራዊና ጉዳይ አዘጋጅነት "ንቁ የወጣቶች ተሳትፎ እና ተካታችነት" በሚል መሪ ሃሳብ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ መከበር ጀምሯል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ( ዶ/ር ) በመርሐ ግብሩ መክፈቻ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት በዓሉ በዋናነት የሀገራችን ወጣቶች እርስ በእርስ ተቀራርበው በሀገራቸው ብሎም በአህጉራቸው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም በልማትና በሰላም ጉዳዮች ዙሪያ በባለቤትነት የሚወያዩበት እንዲሁም የተሻለች ሀገርና አህጉር ለመፍጠርና ለማጽናት ቃልኪዳናቸውን የሚያድሱበት ነው። በዚህ መነሻነት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የግንዛቤና ንቅናቄ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

ትምህርት ለአንድ አገር ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና ቁልፍ መሣሪያ መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትሯ መድረኩ ከዩኒቨርሲቲ የጀመረው በዚህ እሳቤ ነው ብለዋል። ትምህርት የአንድ ማኅበረሰብ እውቀት፣ጥበብ፣ ደንብና ወግ እንዲሁም ልምድና ባህላዊ እሴት ከሀገር የልማት ፍላጎትና ዓላማ ጋር በተጣጣመ መልኩ የሚሰርጽበትና ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍበት ሂደት እንደሆነ ተናግረዋል።

የወጣቶች ስብዕና እንዲገነባ ከማስቻል ረገድ ከቤተሰብ፣ ከሃይማኖት እና ከሚዲያ ተቋማት በተጨማሪ የትምህርት ተቋማት ሚና የላቀ እንደሆነ ገልጸዋል።

ወጣቶች ሁሉን ነገር ለማወቅ ካላቸው ጉጉት የተነሳ በዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ስር እየወደቁ በሀገራችን ተቀባይነት ካለው ባህሪ እያፈነገጡ ላልተፈለጉና ተቀባይነት ለሌላቸው መጤና ጐጂ ድርጊቶች እየተጋለጡ መሆኑን በመጠቆም ወጣትነት ወርቃማ የዕድሜ ዘመን በመሆኑ በትምህርት ቤት አካባቢ ወጣቶች ለሱስና ለአልባሌ ስብዕና የሚዳርጉ ተግባራትን እንዳያከናውኑ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። ለሀገር ልማት ተብለው የሚወጡ ፖሊሲዎች ለወጣቱ ስብዕናና ልማት ጉልህ አስተዋጽዖ ያላቸውና እርስ በርሳቸው የማይጣረሱ እንዲሆኑ፣ለውጤታማነቱም ሁሉም እንዲረባረብ ጥሪ አስተላልፈዋል።

በመርሐ ግብሩ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው እንደገለጹት ኢትዮጵያ የአገራችንን መጻኢ ዕድል በመወሰን ላይ ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚችሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ እድገትና ብልጽግናዋን ማረጋገጥ የሚችሉ እምቅ አቅም ያላቸው የበርካታ አፍላ ወጣቶች ምድር ነች። ይህን ግዙፍ የማኅበረሰብ ክፍል በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ የአገራችንን ቀጣይነት ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ተብትቦ ከያዛት የድህነት ማቅ በአጭር ጊዜ ማላቀቅ ይቻላል።

ይህንን ግዙፍ አቅም በአግባቡ መጠቀም ባለመቻሉ ልማትና እድገታችን በሚፈለገው ልክ ወደ ፊት ሳይራመድ መቅረቱ ብቻ ሳይሆን ሰላማችንንም ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ሆኗል ብለዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን መንግሥት ለወጣቱ ከፍተኛ ትኩረት እየሰጠ በመምጣቱ ወጣቶች በሀገራችን ፖለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ስነልቦናዊ መስኮች ሁለንተናዊ ተሳታፊ የሚሆኑበት ዕድል ተከፍቷል። በቂ ነው ባይባልም ማኅበረሰቡ በዚህን እምቅ ኃይል አቅም እየተረዳ ተጠቃሚ እያደረገው ይገኛል። በተለይም ባለፉት አራት ዓመታት ሴቶችና ወጣቶችን ማዕከል ያደረጉ መልከ ብዙና ግዙፍ ፕሮጀክቶች እየተቀረጹ ወደ ሥራ ተገብቷል ብለዋል።

የትምህርት ሚኒስቴርም አገር ተረካቢ ለሆነው ወጣት ትኩረት በመስጠት በአግባቡ የሰለጠነ ፣ ከዘመኑ የዓለም ውጣቶች ጋር ተወዳዳሪ እውቀት ያለው ፣በስብዕናና ሥነ ምግባሩ የተመሰገነ፣ ምክንያታዊ ስብዕና ያለው ወጣት ለማፍራት እየሠራ ይገኛል ሲሉም ተናግረዋል።

ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ "የመጪው ጊዜ የአፍሪካ መሪዎች" በሚል መሪ ሃሳብ የወደፊቷ አፍሪካ ተረካቢና ባለአደራ ወጣቶች የመጀመሪያውን ሀገራዊ ጉባኤ በአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ አካሂደዋል ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ወጣቶች ይህን ወራችሁን ስታከብሩ ለሀገራችሁና ለአህጉራችሁ፣ ከፍ ሲልም ለዓለምና ለሰው ልጅ አስተዋጽዖ የምታገኙበትን ፣ ልምድ የምትለዋወጡበት፣ ቃልኪዳናችሁን የምታድሱበትና ኢትዮጵያዊ ወንድማማችነት እና እህትማማችነትን የምታጸኑበት ወር መሆን አለበት ብለዋል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና ማኅበራዊ ልማት ባህልና ስፖርት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወርቅሰሙ ማሞ ፣ የጋሞ ዞን አስተዳዳሪ አቶ ብርሃኑ ዘውዴ፣ የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳምጠው ዳርዛ ፣ የጋሞ አባቶችና የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የታደሙ ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ተወካይ ሚስስ ሱዛን መንዶክም ተገኝተዋል።

# በጦርነቱ ወቅት የፈረሰው የጥራሪ ወንዝ ድልድይ ጥገና እየተደረገለት ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር



ሰቆጣ ፡- በጦርነቱ ወቅት በደረሰበት ጉዳት ፈርሶ የነበረው የሰቆጣ-ኮረም መንገድ መሐል የሚገኘው የጥራሪ ወንዝ ድልድይ የመልሶ ግንባታ ሥራ መጀመሩን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ።

ድልድዩን በተገጣጣሚ ብረት ለመገንባት ከጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የዘርፉ ባለሙያዎችና ግብዓት የማንቀሳቀስ ቀጥሎም ቦታውን የማስተካከል ሥራ ሲከናወን መቆየቱን በአስተዳደሩ የድልድይና ስትራክቸር ሥራዎች ዳይሬክተር ኢንጂነር ጌትነት ዘለቀ ለኢዜአ ተናግረዋል። የብረት ድልድዩን የመገጣጠም ሥራ ደግሞ ከዛሬ ጀምሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል። የሚሠራው ተገጣጣሚ ደልድይ 42 ሜትር ርዝመትና 4 ነጥብ 2 ሜትር ስፋት እንደሚኖረው አስረድተዋል።

ድልድዩ የሰቆጣ ከተማን ከዛታ እና ኮረም ከተሞች እንደሚያገናኝ ያመለከቱት ኢንጂነር ጌትነት መገንባቱም በአካባቢው የንግድና ሌሎች ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎችን ለማቀላጠፍ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

የመከላከያ ሠራዊት ለሥራው ሎደርና ዶዘር ከነባለሙያዎቹ በመመደብ ድጋፍ መስጠቱን ጠቅሰው፤ ተገጣጣሚ ድልድዩን በ10 ቀናት ወስጥ ለማጠናቀቅ ታቅዶ ርብርብ እየተደረገ መሆኑንም ገልጸዋል።

ቀደሞ የነበረው ድልድይ በጦርነቱ ምክንያት ከፈረሰ በኋላ ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎቱ ተቋርጦ እንደቆየም ጠቁመዋል።

የዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር መንገድ መምሪያ ኃላፊ አቶ ሰለሞን እሸቱ በበኩላቸው፤ የድልድዩ በፍጥነት መገንባት የአካባቢውን ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሥራ ከማቀላጠፍ ባለፈ ሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያሻቸው ወገኖች ተደራሽ እንዲሆን የጎላ ሚና እንደሚኖረው ተናግረዋል።

የመልሶ ግንባታው ሥራ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ መምሪያው አስፈላጊውን እገዛና ትብብር እንደሚያደርግ አረጋግጠዋል ።

የድልድዩ ሥራ መሠረተ ልማቶችን መልሶ ለመገንባት በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት አንዱ ማሳያ መሆኑ ተመልክቷል ።

# የሰላም ስምምነቱ የኢትዮጵያን የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን የማሳደግ አዎንታዊ ሚና አለው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ጎንደር ፡- በመንግሥትና ሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት የኢትዮጵያን የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን በማሳደግ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ።

ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተሳተፉበት ሀገር አቀፍ የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ አካላት የጋራ የምክክር መድረክ በጎንደር ከተማ ተካሂዷል።

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ተመስገን ጥላሁን በመድረኩ እንደተናገሩት የሰላም ስምምነቱ በኢንቨስትመንት ዘርፍ የውጪ ባለሀብቶችን በብዛት ለመሳብ ምቹ አጋጣሚ ይፈጥራል።

የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ከምንም በላይ ሰላም የሚሻ ዘርፍ መሆኑን የጠቀሱት ምክትል ከሚሽነሩ፤ የውጪ ባለሀብቶች በአንድ ሀገር ኢንቨስት ለማድረግ የመጀመሪያ ጥያቄያቸው ሰላምና መረጋጋት መሆኑን ገልፀዋል።

የሰላም ስምምነቱ ተስፋ ሰጪ ከመሆኑም በላይ በኮቪድና በጦርነቱ የተቀዛቀዘውን የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በቀጣይ ለማካካስ የሚያስችል አመቺ ዕድል እንደሚፈጥር ተናግረዋል።



የኢትዮጵያ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ባለፈው ዓመት 3 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር እንደነበር የጠቆሙት አቶ ተመስገን፤ ይህንንም ዘንድሮ ወደ 6 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

እቅዱ ተግቶ መሥራትን የሚጠይቅና የሰላም ስምምነቱንም እንደ አንድ ምቹ አጋጣሚ በመውሰድ በትኩረት ለመፈጸም የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ለውጪ ባለሀብቶች ምቹ የሆኑ በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዳሉ ያወሱት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ በተለይም ግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ማዕድን፣ ቱሪዝምና የአይሲቲ ዘርፍ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑም ጠቁመዋል።

በችግሮች ውስጥም ቢሆን የክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰት አልተቋረጠም ያሉት ደግሞ ከውይይቱ ተሳታፊዎች መካከል የአማራ ክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ እድሪስ አብዲ ናቸው።

በክልሉ በዘንድሮ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 131 ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 1 ሺህ 180 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መሰጠቱን ተናግረዋል።

በመንግሥትና ሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነትም ለክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰት የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አክለዋል።

የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ጉደታ አበበ የሰላም ስምምነቱ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ያለ ስጋት እንዲሠማሩ ዕድል የሚፈጥር ነው ብለዋል።

በክልሉ በበጀት ዓመቱ 400 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያላቸውን ባለሀብቶች ለማስተናገድ አቅድ መያዙን ጠቁመው፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 42 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ከ1 ሺህ 700 በላይ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ማስተናገድ ተችሏል ብለዋል።

ትናንት ለአንድ ቀን በተሰናዳው መድረኩ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ ሁሉም ክልሎች የተሳተፉ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በክልሎች የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳለጥ በሚያስችሉ የጋራ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ አቅጣጫ ተቀምጧል።

# የሲዳማ የሽምግልና ሥርዓት ሕዝቡ በመተማመን እንዲኖር ማስቻሉን የአገር ሽማግሌዎች ተናገሩ

**ዘሳለም ግዛው**

ሐዋሳ፡- የሲዳማ ክልል አቦ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ብይን ከመስጠት ባለፈ የእርቅ ሥርዓት የሚከናወንበት ማኅበረሰቡ በይቅርታና በመተማመን አብሮ እንዲኖር በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱን የአካባቢው ሽማግሌዎች ተናገሩ። ሥርዓቱ ሕጋዊ እውቅና አግኝቶ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጎን ለጎን አገልግሎት እንደሚሰጥም ተመልክቷል።

በወንሾ ወረዳ አካባቢ ሽማግሌ አቶ አለሙ ዮኔ፤ ከትውልድ ትውልድ በመሸጋገር እየተከናወነ የሚገኘው አቦ ወንሾ ባህላዊ ዳኝነት ለሲዳሞዎች ትልቅ እሴት እንደሆነ ነው የገለጹት።

ሥርዓቱ ለአገር የሚጠቅም፣ ወቅታዊ ችግሮችን መፍታት እንደሚያስችል በመጠቆምም፤ ሲዳሞዎች በባህላቸው አስከሬን አስቀምጠው ይቅር የሚባባሉበት ‹‹አፍን›› ሥርዓት መረጋጋትን በመፍጠር፣ ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ለግጭት የሚያነሳሱ ጉዳዮች እንዲረግቡ ጉልህ ሚና እንደነበረው አመልክተዋል።

አፍን ቂም በቀልን በመተው እርቅ የሚፈጸምበት ሥርዓት እንደሆነ የጠቆሙት የአገር ሽማግሌው፤ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ቢስፋፋ ኖሮ እርስ በእርስ ግጭት አይኖርም፣ ጦርነት ውስጥም አይገባም፣ የታለፈው አይነት ችግርም አይደርስም ነበር ብለዋል።

አሁን አሁን የሕይወትና የንብረት ውድመት የተባባሰው የእርቅ ሥርዓት ባለመስፋፋቱ ነው። እሴቱን መጠበቅም ማስፋፋትም ይገባል ብለዋል። በሁሉም አካባቢ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሥርዓቱን ቀስመው



ሊያስፋፉት እንደሚገባም መክረዋል።

ሁለት ሰዎች በምስጢር የፈጸሙትን በፍርድ ቤት፣ በፖሊስና በዐቃቤ ሕግ ፊት ቢክዱ አራት ሆነው በሚሰየሙት ሽማግሌዎች ፊት ሊክዱ አይችልም። እውነት የሚናገሩበት፣ በትክክልና በሐሊናዊ ሚዛን ዳኝነት በመስጠት እውነት እንዲወጣ የሚደረግበት ሥርዓት መሆኑንም ጠቁመዋል።

ቅዳሜ ከሰዓትና እሁድ የሚከናወነው ሥርዓቱ፤ በአንድ ወር ውስጥ የቀረበው አቤቱታ እልባት የሚሰጥበት፣ ሽማግሌዎቹ በነጻ የሚያገለግሉበትና የአገር ሽማግሌዎችና የጎሳ መሪዎች ቦታው ድረስ በመገኘት ችግሩ እንዲፈታ የሚያደርጉበት እንደሆነም አመልክተዋል።

ሽማግሌዎቹ ጉዳዩን ተመልክተው እውነታውን የሚያወጡበት አሠራርን ያከናውናሉ። የግጭቱን መንስኤ አጥንተው ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋሉ። በሽማግሌዎች ፊት ክህደት የፈጸመ ይቀሰፋል ተብሎ ስለሚታመን ውሸትም መካካድም አይቻልም።

ተበዳይ ቅሬታ ካቀረበ ቅሬታ የቀረበበትን ሰው አስጠርተው መፍትሔ የሚሰጥበት፣ ተጠሪም ሽማግሌዎችን በማክበር እንደሚቀርብ፣ የሐሰተኛ ምስክርም እንደማይኖር አመልክተዋል።

ዳኞቹ የሚመረጡት በሰው ሳይሆን እውነት ይናገራሉ፣ ትክክለኛ ፍትሕ ለሕዝብ ይሰጣሉ ተብለው በሚታመኑት በአካኮ ነው። እነርሱም የሚያግዟቸውን ሽማግሌዎች ይመለምላሉ፣ የሴቶችን ተሳትፎ ማዕከል በማድረግ ይመርጣሉ።

በ16ኛውና በ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲተገበር የነበረ ጉዳዩን የሚመለከቱት ሽማግሌዎች ስህተትና አድልኦዊ ዳኝነት እንዳይፈጽሙ አካኮ ስላስጠነቀቃቸው ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ለራሳቸው ሲሉ እንደሚወስኑም ነው ያመለከቱት።

የሲዳማ ክልል ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አበበ ማሪም፤ በክልሉ ሁሉም ወረዳዎች እንዲህ አይነት ዳኝነት እንደሚተገበር ተናግረዋል።

ሥርዓቱ በፍትህ ሚኒስቴርና ፍትህ ቢሮ እውቅና አግኝቶ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጎን ለጎን አገልግሎት የሚሰጥበት መሆኑንም አመልክተዋል።

በጉዳዩ ላይ ብይን ከመስጠት ባለፈ የእርቅ ሥርዓት የሚከናወንበት በመሆኑ የአካባቢውን ማኅበረሰብ እንዲተማመን በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለው፣ ሽማግሌዎቹ በአገር በቀል እውቀት የሚያገለግሉበትና ምንም ክፍያ የማይጠይቁበት ሥርዓት እንደሆነም ተናግረዋል።

ችግሩን የሚፈቱት የሲዳማ ጭሜሳዎች (ብቁ አረጋውያን) ማኅበረሰቡና ፈጣሪ ሕዝቡን እንዲመሩ አደራና ስልጣን የሰጣቸው ተብሎ ስለሚታመኑና በሐሊናዊ ፍርድ ውሳኔ የሚሰጡም ናቸው ተብሎ ስለሚታመኑ የእነዚህ ሰዎች ውሳኔና ትእዛዝ ይከበራል ብለዋል።

በገጠር አሰፋፈር ሥርዓቱ በሚከናወንባቸው ቦታዎች ደን መቁረጥ የማይቻልባቸው፣ ለአገልግሎቱ የሚውል የተከለለ ሕዝባዊ ስፍራ እንደሚኖርና በሁሉም አካባቢዎች እንደሚገኙም ነው የጠቆሙት።

"ሕብረብሔራዊ አንድነት ለዘላቂ ሰላም" በሚል መሪ ሃሳብ ዘንድሮ ለ17ኛ ጊዜ በሲዳማ ክልል አስተናጋጅነት የሚከበረው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል ላይ ከሚታዩት እሴቶች ይህ እንደሚሆን ይጠበቃል።

# ኢትዮጵያ በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ትገኛለች

**ዘሳለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በተደረገው የሟሟያ ኦዲት ኢትዮጵያ 88 ነጥብ 59 በማምጣት በአፍሪካ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገቧንና ዕውቅናና የሰርተፊኬት ሽልማትም መቀበሏን የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው መንግሥቴ እንደገለጹት፣ ውጤቱ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎቱ አስተማማኝ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

አቶ ጌታቸው ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት የካውንስል አባል ሆና መመረጧን አስመልክቶ ባለፈው ሳምንት በተዘጋጀው የእውቅና እና ምስጋና መድረክ ላይ ለብዙኃን መገናኛ ባለሙያዎች እንደገለጹት፤ ባለስልጣኑ አሠሩራን ይበልጥ አስተማማኝ ለማድረግ የራዳር ግዢ ለመፈጸም በሂደት ላይ እንደሚገኝና ግዢው በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በኩል እንዲፈጸም ሙሉ ውክልና መስጠቱንም አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ በ41ኛው የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት (ICAO) ካውንስል አባል ሆና መመረጧንና ይህም ለሀገርና ለአህጉር ጠቃሚ አሠራሮች እንዲተገበሩ ለመሞገት እንደሚያስችላትም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያን የአየር ክልል የሚያስተዳድረው የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን፤ በኮሙዩኒኬሽን፣ በናቪጌሽንና በቅኝት ሽፋን ይሰጣል፤ ለዚህም ዘመናዊ ራዳሮች እና የመገናኛ መሣሪያዎች አሉን ብለዋል።

ሆኖም መሣሪያዎቹ ጊዜአቸው እያለፈ በመሆኑ ምክንያት በተያዘው በጀት ዓመት አዲስ የራዳር ግዢ እንፈጽማለን። የራዳር ግዢው በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በኩል እንዲፈጸም የመግባቢያ ስምምነቱ በሂደት ላይ ይገኛል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በ41ኛው የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት (ICAO) ካውንስል አባል ሆና መመረጧን በማስታወስም፤ የሚወጡ እቅዶች፣ ሕጎችና አሠራሮች የኢትዮጵያን፣ ብሎም የአፍሪካን ጥቅም ያስከበሩ ለማድረግና በቀጥታ ተጽዕኖ ለመፍጠር እንደሚያስችል ነው የተናገሩት።

ኢትዮጵያ አባል ሆና መመረጧ በካውንስሉ የሚወሰኑ ውሳኔዎች የሀገርን ብሎም የአፍሪካን ፍላጎት እና ጥቅም መነሻ አድርጎ እንዲጸድቅ፤ ጉድለቶችን ለይተን የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ለማግኘት ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። በቀጣይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚረዳ ነውም ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለአየር ተመራጭ እንድትሆን እና ብሔራዊ አየር መንገዱ በሚኖሩት ዓለም አቀፍ መዳረሻዎች ተቀባይነቱ እንዲጨምር እንደሚያደርገውም ተናግረዋል።

የበረራ መዳረሻዎች፣ የአውሮፕላን ቁጥር፣ የአብራሪዎችና የቴክኒሽያኖች ቁጥር እየጨመረ እንደሚገኝ፤ ቴክኖሎጂውም እያደገ መሆኑን እና በዓለም አቀፍ ደረጃ መስፈርቶች ውስብስብ እየሆኑ በመምጣታቸው ብቃት ያለው የአቪዬሽን ባለስልጣን መገንባት የግድ እንደሚል አመልክተዋል።

ለ13 የግል ኦፕሬተሮች ፈቃድ በመስጠት የጄኔራል አቪዬሽን አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ጌታቸው፤ በአውሮፕላን ጥገና እና እድሳት፣ በአቪዬሽን ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን፣ በኤርፖርቶች ልማት፣ በሰው ሃብት ልማትና መሰል ዘርፎች የግል ባለሃብቱን ተሳትፎ በማሳደግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና የአፍሪካ ዋነኛ ማዕከል የሆነ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት እየሠራ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የካውንስል አባል ሆና ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት መመረጧ የተጻረሩ ሕጎችና አሠራሮች እንዳይወጡ ድምፅ ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

በደህንነት ምዘና ኢትዮጵያ ከፍተኛ ውጤት እንድታገኝና እንድትሸለም በማድረግ አስተዋጽዖ ያደረጉ ሁሉ ሊመሰገኑ ይገባል፣ የተገኘው ውጤት ድርብ ድል የሚያጎናጽፉት ነው ሲሉ አመልክተዋል። ‹‹ጥቅምን ማዕከል ያደረጉ አሠራሮች ወጥተው እንዲተገበሩ ድምፅ የምንሰጥበት ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ ተሳታፊ በመሆን እንጠቀምበታለን›› ነው ያሉት።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ደንጌ ቦሩ በበኩላቸው፤ በውድድሩ ኢትዮጵያ አሸናፊ መሆኗ ሌላ የተጎናጸፈችው ክብርና ድል መሆኑን ተናግረዋል። ለአቪየሽን ዘርፉ የማያቋርጥ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለውም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ከተቋቋመ 78ኛ ዓመቱን የያዘ ሲሆን፤ ባለፈው በጀት ዓመት 130 ዓለም አቀፍ መዳረሻዎችን፣ 67 የአየር ጭነት መዳረሻዎችን እንዲሁም በ22 የአገር ውስጥ መዳረሻዎች የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት መቻሉ ታውቋል።

# የደረሱ ሰብሎች ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ እንዳይጎዱ ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ተጠየቀ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በአንዳንድ አካባቢዎች እየተስተዋለ ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል ኅብረተሰቡ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የደረሰውን ስንዴና ጤፍ ለመሰብሰብ 1 ሺህ 500 ኮምባይነሮች በሀገር ደረጃ መሠማራታቸው ተገልጿል፡፡

የሚኒስቴሩ የሕዝብ ግንኙነትና የኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ አበራ ለማ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ የደረሱ ሰብሎችን ለመሰበሰብ ጥረት እየደተደረገ ባለበት ወቅት ሰሞኑን አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለ የደመና ሽፋን ወደ ዝናብ መሸጋገሩ ስጋትን ፈጥሯል፡፡

ቀደም ሲል የደረሱ የስንዴና የጤፍ ሰብሎችን ከብክነት በጸዳ መልኩ ለመሰብሰብ በሀገር ደረጃ 1 ሺህ 500 ኮምባይነሮች በኢንተርፕራይዞችና በዩኒዬኖች አማካኝነት ተሠማርተዋል ብለዋል፡፡

በመኸሩ ወቅት በአጠቃላይ 13 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኖ ወደ 400 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ መታቀዱን ያብራሩት አቶ አበራ፤ ከእነዚህም እስካሁን ወደ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ከሚጠጋው መሬት የደረሱ ሰብሎች የመሰብሰብ ሥራ መከናወኑን አመልክተዋል፡፡

በቆላማና በወይናደጋ አካባቢዎች እንደ ስንዴ፣ ማሽላ፣ ሰሊጥና ጤፍ ያሉ የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ያነሱት አቶ አበራ፤ በአንጻሩ ሰብሎች ገና በመድረስ ላይ ያሉ በደጋማ አካባቢዎች ለጊዜው ሥጋት እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡

ዝናቡ የደረሱ ሰብሎች ላይ ከፍተኛ የብክነትና የጥራት ጉድለት ችግር ሊያስከትል ስለሚችል ኮምባይነር ባለበት አካባቢ በኮምባይነር አሊያም አርሶ አደሩ በተደራጀ መልኩ ሰብሎቹን መሰብሰብ ይጠበቅበታል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች፣የከተማ ነዋሪዎችና የመንግሥት ሠራተኞች አርሶ አደሮችን እንዲያግዙ አቅጣጫ መቀመጡን አስታውቀዋል፡፡



እንደ አቶ አበራ ማብራሪያ፣ ዝናቡ የአጭር ጊዜ እንጂ ዘላቂነት እንደሌለው ከብሔራዊ ሜትዎሮሎጂ መረጃ ተገኝቷል፡፡ ሆኖም በመረጃው መዘናጋት አስፈላጊ ባለመሆኑ ዝናቡ ቢያቆምም ምርትን ከብክነት በጸዳ መልኩ ለመሰብሰብ ርብርብ ማድረግ ምን ጊዜም ወሳኝ ነው፡፡

አርሶ አደሮች ከቤተሰቦቻቸውና ከጎረቤታቸው በዘለለ እልፍ ብለው የደረሱ ሰብሎችን ተጋግዘው እንዲሰበስቡ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሠራቱን የገለጹት አቶ አበራ፤ በአንጻሩ አርሶ አደሮቹ ተባብረው ከሠሩ በእቅዳቸው መሠረት በዝናብ ያልተጎዳና ከብክነት የጸዳ ጥራት ያለው ምርት እንደሚያገኙ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል፡፡

## የናይሮቢው ውይይት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተናግረው፤ በተደረገው ውይይት መግባባት ላይ መደረሱንና ይህንንም መፈራረማቸውን ተናግረዋል፡፡

ኤታማዦር ሹሙ እንደተናገሩት፣ የፕሪቶሪያው ስምምነት ጥሩ እና ወደ ሕግና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ለመምጣት ፍላጎት የታየበት ሲሆን በተመሳሳይ የናይሮቢው ውይይት ያሉ ክፍተቶች እንዲዘጉና በአተገባበሩ ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዲደረስ ያስቻለ መሆኑን አብራርተዋል።

ያለፉት አራት ዓመታት ለኢትዮጵያ ከባድ ጊዜያት ነበሩ ያሉት አዛዡ፤ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የመቀጠልና ያለመቀጠል ትንቅንቅ ውስጥ መቆየቷን አንስተው ለውጡ ሲመጣ ያኮረፉ ኃይሎች በመኖራቸው ምክንያት በየቦታው የፀጥታ ችግር እና ሌሎች ውጣ ውረዶች ሲከሰቱ መቆየታቸውን አብራርተዋል።

ሆኖም የሀገር መከላከያ ሠራዊት ሀገሩን ማዕከል አድርጎ የተከሰቱ ሀገር አፍራሽ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር ደፋ ቀና ሲል መቆየቱን አስታውሰው ሠራዊቱ በዚህ ሁኔታ እያለ በደረሰበት ጥቃት ሀገሪቱ ተገድዳ ወደ ጦርነት በመግባቷ ምክንያት በሀገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል ሰላም ርቆ መቆየቱን ጠቁመዋል።

ጦርነቱ ከተካሄደ በኋላም ሰላም ማምጣት ይቻል ነበር ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ ሆኖም ሰላም በአንድ ወገን ፍላጎት ሊመጣ የማይችል በመሆኑ ኢትዮጵያ ተደጋጋሚ የሰላም ዕድሎችን ብታመቻችም ሳይሳካ መቆየቱን ተናግረዋል።

ጦርነቱ ከባድ እና ሀገሪቷን ብዙ ዋጋ ያስከፈለ ነው ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ አሁን ከደምና ከውድመት ተምረን ችግሮችን ለመፍታት የተካሄደው የሰላም ድርድር ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ተናግረዋል። የሰላም ስምምነቱ ከረፈደ የመጣ ቢሆንም መልካም ነው ብለዋል።

እንደ ፊልድ ማርሻሉ ገለጻ፤ ከዚህ በኋላ ሀገሪቷ ጦርነት የምትሸከምበት ትከሻ የላትም። አሁን ትግራይ ያለው አመራር ይህን የተረዳ ይመስላል። በመሆኑም በፕሪቶሪያ የተደረገው ስምምነት በጣም ጥሩ የሚባል ስምምነት ሊካሄድ ችሏል።

ሁሉም በሰከነ መንገድ ወደ ሕግና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እና ችግርን በውይይት ወደ መፍታት እና የተበላሹ ነገሮችን ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ለማስቻል በሁለቱም ወገን መግባባት ላይ መደረሱንም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ተናግረዋል።

## የቱሉ ዲምቱ-ቃሊቲ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ወጪ እየተከናወነ ይገኛል።

መንገዱ ከደቡብ፣ ከምስራቅና ከሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ አቅጣጫና ከጅቡቲ የሚመጡ ተሽከርካሪዎች የመውጫና የመግቢያ መስመር በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የጎላ ነው ያሉት አቶ እያሱ፤ እስካሁን ባለው ሂደት የመንገዱ 55 በመቶ የሚሆነው ግንባታ ተጠናቋል፤በተለይ ከፍተኛ ጊዜና በጀት የሚጠይቁ ሦስት የማሳለጫ ድልድዮች መገንባታቸው ፕሮጀክቱን ቶሎ ለማጠናቀቅ ይረዳል ብለዋል።

አቶ እያሱ እንደተናገሩት፤ ቃሊቲ ማሰልጠኛ የቀለበት መንገድን በውስጥ በኩል የሚያልፍና 140 ሜትር ርዝመት ያለው ባለ ሁለት አቅጣጫ ድልድይ ግንባታ ተጠናቋል። ሌላው ወደ ጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል አካባቢ 90 ሜትር ርዝመት ያለው የማሳለጫ ድልድይ ግንባታም ተከናውኗል።

ከዚህም በተጨማሪ በተለምዶ ጋሪ ድልድይ በሚባለው አካባቢም 50 ሜትር ርዝመት ያለው የመሳለጫ ድልድይ ተገንብቷል። እነዚህን ጨምሮ የመንገዱ ቀኝ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ አስፋልት ለብሶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል ሲሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

እንደ አቶ እያሱ ገለፃ፤ ፕሮጀክቱ በሁለት ጉዳዮች ሊዘገይ ችሏል። አንደኛው ከወሰን ማስከበር ጋር የተያያዘ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የበጀት ማነስ ነው። በዚህም በመንገዱ የግራ ክፍል የሚያልፍ የከርሰ ምድር ውሃ ተሸካሚ ማስተላለፊያ መስመር ለማንሳት የወሰደው ጊዜ ለግንባታው መዘግየት ምክንያት ሆኗል።

ከዚህ ውጪ መንገዱ ወደ ጎን 50 ሜትር ስፋት እንዲኖረው በመደረጉ በሰፋው ሜትር ልክ የነበሩ ቤቶችና የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን ለማንሳት የፈጀው ጊዜ ለፕሮጀክቱ መጓተት ሌላኛው ምክንያት ነው።

በአሁኑ ወቅት ግን እነዚህን ችግሮች መፍታት የተቻለ ሲሆን ሌሎች ችግሮች በሂደት እየተስተካከሉ ይመጣሉ ብለዋል።

ሌላኛው ምክንያት የቻይናው ኢግዚም ባንክ ለፕሮጀክቱ እሰጣለሁ ያለውን ብድር ሙሉ ለሙሉ ባለመስጠቱ ፕሮጀክቱ ተጓቷል። በመሆኑም የከተማው አስተዳደርና የፌዴራል መንግሥት መንገዱ ካለው ፋይዳና ኅብረተሰቡ ከሚያነሳው የልማት ጥያቄ አንጻር ምላሽ መሠጠት እንዳለበት በማመን የመንገዱን ቀሪ ግንባታ ለማጠናቀቅ የ2 ቢሊዮን ብር ድጋፍ አድርጓል ሲሉ አቶ እያሱ ገልጸዋል።

በአሁኑ ሰዓት የፕሮጀክቱን የማማከር ሥራ እስክንድር አማካሪ ድርጅት እያከናወነ ሲሆን የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ደግሞ የክትትልና የቁጥጥር ሥራውን እየሠራ ይገኛል ብለዋል፤ ከቱሉ ዲምቱ- ቃሊቲ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ጋር እኩል ተቋርጦ የነበረው የቂሊንጦ-ቃሊቲ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በዚህ ዓመት ለማጠናቀቅ መታቀዱን ተናግረዋል።

የቂሊንጦ-ቃሊቲ የመንገድ ግንባታ ቡልቡላ አካባቢ ባለው ድልድይ ምክንያት ተቋርጦ የነበረ ሲሆን የአስፋልት ማንጠፍ ሥራው ተከናውኗል። መንገዱም 10 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ነው በማለት ኅብረተሰቡ ስለነበረው ትዕግስት በባለስልጣኑ ስም አመስግነዋል።

## ‹‹የሰላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ አባተ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ የጥይት ድምጽ እንዳይሰማና ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ የሚያደርግ ስምምነት መደረጉም ትልቅ ስኬት ነው፡፡ ይኸው በቅርቡ በደቡብ አፍሪካ ላይ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተካሄደው የሰላም ስምምነት የኢትዮጵያውያኑን ቁርጠኝነትና ጽኑ አቋም ያሳየ ነው፡፡ አፍሪካ ለራሷ ችግር በራሷ ልጆች መፍትሔ ማምጣት እንደምትችልም ያመላከተ ሲሆን፣ ሌሎቹ የአፍሪካ አገራትም በአህጉሪቱ ላይ እምነት እንዲያሳድሩ የሚያደርግ ነው፡፡

ይህን የአህጉሪቷን መንገድ ሌሎች አገሮችም ሊያከብሩላት ይገባል ያሉት አቶ አባተ፣ አፍሪካውያንም ችግር ቢፈጠርባቸው ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ በማድረግ ረገድ ኢትዮጵያ የተጫወተችው ሚና የላቀ ነው ብለዋል፡፡ ይህም ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካ ትልቅ ኩራት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ የሰላም ስምምነቱ ኢትዮጵያ ቀደምት የአፍሪካ መሥራችነቷ ክብር ዳግም እንዲሰጣት ያደረገ ነው፡፡ በቀጣይ በአፍሪካ ለሚኖሩ ግጭቶችም ጭምር በኢትዮጵያ አማካይነት መፍትሔ ማስቀመጥ እንደሚቻልም ያሳየ ነው፡፡

አቶ አባተ፣ አድዋ ለጥቁሮቹ የአልደፈርምና የአልገዛም ባይነትን መሠረት የጣለ መሆኑን አስታውሰው፤ ይህም የሰላም ስምምነት ማንም እንደፈለገ ጣልቃ ገብቶ እኔ ያልኩትን ብቻ አድርጉ ብሎ እንዳይወስን የሚከላከል ነው ብለዋል፡፡ ስምምነቱ ሌሎች አፍሪካዊ ወንድሞቻችንም አፍሪካ በአፍሪካውያን መፍትሔ ማምጣት ትላለች ብለው እንዲያምኑ አድርጓልና በአንድ በኩል ለአፍሪካ ትልቅ ክብር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አፍሪካውያን የራሳቸውን ችግር በራሳቸው አቅም ለመፍታት እንደሚችሉ ማሳያ መሆኑንና ለዚህ ደግሞ ለቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ለኦሊሴንጉ ኦባሳንጆ እና ለቀድሞው ቀድሞው የኬንያ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ትልቅ አክብሮት እንዳላቸውም አስረድተዋል፡፡

አቶ አባተ አፍሪካ በመታረቅና በማስታረቅ ሥራ ላይ መጠመድና በዚህም ተግባር መገታት እንደሌለባት ጠቅሰው፤ በዓለም አቀፉም ማኅበረሰብ ዘንድ የውሳኔ አካል በመሆን ድርሻ ሊኖራት ይገባል ብለዋል፡፡ ማንም ቢሆን ይህ ለአፍሪካ ተገቢ ቦታ ነው ብሎ ሊሰጠን አይችልም ያሉት አቶ አባተ፣ እኛ አፍሪካውያን ራሳችን ቁርጠኞች ሆነን ተገቢ ቦታ ላይ ለመድረስ መጣጣር አለብን ሲሉም ተናግረዋል፡፡ ይህም ደቡብ አፍሪካ ላይ በተደረሰው የሰላም ስምምነት ተጀምሯል ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል፡፡

አቶ አባተ፣ ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀደምት ከሚባሉ ሀገራት መካከል ተጠቃሽ ነን። መንግሥት ያለን፣ ዴሞክራሲን ለሌሎች ያለማመድን እንዲሁም በርካታ እሴቶች ያሉን ነን፡፡ በመሆኑም የውስጥ ችግራችንን ወንድሞቻችን ወደሆኑት አፍሪካውያንም ድረስ ሳይደርስ እና እነርሱንም ሳናደክም ችግሮቻችንን በራሳችን መፍታት እንችላለን›› ብለዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ የመጀመሪያው የጦርነት ሰለባ የሆነውና የሚሆነው ራሱ ኅብረተሰቡ በመሆኑ ከስምምነቱ በኋላ ከኅብረተሰቡ የተደመጠው እፎይታ ነው፡፡ የጥቂት ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች አዕምሮ ውስጥ ያለው ነገር ግን በየሰው ልብ ውስጥ ያለውን ረመጥ በመቆስቆስ ከፍሙ በመሞቅ የራስን ኑሮ ማደላደል የሚፈልግ አይነት ስሜት ነው፡፡ ሰው እንዲጋጭና እንዲፈናቀል ሌሎች ሰበቦችን የምንፈልገው እኛ ጥቂት ፖለቲከኞች ነን ባዮች ነን፡፡ ይህ ጎደለብህ፤ እዚህ ላይ ተጨማሪ የለህም፤ አንተኛው አሸነፍክ፤ ያኛው ደግሞ ተሸነፈ እያልን ከበሮ የምንደልቀው እኛው ፖለቲከኞች ነን፡፡ ሕዝብ በዚህ የሰላም ስምምነት ጉዳይ ቁርጠኛ ነው፡፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጦርነቱ ይቁም እንጂ ሌላ ፍላጎት የለውም፡፡ ጦርነት ሲቆም ሰው አይሞትም፤ ጦርነት ሲቆም ሰው አይፈናቀልም፡፡ ስለዚህ በሕዝብ ልብ ውስጥ የጦርነቱ መቆም የፈጠረው ስሜት በፖለቲከኞቹና በአክቲቪስቶቹ አካባቢም ቢፈጠር ሰላሙን በአግባቡ ማጣጣም ይቻላል፡፡

ለሰላም መስፈን አንድ ጠብታ አስተዋጽኦ ላይጨምር በየአህጉራቱ ተሰልፎ ይህ ጎድሎብሃልና መጮህ አለብህ፣ ይህንን አጥተሃልና ጦር መምዘዝ አለብህ ብሎ የሚያዘውን አካል ስፍራ አለመስጠት መልካም ነው ያሉት አቶ አባተ፣ ያለፈን በመነካካትና ያልተፈጠረውን እንደተፈጠረ አድርጎ ማቅረብ የሕዝብ መፈናቀልና ከኑሮው መስተጓጎል ውጭ የሚያመጣው ፋይዳ የለውም ብለዋል፡፡

የሰላም ባለቤት ራሱ ሕዝቡ ነውና ስምምነቱንም ተቀብሎታል ያሉት አቶ አባተ፣ ሕዝቡ የሰላም ስምምነቱን በተቀበለው ልክ በየቦታው እና በየደረጃው የሚገኙም መሪዎች ለዚህ ጉዳይ በተለይ ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰዎች ኃላፊነቱን ሊወስዱ ይገባል ብለዋል፡፡ በጦርነት ለዘመናት ብንቆይም እንኳ ጎዶሏችንን አንሞላውም ሲሉ ጠቅሰው፤ ያለፈውን እያሰብን የወደፊታችንን ማበላሸት ለሰላም የሚያመጣው አስተዋጽኦ እንደሌለው አመልክተዋል። በተለይ ማሳሰብ የምፈልገው ፖለቲከኞቹ ከአዙሪትና ከጀብደኝነት ስሜት ወጥተው ሕዝባቸው ወደሰላም እንዲመጣ ማድረግ ግዴታ ውስጥ መግባት አለባቸው። አሁንም የውይይቱ ማዕከል መሆን ያለበት ሰላም ነው ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሃገር ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከፖለቲካ አስተሳሰብ በላይ ናት!

ማንም ቢሆን በየትኛውም መንገድና ሁኔታ ከኛ በላይ የኛ ጉዳይ ሊያሳስበው ይቻላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ከዚህም ባለፈ ለችግሮቻችን ከሌላ አካል መፍትሔ ለማፈላለግ መሞከር ድንገትም ከየዋህነት ባለፈ ቂልነት ሊሆን ይችላል ።

በተለይም ባለንበት ዘመን እያንዳንዷ እንቅስቃሴ የተለያየ ስም እየተሰጣት ጥቅም አነፍናፊነት በገነነበት ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ውስጥ፣ የራስን ጉዳይ ለሌላ አካል ሰጥቶ ዘላቂ መፍትሔ የመፈለግ አካሄድ ብዙም አዋጭ አይደለም። ድርጊቱ ብሔራዊ ጥቅምን አሳልፎ ከመስጠት የሚተናነስ ላይሆን ይችላል ።

እያንዳንዱ ዜጋም ይህንን ዓለምአቀፋዊ እውነታ በአግባቡ በመረዳት ከገባንበት ችግር ለዘለቄታው በመውጣት የጀመርነውን ልማት አስቀጥለን ሀገራዊ እና ትውልዳዊ ግባችን ያደረግነውን ብልጽግና እውን ለማድረግ ራሳችንን በሁለንተናዊ መልኩ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል ።

በርግጥ በቀደመው ዘመን በአግባቡ መደማመጥ አቅቶን፣ ከትናንት የከፉ አስተሳሰብ አንጎበር መውጣት ተስኖን ፤ ከሁሉም በላይ ከትናንት ጥቁር ታሪኮቻችን ለመማር ባለመፍቀዳችን ያልተገባ ዋጋ ከፍለናል። በዚህም እንደ ትውልድ እኛም በታሪካችን ውስጥ ተጨማሪ ጥቁር ጠባሳ/ታሪክ አስቀምጠን ለማለፍ ተገደናል ።

ትናንት የሆነብንን በየትኛውም መልኩ ልንለውጠው አንችልም፤ አባቶች "የፈሰሰ ውሀ አይታፈስ" እንደሚሉት አንዴ ሆኗልና። ስለሆነው ነገርና ስለከፈልነው ያልተገባ ዋጋ ግን ቢያንስ ቢያንስ ያለማንም ወትዋች/ጎትጓች ከልባችን ልንጸጸትና ልንማርበት ይገባል ።

መጸጸታችን ፤ መሳሳታችንን ከማመን ብቻ ሳይሆን ፤ አንድም ስህተታችን የቱን ያህል ሕዝባችንንና ሀገራችንን ያልተገባ ዋጋ እንዳስከፈለ በማጤን ፤ ከዚያም በላይ ከታሪክ መማር አቅቶን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ፤ ዘመኑንና የዘመኑን አስተሳሰብ የማይመጥን ስህተት መሥራታችንን ከመረዳት የመነጨ ሊሆን ይገባል።

መጸጸታችን ፤ በቀጣይ ተመሳሳይ ስህተት ላለመድገም ብቻ ሳይሆን አሁን የሠራነው ስህተት በሀገርና በሕዝብ ላይ ያስከተለውን ሁለንተናዊ ቀውስ እንዳይደገም ለማድረግ ባለን አቅም ሁሉ ተሳታፊ በመሆን ትናንትን ዛሬ ላይ ለመካስ ከራሳችን ጋር ቃል በመግባት መሆን አለበት ።

በተለይም በሃገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎችና በፓርቲ ፖለቲካ የሀገርና የሕዝብ ዕጣ ፈንታ የተሻለ ይሆናል ብለው የሚያምኑ ፖለቲከኞቻችን ከዚህ ስህተታችንና ስህተታችን ፈጥሮት ካለፈው የሀገር ሕልውና አደጋ በአግባቡ ሊማሩ ይገባል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ሆኑ የፖለቲካ ፍላጎታቸው ነፍስ ዘርቶ ሃገርን ሆነ ሕዝብን ሊጠቅም የሚችለው ሃገር ቀድማ ስትኖር ብቻ መሆኑን ሊዘነጉት አይገባም ፤ ይህን ታሳቢ ያላደረገ ፖለቲከኝነት ሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብ ሀገርና ሕዝብን ያልተገባ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ ትርጉም አይኖረውም። ይህንንም ከትናንት ስህተታችን እና ስህተታችን ካስከፈለን ዋጋ ለመማር ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል ።

ሀገርና ሕዝብን አደጋ ውስጥ ወደሚከት ያልተገባ መንገድ የምናደርገው የእልህ ጉዞ ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ብቻ ሳይሆን እንደሀገር እንድንቀጥል ለማይፈልጉ ኃይሎች አሳልፎ እንደሚሰጠን ፤ይህም ስለ ስህተታችን የምንከፍለውን ዋጋ በአንድሺ አንድ እጥፍ ሊያሳድገው እንደሚችል መርሳት አያስፈልግም ።

ትናንት ገብተንበት የነበረው ችግራችን ምን ያህል ብዙዎችን እንደጋበዘ ፤ ከግብዣው በስተጀርባ የነበሩ መሻቶች የቱን ያህል ከገባንበት ችግር በላይ እንደተፈታተኑን የምንረሳው አይደለም ።

ይህ በአደባባይ ያጋጠመን እና ከፉኛ የተፈታተነንን ተግዳሮት እንዳላየ እና እንዳልሰማ ልንሆን አንችልም ፤ከዛ ይልቅ ዓይኖቻችንን እና ጆሮዎቻችንን ከፍተን ደጋግመን ልናየውና ልናዳምጠው የሚገባ ፤ስለ ነገዎቻችንም ብዙ ልንማርበት የሚገባ ነው ።

እያንዳንዱ ዜጋም ሀገር ከፖለቲከኞች እና ከፖለቲካ ፍላጎቶቻቸው በላይ የሆነች፤ እንደ ፖለቲከኞች እና አስተሳሰቦቻቸው በተወሰነ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ታይታ የማትጠፋ፤ በብዙ ትውልዶች የተንሰላሰለ ተጋድሎ ዘመናትን እየተሻገረች ስለመምጣቷ በአግባቡ መረዳት ይጠበቅበታል!


እፎይ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የሠላም ስምምነቱ ሠላም የነሳቸው የሞት ነጋዴዎች!

ዳንኤል ዘነበ

በደቡብ አፍሪካ የሰሜኑ ጦርነት በሠላም መቋጨት የሚያስችል የሠላም ሥምምነት ተፈርሟል። ያውም በአፍሪካውያን አደራዳሪዎች (ድርድሩን ከአፍሪካ እጅ ለማስወጣት ብዙ ጥረት ቢደረግም፤ አፍሪካዊ ሃሳብ ማሸነፍ ችሏል)። ይህም ስምምነት በብዙ መልኩ ታሪካዊ ያደርገዋል፤ በተለይ ለኢትዮጵያውያን።

በእርግጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ የጦርነት የታሪክ ምዕራፎችን አልፏል። በነዚህ የታሪክ ምዕራፎች ያለፈ ሕዝብ የሠላም አማራጮች ቀርበውለት ተራምዶ ይሄዳል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። የሆነውም ይኸው ነው። እውነተኛ ሠላምን የመሻቱ ፍላጎት ሲመጣ ለመቀበል አሻፈረኝ አላለም።

የኢትዮጵያ መንግሥትም የሕዝቡን ፍላጎት ባዳመጠ መንገድ በደቡብ አፍሪካ ለሰላም ድርድር ወንበር ስቧል። የአገርን ሉዓላዊነት ያከበረ ሥምምነት ፈርሟል። የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያዊነት መልክ የሆነው የትግራይ ሕዝብ አንገቱን ቀና እንዲያደርግ ያለውን ፍላጎት በተግባር አረጋግጧል።

ስምምነቱን ተከትሎ በአገሪቱ አራቱም ማዕዘናት ስለስምምነቱ የታየው እና እየተሰማ ያለው እውነታ፤ ሕዝባችን ስለሰላም ያለውን የጸና እምነት ከማሳየት ባለፈ ጦርነት የቱን ያህል አውዳሚ እንደሆነ መገንዘብ መቻሉን በተጨባጭ ያመላከተ ነው። ሠላም ሲመጣ አየሩን የደስታ መንፈስ መሙላቱም የሠላም ዋጋን ጠንቅቆ ከሚያውቅ ሕዝብ የሚጠበቅ ነው ፤ ያዝልቅልን እንጂ !።

ስምምነቱን ወደ ተሟላ እርቅ ለመቀየር በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተጀመረው ውይይት እንደቀጠለ ነው። የሕወሓት ታጣቂዎችን ትጥቅ የማስፈታት ሂደቱን (በሰላም ስምምነቱ የተደረሰበትን) ለማሳለጥ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትና የትግራይ ታጣቂዎች አዛዦች ናይሮቢ ላይ ተገናኝተው እየተወያዩ ነው።

ውይይቱን አስመልክተው የቀድሞ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ፤ «ፕሪቶሪያ ጀምረናል፤ እየተጠጋን እንገኛለን፤ እናም አሁን ናይሮቢ ነን። በሚቀጥለው ጊዜ መቀሌ ተገኝተን ለስብሰባችን ማሳረጊያ አዲስ አበባ ላይ አብረን እንደምንደሰት ትልቅ ተስፋ አለን። ጸሎት እና ተስፋችን ይህ እንዲሆን ነው» ሲሉ፤ የሰላም ድርድሩ ከስምምነት ተሻግሮ ወደመሬት እየወረደ መሆኑን ጠቁመውናል።

የኡሁሩ ንግግር የሰላም ስምምነቱ በሚፈለገው መልኩ እየሄደ ከመሆኑ ባሻገር በተጨባጭ ከጦርነት አዙሪት የምንወጣበት ጊዜ ሩቅ አለመሆኑን አመላክቶናል፤

**እነዚህ ኃይሎች የትግራይ ሕዝብ በጦርነቱ ምክንያት የከፈለው አሳስፈሳጊ ዋጋ አስፈሳጊ ነው ብለው፤ ከሕዝቡ ማሓበረሰባዊ ስብዕና ባፈነገጠ መንገድ የሚያስቡ፤ በሕዝቡ ሞት፣ መከራና ስቃይ የፖለቲካ ትርፍ የሚሹ ስለመሆናቸው ሥራቸው በራሱ የሚናገረው ነው**

ያድርግልን!። በምድራችን ዛሬ እንዲነግስ የምንሻው ሠላም ፋይዳው ተሻጋሪ፤ ለልጆቻችን ነገ የምናወርሳትን አገራዊ ቁመና የሚወስን ነውና።

ለመጪው ትውልድ ልናወርሳት የምንፈልጋት አገር በጦርነት የጥላቻ አዳፋ የጠቆረች ሳይሆን በአብሮነት ክንፍ በሙብረር፤ በእድገት የተመሰገነች አገር ነው። ለዚህ ደግሞ የሰላም ስምምነቱ ውጤታማ መሆን አልፋና ኦሜጋ ነው።

የሠላም ስምምነቱ አሁንም በሆነው አገራዊ አውድም፤ የሚኖረው ትርጉምም በጦርነቱ ምክንያት ለህልፈት ሊዳረጉ የሚችሉ ዜጎችን ሕይወት ለመታደግ፣ በጦርነት የተጎዱትን ወገኖቻችንን መልሶ ለማቋቋም፣ የፈረሱ መሠረተ ልማቶችን እንደገና ለመገንባት ያስችላል። ለጦርነት ሲውል የነበረውን በጀት ወደልማት በማዞር ኢኮኖሚው እንዲያገግም ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተጨማሪም የውጭ ኢንቨስትመንትን በስፋት ወደ አገር ውስጥ በመሳብ ባለሀብቶች ያለ ስጋት እንዲተሙ ያደርጋል።

ለዚህና ከዚህም በላይ ሊሆኑ በሚችሉ ምክንያቶች ነው በአገር ውስጥ ሆነ ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሠላም ስምምነቱ የተሰማቸውን ደስታና እፎይታቸውን ሲገልጹ ማየታችን። ከሰሞኑ የአሜሪካ ድምጽ (ቪኦኤ) የመቀሌ ነዋሪዎችን አነጋግሮ የሠራው ዘገባ ለዚህ ትልቅ ማሳያ ነው።

በተቃራኒው ደግሞ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ያንዣበበውን ሠላም ለማደፍረስ ደፋ ቀና የሚሉ እየተመለከትን ነው። በተለይ ደግሞ በትግራይ ሕዝብ ስም የትግራይን ሕዝብ ልባዊ የሠላም ፍላጎት ለማዳፈን የሚጥሩ፤ ይህንኑ አላማቸውን በአደባባይ ሳይቀር ሲያስተጋቡ መስማታችን ከፍ ያለ የልብ በስብራት እየፈጠረብን ነው።

እነዚህ ኃይሎች የትግራይ ሕዝብ በጦርነቱ ምክንያት የከፈለው አላስፈላጊ ዋጋ አስፈላጊ ነው ብለው፤ ከሕዝቡ ማኅበረሰባዊ ስብዕና ባፈነገጠ መንገድ የሚያስቡ፤ በሕዝቡ ሞት፣ መከራና ስቃይ የፖለቲካ ትርፍ የሚሹ ስለመሆናቸው ሥራቸው በራሱ የሚናገረው ነው። ቀደም ባለውም ጊዜ ከግጭቱ ጀርባ በመሆን ግጭቱ ላይ ከጀርባ ሆነው ቤንዚን ሲያርከፈክፉ የነበሩ ከፉ የሞት ነጋዴዎች ናቸው።

ቀደም ባለው ጊዜ አውሮፓና አሜሪካ ላይ ቁጭ ብለው ድሃውን የትግራይ ሕዝብ ግፋ በለው ሲሉ የነበሩ፤ ጦርነቱን በሚፈልጉት ልኬት እየለኩ ሲጮሁና ሲያጯጩሁ የነበሩ ናቸው። አሁን ደግሞ የትግራይ ሕዝብን ልባዊ የሠላም ፍላጎት ለማዳፈን ነጠላ ዘቅዝቀው አደባባይ እየወጡ ናቸው።

የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ ጋር ሕዝብ አብሮ እንዳይኖር 'እንዴት ሰላም፤ ጦርነት ይሻልሀል !' እያሉ በሰለጠነው ዓለም አደባባዮች እያደረጉት ያለው የጦርነት ስብከት ሁላችንንም አንገት የሚያስደፋ አሳፋሪ ተግባር ነው። ትናንት የትግራይ ሕዝብ ተራበ ፣ ሞተ ፣ ተሰቃየ .... በሚል ያሰሙት የነበረው ጩኸት 'እውነት ለትግራይ ሕዝብ ከማዘን የመነጨ ነበርን ' የሚል ጤናማ ጥያቄ እንድንጠይቅም ያስገድደናል።

በተመሳሳይ ባህር ማዶ ተቀጥረው በጋዜጠኝነት ካባ፣ በፖለቲከኛ ጭንብል እና በብሔርተኝነት ጫካ ውስጥ ተደብቀው «ሰላም ይሻላል» በሚል ሲያደነቁሩን የነበሩት እነዚህ ኃይሎች ጨዋታ ቀይረው ጦርነት ሰባኪ መሆናቸው «እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል» እንደሚባለው እውነተኛ ማንነታቸውን ለአደባባይ አብቅቶታል።

እነዚህን ኃይሎች የተፈጠረውን ሰላም ለማደብዘዝ በአንድነት ተሰባስበው ዘመቻ ላይ እንዳሉ ሁሉ፤ እኛም (ኢትዮጵያውያን) በአንድነት ሆነን ስለሠላማችን ዘብ መቆም ይጠበቅብናል። በተለይ የትግራይ ሕዝብ እነዚህ ኃይሎች በቃችሁ በማለት ሠላሙን መጠበቅ ይኖርበታል። ዘላቂ ሠላም ለአገራችን፤ ለኢትዮጵያችን !።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የፋሽን ኢንዱስትሪው ፈተና የሆነው የልባሽ ጨርቆች ገበያ

ልባሽ ጨርቆች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ከከለከሉ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ውስጥ አንዷ በሆነችው ኢትዮጵያ ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡ የጨርቃጨርቅ ምርቶች ውስጥ ግማሽ ያህሉ በሕገ-ወጥ መንገድ እንደሚገቡ አዲስ ዘይቤ በቅርቡ ያስነበበው ሰፊ ሃተታ ላይ የሰፈረው መረጃዎች ያመለክታል። ከዚህ ዘገባ መረዳት እንደሚቻለውም የልባሽ ጨርቆች ወይም በተለምዶ ሰልባጅ ተብሎ የሚጠራው የልብስ ገበያ በአገሪቱ የፋሽን ኢንዱስትሪ ላይ ፈተና እንደሆነ ነው፡፡

ዘገባው ላይ እንደተቀመጠው ያገለገሉ አልባሳት ንግድ በከፍተኛ መጠን ያደገው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው። የፋሽን ኢንዱስትሪው ፈጣን እና ተቀያየሪ የአለባበስ ዘይቤን መከተሉ ከጥቂት አገልግሎት በኋላ የማይፈለጉ አልባሳትን ቁጥር በእጅጉ ጨምሮታል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የሚከማቹትን የማይፈለጉ አልባሳት ማስወገድ የመንግሥታት ፈተና እስከመሆን ደርሷል።

የቆሻሻ ክምችትን ይጨምራሉ፣ የአካባቢ ብክለትን ያባብሳሉ፣ ለምርት የወጣባቸውን ንጥረ-ነገር ያባክናሉ የሚባሉት የማይፈለጉ ልባሽ ጨርቆች አንዱ መዳረሻቸው በማደግ ላይ የሚገኙ የአፍሪካ አገራት ናቸው። የምዕራቡ ዓለም የኢኮኖሚ አሻጥረኞችም ዝቅ ባለ ዋጋ የሚቀርበውን የቻይናን ምርት ስርጭት ለማዳከም እንደመሣሪያ እየተጠቀሙበት ነው የሚሉ ተንታኞችም አሉ፡፡ እነኚህ ወገኖች የአፍሪካ አገራት በልባሽ ጨርቆች ንግድ ጉዳይ የእገዳ ሕጎች ሲያወጡ አሜሪካ እንደ አጎዋ ካሉ የንግድ ስምምነቶች የማስወጣት ውሳኔ ማሳለፏን የጉዳዩን ውስብስብነት ለማሳየት ተጠቅመውበታል።

በኢኮኖሚ ካደጉት ምዕራባውያን አገራት የሚነሱት ልባሽ ጨርቆች (ሰልባጅ) መዳረሻቸው ከሰሀራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገራት ናቸው። የገቢያቸውን አብዛኛውን ድርሻ ለምግብ ወጪ የሚያውሉ ብዙ ዜጎች ላላቸው ድሃ አገራት ሰልባጅ ዋነኛ የአልባሳት አቅርቦት ምንጭ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በንግድ ሰንሰለቱ ላይ የሚገኙ እንደ ጫኝና አውራጅ፣ ቸርቻሪ፣ አጣቢ፣ ጠጋኝ ያሉ የሥራ መስኮች ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች በሂደቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ።



ሰልባጅ ተብሎ የሚጠራው የልብስ ገበያ በአገሪቱ የፋሽን ኢንዱስትሪ ላይ ፈተና እየሆነ ይገኛል፣

የልባሽ ጨርቆች ንግድ በሚፈቅዱ አገራት የገቢ ግብር የሚሰበሰብበት ሕጋዊ የንግድ ዘርፍ ሲሆን በተለይ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት አምራች እና አስመጪዎችን አያበረታታም በሚል በሕገ-ወጥነት ተፈርጇል፡፡

ልባሽ ጨርቆች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ከከለከሉ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ውስጥ አንዷ በሆነችው ኢትዮጵያ ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡ የጨርቃጨርቅ ምርቶች ውስጥ ግማሽ ያህሉ በሕገ-ወጥ መንገድ እንደሚገቡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለምአቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር አስናቀ ከፋለ ከዓመት በፊት ካሰናዱት ጽሑፍ የተገኘ መረጃ ያመለክታል። እገዳ ስለተጣለባቸው በስውር ወደ አገር ውስጥ የሚገቡት ልባሽ ጨርቆች ለሽያጭ የሚቀርቡት በግልጽ በአደባባይ ነው። ከፍ ያለ የልባሽ ጨርቆች ግብይት ከሚካሄድባቸው የአገሪቱ ከተሞች መካከል አንዷ አዳማ ናት። በኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞንና በቦረናም ይህ ንግድ በስፋት ይስተዋላል፡፡

ለእርጅና ሳይደርሱ ጥቂት ጊዜ አገልግለው ለአዳማ ገበያ ከሚቀርቡ መገልገያዎች ውስጥ አልባሳት (የወንድ፣ የሴት፣ የሕፃናት)፣ ጫማዎች፣ የወንድ እና የሴት ቦርሳዎች፣ የሕፃናት መጫወቻዎች ይገኙበታል። ቁሳቁሶቹ አዳማ የሚደርሱት በሁለት የድንበር መተላለፊያዎች ማለትም በሶማሌላንድ ድንበር ቶጎ ውጫሌ እና በኬንያ ሞያሌ በኩል ነው።

አልባሳት የታጨቀባቸው ግዙፍ የሸራ ጥቅሎች «ቦንዳዎች» እና ጫማዎች በጭነት እንስሳት፣ በሞተር ሳይክሎች፣ በጭነት ተሽከርካሪዎች ድንበሮቹን አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ ይገባሉ። በድንበር ከተሞች ለሽያጭ በጅምላና በችርቻሮ ከቀረቡ በኋላ በሦስት ዓይነት ነጋዴዎች ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ይሰራጫሉ።

የችርቻሮ ነጋዴዎች ልብሶቹን እና ጫማዎቹን በመደበኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መደበኛ ተጓዥ በመምሰል ዕቃዎቹን ለማሳለፍ የሚሞክሩበት የመጀመሪያው መንገድ ነው።

ሁለተኛው የጅምላ ነጋዴዎች በጭነት መኪናዎች ቁሳቁሶቻቸውን ጭነው በሕጋዊ ሽፋን የሚያልፉበት ነው። ለዚህኛው ዘዴ ከኬላ ጥበቃ ሠራተኞች ጋር መመሳጠር ያስፈልጋል። የገንዘብ ጥቅም ያገኙት ጥበቃዎች ያዩትን እንዳላዩ በማለፍ ነጋዴዎችን ይተባበራሉ።

የጭነት ተሽከርካሪውን ሕጋዊ ባልሆነ፣ ባልተፈቀደ መንገድ ማስጓዝ ሌላኛው አደገኛ መንገድ ነው። ከጠባቂዎች ዐይን እና ጆሮ ተሰውሮ ለማለፍ የሚደረገው ጥረት ላልታሰበ አደጋ የሚዳርግበት ጊዜ ብዙ ቢሆንም አሁንም ያንን መንገድ የሚከተሉ ደፋሮች አሉ። በዚህ መንገድ የተጓጓዘው ቁሳቁስ ኬላ ከመድረሱ አስቀድሞ ለሞተረኞች ይከፋፈላል። ከግዙፉ ጭነት ጥቂቱን የሚቆነጥረው ሞተረኛ ባልተፈቀደ አቋራጭ ኬላውን ያሻገረውን ዕቃ ከኬላው ወዲህ ማዶ ጠብቆ ለባለቤቱ ያስረክባል።

የተለያዩ የፋሽን አልባሳት መሸጫ ሱቆችም ተጫርተው ይገዙና መልሰው ለገበያ ያቀርባቸዋል፡፡ ሱቆቹ ለችርቻሮ ገበያ የሚያቀርቧቸውን አልባሳት፣ ጫማዎች፣ ቦርሳዎች እንደ ቴሌግራም ባሉ ለማኅበራዊ ትስስር ገጾች ያስተዋውቋቸዋል። ክፍያውን በባንክ በመፈጸም የመረጡት አልባሳት ወይም ጫማ በሌላ ገዢ እንዳይወሰድ ማድረግ እየተለመደ መጥቷል።

የአገር ውስጥ አምራቾች በምርት ግብዓት እጥረት፣ በዘመናዊ የማምረቻ ማሽነሪዎች እና ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ አመራረት ዘዴ ስለሚጠቀሙ በቂ ምርት አለማምረታቸው ነጋዴዎች ሕገ ወጡን መንገድ እንዲመርጡ እንዳደረጋቸው ሲናገሩ ይሰማል፡፡

የአገሪቱ ኢንዱስትሪዎች ከአቅም በታች እያመረቱ መሆኑ ቢታመንም በዚህ ረገድ ጠንካራ ሥራ ለመሥራት ጠንካራ ፖሊሲ ያስፈልጋል የሚሉ ባለሙያዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ በመሆኑም መንግሥት በበቂ ሁኔታ የተጠና እና ችግር ፈቺ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ የአገሪቱን ኢንዱስትሪዎች ከመሞት መታደግ እንዳለት የቴክስታይል ምህንድስና ባለሞያዎች እምነት አላቸው፡፡

ተወዳዳሪ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር በመንግሥት በኩል የቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስ፣ የሎጀስቲክ ወቅታዊ መረጃን ለአምራቾች በማቅረብ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፣ እንዲሁም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መሰጠትም አንዱ የመፍትሄ አቅጣጫ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ሕዝባቸውን የማያውቁ ሪልስቴቶች

ደበበ ካሳ

በአገራችን ውስጥ ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት ችግር መኖሩ ይታወቃል፡፡ ችግሩ ለዘመናት የተከማቸ መሆኑንም በተለያዩ አካላት በተለያዩ ጊዜያት የተከናወኑ ጥናቶች ያለመክታሉ፡፡ በተለይም በከተሞች አካባቢ የሚታየው የመኖሪያ ቤቶች ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱና የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ዝቅተኛ መሆኑ፣ በመላው የኢትዮጵያ ከተሞች የ1.2 ሚሊዮን የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ጉድለት መኖሩን ጉዳዩን በበላይነት የሚያስተዳድረው መንግሥታዊ አካል የከተማና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መረጃ ያመላክታል፡፡

ችግሩን ለመፍታት መንግሥት በየጊዜው የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም በርካታ ጥረቶችን ማድረጉ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ችግሩ እየባሰበት መጣ እንጂ አልተሻሻለም፡፡ እንዲያውም በአገሪቱ ውስጥ እየጨመረ ከመጣው ኑሮ ውድነት ጋር ተዳምሮ ችግሩ አሁን ላይ የከፋ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በተለይ በመዲናችን አዲስ አበባ የመኖሪያ ቤት ጉዳይ እጅጉን አሳሳቢ ሆኗል፡፡ የመኖሪያ ቤት ችግር ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው የሚወጡ የነገ አገር ተረካቢ ወጣቶችንም ጭምር የሚፈታተን የዘመኑ ተግዳሮት እየሆነ መጥቷል፡፡ በወጣትነታቸው ቤተሰብ ላይ ሸክም የሆኑ ዜጎች እየበዙ ነው፡፡ ፍቅረኛሞች በመኖሪያ ቤት ዕጦት ምክንያት ትዳር መመሥረት ተስኗቸዋል፡፡ ብዙዎቹ የመንግሥትና የግል ድርጅት ሠራተኞች ከወር ደመወዛቸው ከግማሽ የሚበልጠውን ለመኖሪያ ቤት ኪራይ ለመክፈል ይገደዳሉ፡፡

በሌላ በኩል መገናኛ ብዙኃኖቻችን በቤት ሽያጭ ማስታወቂያዎች ተጨናንቀዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ እንደአሸን ከፈሉ ኤፍ.ኤም ሬዲዮዎችና የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ ጥቂት የማይባሉ የግል የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን የአየር ሰዓት የተቆጣጠሩት እነዚሁ የቤት ሽያጭ ማስታወቂያዎች መሆናቸውን ማንም የሚታዘበው ሃቅ ነው፡፡ እንደዘወትር ጸሎት በየዕለቱ፣ እንደሰበር ዜና በየሰዓቱ፤ በዜና እወጃ ሰዓት ደግሞ በየደቂቃው የሚነበቡልንና የሚነበነቡልን እነዚሁ የማይመለከቱን የቅንጡ ቪላዎችና አፓርትመንቶች የሽያጭ ማስታወቂያዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ማስታወቂያዎች የሚነግሩን ቤቶች በስፋት እየተገነቡ እንደሚገኙ ነው፡፡ በእርግጥ በስፋት እየተገነቡ «እንድንገዛቸው» ሳምንቱን ሙሉ በየቀኑ ያለእረፍት 24/7 በሚዲያዎቻችን እየተዋወቁልንና ለገበያ እየቀረቡልን ያሉት «ቤቶች» አይደሉም፡፡ የተንጣለለ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያ ያላቸው፣ ሃያ አራት ሰዓት ንቁ ሆኖ የሚጠብቅ የደህንነት ካሜራ የተገጠመላቸው፣ መዋኛ ገንዳ፣ መሮጫ ትራክ ጭምር ያለው የስፖርት ሜዳ፣ መንፈስን የሚያድስ ውብ የመዝናኛና የመናፈሻ ስፍራ ያላቸው «ቤቶች» ናቸው፡፡

ምን ይሄ ብቻ በአራት አቅጣጫ መውጫና መግቢያ በር፣ አዲስ አበባን በሁሉም አቅጣጫ ለማየት የሚያስችል ሰገነት፣ የራሳቸው የከርሰ ምድር ውሃ ያላቸው...እንኳንስ ልንኖርበት ምን እንደሆነ እንኳን የማናውቀው ሌላም ሌላም ነገር ሁሉ ያላቸው እጅግ ዘመናዊ ውብና ቅንጡ ቪላዎችና አፓርትመንቶች ናቸው ማንም ሳይቀድመን በፍጥነት «ገዝተን» «የቤት ባለቤት» እንድንሆን እየተዋወቁልን የሚገኙት፡፡ በእውነቱ ነገሩ እጅጉን ግራ የሚያጋባና ሲበዛ የሚያስተዛዝብ ነው፡፡

እንደው ማን ይሙት፣ በመኖሪያ ቤት እጦት ችግር እየተሰቃየ ያለው ማን ነው? እንዲህ በብዛት ቤቶች መገንባትና መቅረብ የነበረባቸውስ ለማን ነው? እንዴት ያሉ ቤቶችስ ናቸው መገንባት የነበረባቸው? እሺ ይሁን ደግሞ፣ «ቤቶች» በመሆናቸው ብንስማማና መገንባትም መብት ነው ብለን ብንቀበል እንኳን እንዲህ ዓይነቶቹን እጅግ ውብና ቅንጡ ቪላዎችንና አፓርታማዎችን የሚፈልጉ «የመኖሪያ ቤት ችግር ያለባቸው» ዜጎቻችን ቁጥር ምን ያህል ነው? እርግጠኛ ነኝ፤ ጥናት ቢጠና እንዲህ ዓይነት ቤቶችን የሚፈልጉ «ቤት አልባ» ዜጎቻችን ቁጥር አንድ በመቶ እንኳን የሚሆን አይመስለኝም፡፡

ቀሪው 99 ነጥብ 9 የሚሆነው ሰፊው ሕዝብማ ከተማን ከላይ ወደታች የሚያሳይ ሰማይ ጠቀስ ሰገነት ያለው እጅግ ውብና ቅንጡ ቪላና አፓርታማ ሳይሆን መኖሪያ ቤት ነው የሚፈልገው፡፡ ሃያ አራት ሰዓት ንቁ ሆኖ የሚጠብቅ የደህንነት ካሜራ ሳይሆን ድህነቱን የሚያቃልልበትና ውሎ የሚገባበት፤ ከገቢው እኩል ኪራይ እየከፈለ ሳይሆን ግብር እየከፈለ፣ እንደጋርዮሽ ዘመን ሰው ከቦታ ቦታ እየተንከራተተ ሳይሆን ዘላቂ የሕሊና ሰላምና እረፍት አግኝቶ ተረጋግቶ የሚኖርበት መኖሪያ ቤት ነው የሚፈልገው፡፡ እናም ሁኔታው ብዙኃኑን ለቅሬታና ለብሶት እየዳረገ የሚገኝና ፍጹም ተገቢ ያልሆነ አካሄድ ነውና የሚመለከተው አካል ተገቢውን መፍትሔ ሊፈልግለት ይገባል፡፡

በእርግጥ ከላይ በመግቢያችን እንደጠቆምነው ይህንን አንገብጋቢ የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት መንግሥት አያሌ ጥረቶችን አድርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መንግሥት 750 ሺህ ቤት የመገንባት ዕቅድ አስቀምጦ ተንቀሳቀሷል፡፡ በሁለት ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራቱንም መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የመጀመሪያው ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላለው የኅብረተሰብ ክፍል በየዓመቱ 50 ሺህ ኮንዶሚኒየም ቤቶች በ1.5 ቢሊዮን ብር ወጪ መገንባት፣ ሁለተኛው ደግሞ ከፍተኛና መካከለኛ ገቢ ላለው የኅብረተሰብ ክፍል የሚሆኑ የሪል ስቴት ቤቶችን በግሉ ዘርፍ እንዲገነባ ዕድሉን ማመቻቸት የሚሉ ናቸው፡፡

የቅርብ ጊዜውን ስንመለከት ደግሞ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፤ «ተደራሽ የቤት ልማት» በሚለው የዕቅዱ ንዑስ ክፍል በከተማና በገጠር ማዕከላት ተደራሽና ደረጃውን የጠበቀ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ማሳደግ እንደ ዓላማ፤ በከተሞች የቤት አቅርቦት መጠን አሁን ካለበት 64 በመቶ ወደ 80 በመቶ እንዲያድግ 4,410,400 ቤቶች እንዲገነቡ ማድረግን እንደ ግብ አድርጎ በማስቀመጥ ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ አመላክቷል፡፡ የሚገነቡት ቤቶችም በመንግሥት አስተባባሪነት 20 በመቶ፣ በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት 35 በመቶ፣ በግለሰቦች 15 በመቶ፣ በሪል ስቴት ገንቢ ባለሀብቶች 10 በመቶ፣ በመንግሥትና በግል ባለሀብት አጋርነት 15 በመቶ እና በሽርክና (ጆይንት ቬንቸር) 5 በመቶ መሆናቸውንም በዝርዝር አቅዷል፡፡

ይሁን እንጂ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው በስፋት እየተገነቡ ያሉት ቤቶች «መካከለኛ ገቢ ላለው የኅብረተሰብ ክፍል የሚሆኑ የሪል ስቴት ቤቶችን በግሉ ዘርፍ እንዲገነባ ዕድሉን ማመቻቸት» በሚለው ሥር ያሉት ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ በራሱ በመንግሥት መረጃ መሠረት አስር በመቶ ብቻ ናቸው፡፡ አሁን ላይ ከምናየው ተነስተን ነገሩን ስንመረምር ግን እየተገነቡ ያሉት እጅግ ውብና ቅንጡ ቪላዎችና አፓርታማዎች አስር በመቶ ሳይሆን አስር ጊዜ አስር በመቶ ነው የሚመስለው፡፡ በዚህ ላይ በዚህ መንገድ በሪል ስቴቶች አማካኝነት እየተገነቡ ያሉ ቤቶች ዋጋቸው እንኳንስ መካከለኛ ገቢ ላለው የኅብረተሰብ ክፍል ለባለከፍተኛ ገቢዎቹም የሚቻል አይመስልም፡፡ ይህንኑ መሰለኛችን እነሆ በማስረጃ እናስደግፍና እውነት መሆኑን እናረጋግጥላችሁ፡-

«የቤት አቅርቦትና የዜጎች የመግዛት አቅም አዲስ አበባ ውስጥ በሪል ስቴቶች በሚገነቡ ቤቶች» በሚል ርዕስ በ2009 የተደረገ ጥናት እንደሚያመላክተው በመዲናዋ በቤት ግንባታ ላይ የተሰማሩ 125 የተመዘገቡ ሪል ስቴቶች ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ መካከለኛ ገቢ ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል ማዕከል አድርገው ቤት የሚገነቡት 16 ነጥብ 7 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው፡፡ 83 ነጥብ 3 የሚሆኑት ሪል ስቴቶች የሚገነቧቸው ቤቶች ዋጋቸው የመግዛት አቅም አለው ተብሎ ለሚታሰበው መካከለኛ ገቢ ላለው ኅብረተሰብ እንኳን የሚቀመስ አይደለም፤ ባለ ከፍተኛ ገቢዎቹን ወይንም እጅግ ውድ የሚባል ዋጋም ቢሆን መክፈል የሚችሉትን የናጠጡ ከበርቴዎችን ብቻ ነው፡፡ በስፋት እየተገነቡ ያሉትና እንድንገዛቸው በማይመለከተን ማስታወቂያ እያጥለቀለቁን ያሉት ግን እኒሁ ቤቶች «ናቸው»፡፡

# ለትውልድ የተገለጡ ልቦች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)**

አገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ልበ ቀናዎችን ትፈልጋለች:: ልብ ስላችሁ ደረታችን ስር ያለውን ማለቴ አይደለም ቀናውን የሚያይ ልብ እንጂ:: ልብ የርህራሄ ምልክት ነው:: ልብ የእውነትና የፍቅር ማደሪያ ነው:: ልብ ከአእምሮ የላቀ የፍቅር ስፍራ ነው:: ልብ በፍቅር፣ አእምሮ በሀሳብ እስካልተሞሉ ድረስ አገር ታታሪ ነፍሶች አይበቅልባትም:: አእምሮና ልብ ድርና ማግ ናቸው:: ልብ ማፍቀር ሲሳነው አእምሮ ማሰብ ያቆማል:: ልብ ጥላቻን ሲማር አእምሮ ክፉ ሀሳብን ይማራል:: እኛ የልብና የአእምሯችን ጥንስሶች ነን::

በነዚህ ሁለት ኃይሎች ተሠርተን ነው ሰው የሆንነው:: ይህን ሰውነታቸውን ለአገራቸው ገብረው ታረክ የጻፉ አያሌ ነፍሶችም በዙሪያችን አሉ:: በዚያው ልክ ደግሞ ከእውነትና ከሰውነት ሸሽተው ልባቸውን የክፋት ማደሪያ ያደረጉም አይጠፉም:: እኛስ ምን ዓይነት ነን? በልባችንና በአእምሯችን ውስጥ ምንድነው ያለው? አገራችን የምትፈልገን ነን ወይስ ሌላ ነን? እኒህን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ወቅቱ አሁን እንደሆነ ይሰማኛል።

በአእምሯችን ክፉ ሀሳብ፣ እጆቻችን ነውር የሚሠሩ፣ ልባችን ክፉ ምኞት፤ እግሮቻችን ወደ ክፉ የሚሮጡ፣ አንደበቶቻችን መጥፎ የሚናገሩ፣ ከሆነ ገና ተሠርተን አላለቅንም:: ገና ወደ ሰውነታችን አልተመለስንም:: አይደለም ለአገራችን ለራሳችንም ያልበቃን የዋህን ነን ። ፈርሰን መሠራት ይኖርብናል::

አገር የዜጎች እጅ ሥራ ናት:: አንድ ጥበበኛ ሰዐሊ እውቀቱንና ምናቡን ተጠቅሞ አንድ ውብ ስዕል እንደሚሠራ ሁሉ አገርን ውብ አድርገው የሚሠሩ ዜጎች፤ እኛ ነን:: አገራችንን እንደምንፈልገው አድርገን ለመሥራት መዶሻውም ሚስማሩም እኛው ጋ ነው:: መዶሻና ሚሰማራችን ሀሳብና እውቀት፣ ፍቅርና አንድነት ናቸው:: መዶሻና ሚስማራችን ይቅርታና ወንድማማችነት ናቸው:: መዶሻና ሚስማራችን ትህትናና እግዚአብሔርን መፍራት ናቸው::

ብዙ ዓይነት መዶሻና ሚስማር እያለን በኅብረት የተሻለ ቤት መሥራት ሳናውቅበት ቀርተናል:: አሁን ግን ጊዜው ቤት የመሥራት ነው:: አሁን ጊዜው ለሁላችን የምትበቃን ኢትዮጵያን አምጦ የመውለጃ ነው:: አሁን ጊዜው የመተቃቀፍ ነው:: በመነቋቆር የብቻ ቤት የምንሠራበት ሳይሆን በመነጋገር የጋራ ቤት የምናበጅበት ነው::

ለትውልድ የሚተላለፉ አእምሮና ልብ ያስፈልጉናል፡ እውነት የተጻፈባቸው፣ ፍትህ የደመቀባቸው የሰውነት ብራናዎች ያስፈልጉናል:: ፍቅርን የሚሰብኩ፣ መቻቻልን የሚዘምሩ አንደበቶች ያስፈልጉናል:: ነውርን የሚጸየፉ፣ ጨዋነትን የሚናገሩ አንደበቶች ግድ ይሉናል::

በደልን የማይቆጥሩ ይቅር የሚሉ ልቦች ያሹናል:: በእውቀት የሚራመድ፣ በምክንያት ከፍ የሚል አእምሮ ያስፈልገናል:: ይቅር ለእግዜርን የሚያውቁ አስታራቂ ሽማግሌዎች ማብዛት ይጠበቅብናል::

አገር በአእምሮ ተጠንስሳ፣ በልብ የምትፈጠር፣ በተግባር የምትጸና የሁላችን የቤት ሥራ እንደመሆኗ፤ በዚህ መነሻና መድረሻ ውስጥ አገርን ከነሙሉ ክብሯና፣ ነፃነቷ ጋር የሚፈጥሩልን በልባችንና በአእምሯችን ውስጥ ያስቀመጥናቸው በጎ መንፈሶች ያስፈልጉናል:: በጎ መንፈስ ሁልጊዜም የበጎ አእምሮና ልብ ነጸብራቅ ነው::

ሰው ለራሱ በጎ ሲሆን በዙሪያው ላሉ ሁሉ በጎ ይሆናል:: በጎ መሆን ማለት ራስን ወዶ ሌሎችን መውደድ ማለት ነው:: በጎ መሆን ማለት ራስን አፍቅሮ ሌሎችን ማፍቀር ማለት ነው:: በጎ መሆን ማለት ራስን አክብሮ ሌሎችን ማክበር ማለት ነው:: በዚህ ሁሉ የጋራ በጎነት ውስጥ አገር ነው የምንፈጥረው:: ትውልድ ነው የምንቀርጸው::

ልብ እንዲወድ፣ እንዲምር፣ ቸርነትን እንዲያደርግ የተፈጠረ ነው:: ልብ ለሌሎች ደስታ እንዲሆን፣ ለሌሎች በረከት እንዲሆን የተሠራ ነው:: በዚያው ልክ ደግሞ በጎ ማሰብና በጎ ማድረግ ተስኗቸው ራሳቸውን በመርዘኛ ሀሳብ መርዘው ሰውነታቸውን አውሬ ያደረጉ አሉ:: ሰው ፍቅርን ካልተማረ በራሱ ላይም በሌሎች ላይም አውሬ መሆን ይችላል::

ሰው አውሬ ሲሆን ጥፋቱ ብዙ ነው:: ሰው አውሬ ሲሆን ፍቅር ምን እንደሆነ አያውቅም:: ኃይሉ ጥላቻና በቀል ይሆናል:: ማሸነፊያው እልህና ማንአለብኝነት ይሆናል:: ሰው አውሬ ሲሆን ሌሎችን ለማሸነፍ የሚሮጠው በኃይልና በጉልበቱ ይሆናል:: ሰው አውሬ ሲሆን እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ ውስጥ ይቆማል:: እኛ ምርጫችንን ነን:: እኛ ራሳችንን ያደረግነውን ነን:: በሀሳባችንና በድርጊታችን አውሬም ሰውም መሆን ይቻለናል::

> **ከ**መቼውም ጊዜ በላይ ልባችንን የምንገልጥበት ጊዜ ላይ ነን:: ከገንዘባችን፣ ከእውቀታችን፣ ከጊዜአችን ለአገራችን የምናዋጣበት ጊዜ ላይ ነን:: ያለንን ሁሉ እየሰጠን አገራችንን ወደ ፊት የምናራምድበት ሰሞን ላይ ነን:: አላማ ይዞ እንደ ተሰለፈ ሰራዊት በአንድ ልብ የምንቆምበት የፈተና ጊዜ ላይ ነን:: በእኛ የአንድነት ግፊት ከፊታችን ያለውን ዳገት ሰላምን ምርኩዝ አድርገን እንሻገር

አሁን አገራችንን እያሰቃየናት ያለው በልባችን ውስጥ ያጨቅናቸው ክፉ ሀሳቦች ናቸው ነው:: በመልካም ልብ ፍቅርን አውርተን፣ ፍቅርን ተናግረን ሰው መሆን ለምን ተሳነን? በክፉ ሀሳባችን ራሳችንን አውሬ ለማድረግ ሳይሆን ለማፍቀር ነው የተፈጠርነው:: በዙሪያችን ያሉትን ለማቀፍ ነው ሰው የሆንነው:: በፍቅር ጽዋ እንሙላ፤ በእውነት ጸጋ እንትረፍረፍ::

የአገር ስቃይ የትውልድ ስቃይ ነው:: የአገር ስቃይ የዜጎች ስቃይ ነው:: አገራችን ኢትዮጵያ ለነፍሳቸው ኩነኔን፣ ለልባቸው ሀጢዐትን፣ ለሰውነታቸው አረመኔነትን ባስተማሩ ነፍሶች ብዙ ዋጋ ከፍላለች። ለእኛ ግን ፍቅራችን ያለው መቻቻል ውስጥ ነው:: ደም ባልነኩ፣ ጥላቻ ባላስነወራቸው ጸዐዳ ጣቶቻችን ልቦቻችን ላይ ወንድማማችነትን እንጻፍ::

ይሄ የታሪክ ድርሳን በልጆቻችን እየተገለጠ ሲነበብ የት ቦታ ምን እየሠራን እንደነበር አስረጂ ይሆናል:: ምን ያክል ጥያቄ፣ ምንም ያክል ቅሬታ ቢኖርብንም በፍቅር መድረክ ላይ በመልካም አንደበት መነጋገር እንችላለን:: ልቦቻችንን ለፍቅር እንግለጥ:: ለአንድነት እንክፈት::

## የተገለጡ ልቦች....

የተገለጡ ልቦች..ክፉ ሀሳቦችን፣ ክፉ ምኞቶችን፣ ክፉ ተግባራትን ማንበርከኪያ ጥበቦች ናቸው:: የተገለጡ ልቦች ክፉ ሰውነትን፣ እኩይ ስብዕናዎችን መርቻ መንገዶች ናቸው:: አገራችን ከትናንት እስከዛሬ በዚህ ግልጽ ማንነት ጠላቶቿን ስታንበረክክ ኖራለች፤ አሁንም በነዚሁ መንገዶች ታሸንፋለች::

ነፍሶች ስውር ሀቃቸውን የሚገልጡት በአገር ነው፣ ልብ የነፃነት ድሉን የሚቀዳጀው ከወገኑ አጠገብ ሲቆም ነው:: ያለ አገርና ሕዝብ ሰውነት ምንም ነው:: ይሄ ሊገባን ይገባል:: የልብ መገለጥ ለአገር ጥሪ፣ ለወገን መከራ ምላሽ መስጠት ነው::

ልብ ስለ አገር ሲያዜም ደስ፤ ቀልብ በእናት አገር ላይ ሲያርፍ ደስ ይላል:: የሁሉም የሰው ልጅ የነፍሱ ማረፊያ አገርና ሕዝብ ነው:: በበጎ ሀሳባችን ተገልጠን ሰላም ላጣችው አገራችን ሰላም እንሁናት:: የተገለጡ ልቦች ነውር አያውቁም፣ ለወገን የተገለጡ ልቦች ፍትህ አያጓድሉም::

ለኢትዮጵያ መገለጥ ስቃይዋን መሰቃየት፣ ችግሯን መቸገር ነው:: ለኢትዮጵያ መሰቃየት በደስታዋ መደሰት፣ በትንሳኤዋ እልልታ ማሰማት ነው:: ዳር ቆሞ ማጨብጨብ፣ ወደነፈሰበት መንፈስ ለኢትዮጵያ መገለጥ አይደለም:: ለአገር በመኖር ውስጥ ያለውን ክብር፣ ለወገን በመቆም ውስጥ ያለውን ፍሰሀ ልባችንን ገልጠን እንመልከት:: በምንም የማይገኙ ትላልቅ ደስታዎች በዚህ እውነታ ውስጥ የተደበቁ ናቸው::

በምንም የማይተኩ የነፍስ ፈንጠዝያዎች በልብ መገለጥ ውስጥ የተቀመጡ ናቸው:: የአገር መገለጥ የትውልድ መገለጥ ነው:: የአገር መነሳት የእኔና የእናንተ ብርሃናዊ ነገ ነው:: ይሄ ሁሉ እንዲሆን ግን ከሁሉ በፊት እኛ ስለአገራችን ልቦቻችንን መግለጥ ይኖርብናል:: ስለኢትዮጵያ ክፉ አላይም፣ ክፉ አልሰማም፣ ክፉም አልናገርም ስንል ልባችንን በክፉዎች ላይ ማጽናት ይኖርብናል::

አገር ስትታመም ስትስቃ የሚታመሙትና የሚሰቃዩት ሕዝቦቿ ናቸው:: እኛ የአገር ደስታ ማረፊያዎች ነን:: መገፋፋት ያበላሸውን ኢትዮጵያዊነት ማደስ ይኖርብናል:: ጥላቻ የመረዘውን ታሪካችንን ማስተው:: እኛ ለአገራችን ስር ግንድና ቅርንጫፎች ነን:: አገራችንን ዋርካ የምናደርጋት እኛ ነን::

የምዕራባውያኑን የተንኮል ሩጫ ጥሰን፣ የብሔር ካባ የለበሰ ፖለቲካችንን አስተካክለን፣ ወንድማማችነትን አግንነን፣ በተባበረ ክንድ የጋራ ቤታችንን መሥራት ይኖርብናል:: ስለ አገራችን ልባችንን እንግለጥና በአገራችን በኩል ለራሳችን እንኑር:: ለአገር መልፋት ለራስ መልፋት ነውና:: ለአገር መድከም ለራስ መድከም ነውና::

ለአገራችን የምንሰስተው አንዳች ነገር ሊኖር አይገባም:: ራስን ለአገር እንደመስጠት ያለ ስጦታ የለም:: አገር አርነት የምትወጣው ራሳችንን ስንሰጥ ነው:: ራሳችንን ሰስተን የምንፈጥረው አገርና ሕዝብ የለም:: በሀሳብና በምክክር እስካልተወጣነው ድረስ የአገራችን አሁናዊ ችግር ዳር ቆመን የምንወጣው አይደለም:: ልብን ለአገር መግለጥ ያስፈልጋል::

ራሳችንን ለአገራችን እንስጥ ...ራስን ለአገር መስጠት ራስን ከባዕድ አስተሳሰብ ነፃ ማውጣት ነው:: አሁናዊ ችግሮቻችን እልባት የሚያገኙት ራሳችንን ለውይይትና ለአንድነት ስንገልጥ ነው:: የተገለጠ ልብ የአንድነት ክንድ ነው:: የተገለጠ ልብ አገሬን ለማንም አሳልፌ አልሰጥም የሚል ወኔ የነቀነቀው ነው:: ልባችንን በመግለጥ መርህ ወደፊት ልንሄድ ይገባል::

ከመቼውም ጊዜ በላይ ልባችንን የምንገልጥበት ጊዜ ላይ ነን:: ከገንዘባችን፣ ከእውቀታችን፣ ከጊዜአችን ለአገራችን የምናዋጣበት ጊዜ ላይ ነን:: ያለንን ሁሉ እየሰጠን አገራችንን ወደ ፊት የምናራምድበት ሰሞን ላይ ነን:: አላማ ይዞ እንደ ተሰለፈ ሰራዊት በአንድ ልብ የምንቆምበት የፈተና ጊዜ ላይ ነን:: በእኛ የአንድነት ግፊት ከፊታችን ያለውን ዳገት ሰላምን ምርኩዝ አድርገን እንሻገር::

ጦርና ጎራዴ ሳንመዝ በተከፈተ ልብ ብቻ ወደረኞቻችንን መርታት እንችላለን:: አገራችንን የምናፈቅር ከሆነ ልባችንን እንክፈትላት:: የመለያየት ጉድፋችንን እያጸዳን ከሰላም ውጪ ምንም አማራጭ እንዳይኖረን ሆነን እንኑር:: ሕዝባችን በሚፈልገን ቦታ ላይ ሁሉ እንገኝ:: ኢትዮጵያ በምትፈልገን ስፍራ ላይ ሁሉ መቆም ግዴታችን ነው:: በዚህ የአብሮነት መንፈስ ውስጥ የምትፈጠረውን ኢትዮጵያ ሁላችንም እንናፍቅ::

ትላልቅ አገራት በትላልቅ ሀሳብ የተፈጠሩ ናቸው:: ዘመናዊና ስልጡን ሕዝቦች በዘመናዊና ተራማጅ አስተሳሰብ የተፈጠሩ ናቸው:: እኚህ ሁሉ ስፍራቸው ክፍት አእምሮና ልብ ነው:: ክፍት አእምሮና ልብ የዘመናዊነት መፈጠሪያ ቦታ ነው::

ሰው ሌሎችን ለመፍጠር ከመሞከሩ በፊት መጀመሪያ ራሱን በበጎ ሀሳብ መፍጠር አለበት:: ራሳችንን በበጎ ሀሳብ መፍጠር ከቻልን በጎ ቤተሰብ፣ በጎ ጓደኛ መፍጠር አያቅተንም:: በጎ ቤተሰብ ደግሞ የበጎ ማህበረሰብ መነሻ ነው:: በጎ ማህበረሰብ ደግሞ አገር ነው:: በአሁኑ ሰዓት አገራችን የሚያስፈልጋት በጎ ሀሳብ ብቻ ነው:: የበጎ ሀሳብ መብቀያ ማሳ ደግሞ በጎ ልብ ነው:: በበጎ ልብ አገራችንን እናብቀል ! አበቃሁ::

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱን ግብ የማሳካት ርብርብ

ስምስም መንግሥቱ



የኢትዮጵያ ግብርና የዝናብ ጥገኛ ሆኖ ነው የኖረው:: ይህ ዓይነቱ የግብርና ልማት ግብርናው የሚጠበቅበትን እንዲወጣ እንደማያስችለው እየተጠቀሰ ሲተች ኖሯል:: በተለይ ድርቅ በመጣ ቁጥር በግብርና ላይ የሚደርሰው ጥፋት ችግሩን ይበልጥ አሳሳቢ አድርጎትም ኖሯል:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ በየጊዜው እየጨመረ ያለውን የግብርና ምርቶች ፍላጎት መሟላት አይቻልም የሚሉ ሀሳቦችም ሲንሸራሸሩ ቆይተዋል:: መንግሥት የግብርናው ምርትና ምርታማነት እየጨመረ መምጣቱን እያደነቀ፣ ከግብርናው ከሚጠበቀው አኳያ ምርትና ምርታማነቱ ብዙም እንዳልሆነም ሁሌም ሲያስገነዝብ እንደነበር ይታወቃል::

በተለይ ደግሞ የውሃ ማማ በመባል ለምትታወቀው ኢትዮጵያ ይህ ሁኔታ በእጅጉ የሚያም ስለመሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎችም መንግሥትም በቁጭት ሲያነሱት ኖረዋል:: ክረምት ከበጋ የሚፈሱና ለልማት ሊውሉ የሚችሉ በርካታ ወንዞችና ጅረቶች ያሏት አገር በመስኖ ልማት ስሟ ሳይጠራ ኖራለች::

ባለፉት ጥቂት አመታት ግን በመንግሥት ቁርጠኝነት የተሞላበት አሠራር እነዚህ ሁኔታዎች እየተቀየሩ መጥተዋል:: እንደ አገር ኢኮኖሚን ሊያሳድጉ የሚችሉ ዘርፎችን በመምረጥ መንግሥት ትኩረት አድርጎ እየሠራባቸው ካሉት መካከል የግብርናው ዘርፍ አንዱ ሆኗል::

በዚህም ቅድሚያ ሰጥቶ እየተሠራበት ያለው በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ነው:: እንደ አገርም ከውጭ በግዥ የሚገባን ስንዴ ለማስቀረት በአገር ውስጥ ስንዴ በብዛት ማምረት የሚል አቋም ተይዞ ወደ ሥራ ከተገባ ጥቂት አመታት ተቆጥረዋል::

ይህን ተከትሎም የስምጥ ሸለቆ አካባቢዎችን መሠረት በማድረግ በአገር ደረጃ ላለፉት ሦስት አመታት በተከናወነው የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ውጤት እየተገኘ ነው:: ለእዚህም በተለይ ባለፈው አመት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተገኘው ውጤትና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተለያየ ጊዜ ተዘዋውረው የጎበኙዋቸው በሰፊ ማሳዎች ላይ የተካሄዱ የስንዴ ልማት ሥራዎች ሁነኛ ማሳያዎች ናቸው::

በመስኖ ስንዴ ልማቱም ባለፈው አመት ከ600 ሺ ሄክታር በላይ በዘር በመሸፈን 26 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ማግኘት ተችሏል:: ዘንድሮ ደግሞ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ በማልማት 52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል:: አንዳንድ አካባቢዎች የመኸር አዝመራ ሰብስበው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱን ጀምረዋል::

አሁን በስንዴ ልማት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ብቻ አይደለም የሚሠራው:: ያን ማድረግ ተችሏል፤ አገሪቱ በስንዴ ላይ በመኸርም በበጋ መስኖም ባከናወነችው ተግባር እንደ ቀደሙት ጊዜያት ባለፈው በጀት አመት ስንዴ ከውጭ አላስገባችም:: ዘንድሮ ደግሞ የአገር ውስጥ ፍላጎትን ከማሟላት ባሻገር ለውጭ ገበያ ስንዴ ለማቅረብ አቅዳ እየሠራች ትገኛለች::

በበጋ መስኖ በተከናወነው ተግባር የተገኘው ምርትም ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በሚያስችል ደረጃ ላይ መድረሱም በመንግሥት ይፋ ሆኗል:: በበጋ የመስኖ ስንዴ ልማት ዙሪያ በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት ዳይሬክተር ኢሳይያስ ለማ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል::

### የሦስት አመታት የበጋ ስንዴ ልማት እንቅስቃሴዎች

እንደ አቶ ኢሳይያስ ገለጻ፤ የበጋ መስኖ የስንዴ ልማት ከተጀመረ ወደ አራተኛ አመት ተሸጋግሯል:: ልማቱ በቆላማ ስምጥሸለቆ አካባቢዎች የተጀመረ ሲሆን፣ በዋናነትም አፋር፣ ከፊል ኦሮሚያ፣ሶማሌ እና ደቡብ ክልሎች ውስጥ ነው:: በመጀመሪያው ዙር በተከናወኑት ሥራዎችም በአፋርና ከፊል ኦሮሚያ ላይ ጥሩ ውጤት ተገኝቷል:: ከአገራዊ የልማት መርሃ ግብሩ (ፕሮግራም) አንጻር አፈጻፀማቸው በንጽጽር ሲቀርብ ልዩነት ይኑረው እንጂ ልማቱ በተከናወነበት በሶማሌ ክልልም የተገኘው ውጤት አበረታች ነው::

በመጀመሪያው ዙር በቆላማው አካባቢ የተከናወነውን የበጋ መስኖ የስንዴ ልማት መሠረት በማድረግ በሁለተኛው ዙር የልማት እቅድ አማራጮች ታይተዋል:: ውሃ ገብ ሆነው ነገር ግን በበጋ የማያመርቱ ደጋና ወይና ደጋ አካባቢዎችን በማካተት የልማት ፕሮግራሙን የማስፋት ሥራ ነው የተከናወነው:: በዚሁ መሠረትም አማራ፣ ደቡብ፣ ኦሮሚያና አፋር ክልሎችን ያካተተ ልማት ማከናወን ተችሏል::

በደቡብ ክልል በመጀመሪያው ዙር ደቡብ ኦሞ ላይ ነበር የተጀመረው:: በሁለተኛው ማስፋፊያ ግን መካከለኛው የደቡብ አካባቢዎችን በማካተት ሥራው ተከናውኗል:: እንደ አጠቃላይ የልማቱ ሥራ ሲገመገም በተለይም በማስፋፋቱ ሂደት ከክልሎቹ በልማቱ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበው ኦሮሚያ ክልል ነው:: እንደ አገር በመስኖ ከለማው ከ450ሺ ሄክታር መሬት እንዲሁም በበልግ ወቅት ወደ 255ሺ ሄክታር መሬት ከለማው ውስጥ ኦሮሚያ ከፍተኛውን የልማት ድርሻ ይዟል::

በአጠቃላይ በበልግና በመስኖ እንደ አገር ከለማው ወደ 625ሺ ሄክታር መሬት ኦሮሚያ ክልል ወደ አምስት መቶ ሺ ሄክታር በማልማት ከአጠቃላዩ ብልጫውን ይዟል:: በመቀጠል አማራ ሲሆን፣የተቀሩት በቅደም ተከተል ላይ ይገኛሉ::

በዚህ መልኩ የሦስቱ አመታት የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ነበሩ::በተያዘው በጀት አመት ደግሞ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር ለማልማት በእቅድ የተያዘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ኦሮሚያ አንድ ሚሊዮን ሄክታር፣ አማራ 250ሺ ሄክታር፣ ቀሪውን ሌሎች ክልሎች የሚጠቀሙ ይሆናል:: ይህም የሆነው ክልሎቹ ባላቸው ስፋት፣ የመስኖ አቅም (ፖቴንሻል) እንዲሁም ባላቸው የማልማት ተሞክሮ ነው::

### ለውጤቱ መመዝገብ የተከናወነው ሥራ

እንደ አቶ ኢሳይያስ ገለጻ፤ ወደ ልማቱ ከመግባቱ በፊት መንግሥት ግብ አስቀምጧል:: ወይንም ቅድመ እቅድ አድርጓል:: የበጋ መስኖ ልማት ዋና አላማ በአገር ውስጥ የስንዴ ልማትን በስፋት በማከናወን በግዥ ከውጭ የሚገባ ስንዴን ማስቀረት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ገቢ ማግኘት ነው::

መንግሥት በግብርናው ክፍለኢኮኖሚ ላይ ባስቀመጠው የአስር አመት መሪ እቅዱ በሦስት የሰብል ዓይነቶች ላይ ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቷል፤ ቅድሚያ ልማቱ ውስጥ የገባው ስንዴ ሲሆን፣ ሁለተኛው የቅባት እህል ነው:: ከቅባት እህሎችም በዋናነት አኩሪ አተር ሲሆን፣ ሱፍና ለውዝ ይገኙበታል:: በሦስተኛ ደረጃ ትኩረት የተሰጠው የሩዝ ልማት ነው::

መንግሥት ትኩረት የሰጣቸው እነዚህ የሰብል ዓይነቶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማውጣት ለፍጆታ ወደ አገር የሚያስገባቸው በመሆናቸው ነው:: እነዚህ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው አቅርቦቱ በአገር ውስጥ እንዲሆን ለማስቻል ነው:: እንዲመረቱ የተመረጡት የሰብል ዓይነቶችም የኅብረተሰቡን አቅም ያገናዘበ አቅርቦት እንዲኖር ለማስቻል ነው::

የልማት ተነሳሽነቱ በስንዴ ቢጀመርም ሌሎቹም በእቅዳቸው መሠረት ይከናወናሉ:: ከቅባት ሰብሎች የአኩሪ አተር ልማት ባለፈው አመት አማራ፣ በከፊል ኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ላይ ተጀምሯል::በአኩሪ አተር ልማት ሥራ ደግሞ አማራ ክልል ብዙ ድርሻ ይኖረዋል::

መንግሥት በገበያ አዋጭነቱ፣ በምርታማነቱ፣ በየትኛውም የአየር ፀባይ መልማት በመቻሉ፣በተጠቃሚው የመግዛት አቅምና የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ ማዕከል በማድረግ በልዩ ትኩረት በእቅድ ይዞ ከሚንቀሳቀስባቸውና ልማቱም እንዲፋጠን እየሠራባቸው ከሚገኙ የቅባት ሰብሎች የአኩሪ አተር ተረፈ ምርት ለእንስሳት መኖነት በመዋል ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው:: በመደበኛው የልማት ሥራ የሚቀጥሉት ኑግ፣ ተልባ የመሳሰሉት የቅባት ሰብሎች በዋናነት ለውጭ ገበያ የሚውሉ ቢሆንም በአገር ውስጥም አቅርቦታቸው እንደተጠበቀ ነው::

በልማት እቅድ ውስጥ የተካተተው የሩዝ ልማትም በስፋት የሚከናወን ሲሆን፣ ልማቱ የሚከናወንባቸው ሰባት የሚሆኑ አካባቢዎች ተለይተዋል:: ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው አማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ፎገራ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ሲሆን፣ ወደ አምስት ወረዳዎች ይሸፍናል::ቤኒሻንጉልጉሙዝ፣ ደቡብ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላ ክልሎች ልማቱን ለማከናወን ታቅዷል:: በስንዴ ልማቱ ላይ የተከናወኑትን ተግባራት በተመሳሳይ በመፈጸም በፍጥነት ልማቱ ተከናውኖ ውጤታማ እንዲሆን ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው::

### የስንዴ ልማቱና ቀድሞ የተያዘው ግብ

እየተከናወነ ባለው የልማት ሥራ የተገኘው ውጤት አያጠራጥርም:: በቅድመ እቅድ ላይ የምርት መጠን ተቀምጧል:: ሆኖም ግን ውጤቱን በቁጥር ብቻ መለካት ስህተት ነው:: እንደ አገር የተያዘው ግብ በግዥ ወደ አገር የሚገባን ስንዴ በማስቀረት በምርት ራስን መቻል ነው::

የስንዴ ፍላጎት በየአመቱ በሦስት በመቶ ያድጋል:: በየአመቱ አገራዊ የስንዴ ምርት ፍላጎት ወይንም ፍጆታ ወደ 97 ሚሊዮን ኩንታል እያደገ ይሄዳል:: እንዲህ እያደገ ላለው ፍላጎት ምላሽ እየሰጡ መሄድ ያስፈልጋል:: በየአመቱ የሚያድገውን ፍላጎት ለማሟላት ምርቱን እያሳደጉ መሄድ ይጠይቃል::

እንደ አገር በተያዘው በጀት አመት ከአንድ መቶ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ይመረታል ተብሎ ይጠበቃል:: ስለዚህ አገራዊ ፍላጎትን በማሳካት ለውጭ ገበያ የማቅረቡ ተግባርም ይከናወናል:: የመኸሩ የሰብል ስብሰባ በመካሄድ ላይ በመሆኑ ከታኅሣሥ መጨረሻ በኋላ ነው አጠቃላይ የስንዴ ምርት የሚታወቀው:: አጠቃላይ የምርት ግምገማ ከተካሄደ በኋላ ነው መረጃዎችን ማውጣት የሚቻለው::

በበጋውና በመደበኛው በመኸሩ ከሚከናወነው የስንዴ ልማት መካከል ስላለው ግንዛቤ መያዝ አለበት ብለው አቶ ኢሳይያስ እንዳስረዱት፣ ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የመኸሩ ወይንም መደበኛው ልማት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል:: በመኸሩ የሚለማው መሬትም ሰፊ ነው:: የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ተጨማሪ ፕሮግራም፣ ጉልበትና አቅም የሚጠይቅ ሥራ ነው:: ሆኖም ግን የበጋ ስንዴ ልማቱ በአገር ውስጥ ምርት የመተካት ፍላጎትንና ለውጭ ገበያ የማቅረብ እቅድን ከማሳካት አንጻር ጉልህ አስተዋጽኦ አለው:: ስንዴ ለውጭ ገበያ የማቅረብ እቅድ በተያዘው አመት ይሳካል::

### ልማቱን ለማፋጠን በቴክኖሎጂ የተደረገ እገዛ

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል ሲሉ አቶ ኢሳይያስ ያብራራሉ:: እሳቸው እንዳሉት፤ እንደ ማጨጃ መውቂያና ሌሎች ከእርሻ ጋር የተያያዙ መሣሪያዎች ወይንም ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መንግሥት አመቻችቷል:: በተለይም በማህበር ተደራጅተው መሣሪያውን ገዝተው ለገበሬው ለሚያቀርቡ ብድር ተመቻችቷል:: ባለሀብቶችም ከባንኮች ብድር እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል::

እያንዳንዱ ገበሬ ትራክተር እንዲኖረው አይጠበቅም:: መሣሪያውን ከሚያቀርቡ አገልግሎት ሰጪዎች በመጠቀም ነው የግብርና ሥራውን እንዲያከናውን የሚጠበቀው:: በተለይ የህብረት ሥራ ማህበራት መሣሪያውን ገዝተው በተመጣጣኝ ዋጋ ገበሬውን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ::

በአማራ ክልል ወጣቶች ተደራጅተው የስንዴ ማጨጃ መሣሪያ ገዝተው አገልግሎት በመስጠት እያከናወኑ ያሉት እንቅስቃሴም ተሞክሮ ይሆናል:: አንድና ሁለት ትራክተር የነበራቸው ባለሀብቶችም ተጨማሪ በመግዛት አገልግሎታቸውን በማስፋት ላይ ይገኛሉ:: ጠንካራ ማህበራት የሌሉባቸው፣ ተደራጅቶ ለመሥራት ፍላጎት ባላሳዩ፣ ባለሀብቱም ባለመንቃቱ ክፍተት ያለባቸው አካባቢዎች ይገኛሉ:: በነዚህ አካባቢዎች በትኩረት መሥራት ይጠይቃል::

### በልማቱ የተስተዋሉ ጠንካራ ጎኖችና ተግዳሮቶች

አቶ ኢሳይያስ ከአመራር ጀምሮ ያለውን ቁርጠኝነት በጥንካሬ ጠቅሰዋል፤ ሥራውን የራስ አድርጎ ማየት በአመራሩ ዘንድ እንደሚታይም ነው የገለጹት:: እንደሮሳቸው ገለጻ፤ እቅዱ የእኔ ነው የሚል መንፈስ በፌዴራልም በክልል አመራሮች ዘንድ ይታያል:: የልማቱ ሥራ ውጤታማ የሆነውም ለዚህ ነው:: በስንዴ ልማቱ ላይ የተሻለ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተተግብሯል:: ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ እንዲሁም ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች በመጠቀም የታየው ነገር አበረታች ነው:: በበጋ ስንዴ ላይ በሽታ አለመከሰቱም ሌላው መልካም ጎን ነው:: በቂ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ መገባቱም በጥንካሬ ይገለጻል::

አቶ ኢሳይያስ እንደ ተግዳሮት ካነሷቸው መካከል ደግሞ ሌላ ሰብል ከተነሳ በኋላ ወደ ሌላ ሰብል በመዞር እህል የሚበላ ወፍ ወይም ግሪሳ የሚባለው በአንዳንድ አካባቢዎች መኖሩ ይጠቀሳል:: በልማቱ ቀድሞ ልምድ ባላቸውና በጀማሪዎች መካከል የታየውን የልማት አለመመጣጠንን እንደ ክፍተት አንስተዋል:: ወደ አገልግሎት ያልገቡ የመስኖ መሠረተ ልማቶች ቢገቡ የተሻለ አቅም እንደሚፈጥሩም ሀሳብ ሰጥተዋል::

በአጠቃላይ በስንዴ ልማቱ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት በርብርብ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል:: የዘር ብዜት በሁሉም ክልል እንዲከናወን መደረጉንም ገልጸዋል:: እንደ ማዳበሪያ ያለ የግብአት አቅርቦትን በተመለከተም ችግር እንዳያጋጥም ለበጋ መስኖ ልማቱ ከመኸሩና ከበልጉ ጋር አብሮ ታቅዶ ቀድሞ እንደሚዘጋጅም አስታውቀዋል::

እንደ አቶ ኢሳይያስ ማብራሪያ፤ አገራዊ የስንዴ መርሃግብር(ፕሮግራም)በመኸር የአነስተኛ አርሶ አደሮችና የባለሀብቶች መሬት ላይ የሚለማውን ጨምሮ በበጋ መስኖ የሚከናወነውን የሚያካትት ነው:: ልማቱም በክረምት፣ በበጋና በበልግ የሚከናወን ሲሆን፣ የእርሻ ሥራውም አካባቢዎቹ እንዳላቸው የአየር ፀባይ ይወሰናል:: የምርት አሰባሰቡም ከአካባቢ አካባቢ ይለያያል::

# አካል ጉዳተኞች በአዲሱ ሥርዓት ትምህርት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ኬሪያ ጀማል ትባላለች። የ18 ዓመት ወጣት ነች። በድሬዳዋ ከተማ በየማርያም ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ወደዚህች ምድር ስትመጣ ጀምሮ ነው ሁለት እጇቿን ያጣቻው። ቢሆንም ግን ለእሷ እግሮቿ በተፈጥሮ የተሰጧት ገጸበረከት ሆነውላታል። እግሮቿን ልክ እንደእጇቿ መልካም ዕድል አድርጋ ትጠቀምባቸዋለች። በእግሮቿ ትጽፋለች፣ ትመገባለች፣ ፊቷን ትታጠባለች ልብሷን ማጠቢያም አድርጋቸዋለች።

አካል ጉዳተኛ መሆኗ መጀመሪያ አካባቢ በተለይም ወደትምህርት ቤት ስትሄድ በብዙ መንገድ ፈትኗታል። ነፃነት የማይሰጣት በርካታ ችግርም ገጥሟታል። አንዱ በተማሪዎች ዝቅ ተደርጋ መታየቷ ነው። ይሁንና መብለጧን በተግባሯ ስታሳያቸው ነገሮች ሁሉ ተቀይረዋል። በዚያ ላይ በትምህርትቤት ያለው የመማር ማስተማር ሥራ ለእርሷ አግዟታልና ዛሬ የደረሰችበትን የክፍል ደረጃ ደርሳለች። በእርግጥ አካል ጉዳቷ ታይቶ ወደ ከተማ ባትመጣ ኖሮ ነገሮች የተገላቢጦሽ ይሆንባት ነበር። ከመገለል ባሻገር የትምህርትቤት ቁሳቁስ አቅርቦቱ እጅግ ይፈትናት ነበር። ሆኖም እናቷና እህቷ ከዚህ የመከራ ሕይወት አላቀዋታል። ችግሮችን እንድትጋፈጥ አድርገዋታል።

ሌላኛዋ ተማሪና አካል ጉዳተኛ ሀጃኢባ ያሲን ሸኩር ስትሆን፤ እርሷም እንደ ኬሪያ እጇን በተፈጥሮ አጥታ እግሯን የምትጠቀም ናት። በዘንድሮው የፈተና ጊዜ በአዲስ አበባ ሳይንስናቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን በእግሯ እየሠራች ብዙዎችን አስደምማለች። ለዚህ ደግሞ መሠረቱ ብርቱና ምቹ የትምህርት አካባቢ እንዲሁም ጠንካራ የቤተሰብ እገዛ ስላገኘች ነው።

አካል ጉዳተኝነት ትምህርትን ጨምሮ ከማንኛውም ማህበራዊ መስተጋብር እንደማያግድ ታምናለች። ነገር ግን ብዙ ፈተናዎች እንዳሉበት ታውቃለች። ቢሆንም ግን እነርሱን የሚያግዝ የመማር ማስተማር ሥርዓት ከተዘረጋለትና ለተግባራዊነቱ ሁሉም ከተጋ የአካል ጉዳተኝነት ችግሮች መፍትሄ እንጂ መከራ አይሆኑም ባይ ናት። ከእነዚህ ባለታሪኮቻችን የምንረዳው ነገር አካል ጉዳተኞች በትምህርት ዘርፉ በሚገባ ከታገዙ የአሰቡበት ላይ መድረስ እንደሚችሉ ነው። የተሰጣቸውን ዕድሎች እንደሚጠቀሙም በሚገባ መገንዘብ እንችላለን። ታዲያ እንደ አገር ምን ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላቸው ስንል ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን እንድናነሳ እንገደዳለን። የመጀመሪያው የትምህርት ዘርፉ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ እስከዛሬ ምን ሠራ የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው የሚሻሻሉት የትምህርት ሥርዓቶች ምን አዲስ ነገር አላቸው የሚለው ነው።

### ስለአካል ጉዳተኞች የሚሰጥ ትምህርት ትናንት

የአካል ጉዳተኞች ትምህርት እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ድረስ በልግስና፣ በዕምነት ተቋማት እና ድጋፍ እየተደረገላቸው የቀለም ትምህርትና የክሂሎት ስልጠና ሲሰጣቸው እንደነበር በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ልዩ ትምህርት እንደ አንድ የእውቀት ዘርፍ ተቋቁሟል። በዚህም ጊዜ የተከናወነው መዋቅር በመፍጠር ሥራውን በቅንጅት መምራት ሲሆን፣ ይህም አካል ጉዳተኛ ሕፃናትን እንደአካል ጉዳታቸው ዓይነት ለማስተማር ይቻል ዘንድ ልዩ ትምህርት ቤቶችን ማቋቋም፣ መምህራንን በማሰልጠንና ለትምህርት ሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን ማሟላት ተጀመረ። ሆኖም የተደራሽነቱ ጉዳይ አዝጋሚ ነበር። ከዚህ አንጻርም 2012 ዓ.ም የመደበኛው ትምህርት ተሳትፎ 104 ነጥብ 9 በመቶ ሲሆን፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎው 11 ነጥብ 1 ብቻ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ነባራዊ ሁኔታ ትንተና ይህንን የትምህርት አገልግሎት በተቀናጀና ሥርዓት ባለው መልክ ለማቅረብ፣ ልዩ ፍላጎት ትምህርትን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ በማድረግና የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅ እንዲቻል በሦስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ውስጥ ተካቶ መተግበሩን ቀጠለ። ይህንንም እውን ለማድረግ በ1998 ዓ.ም የመጀመሪያው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ ተዘጋጀና ወደ ሥራው ተገባ። ዓመታት እየተጠበቁም ችግሮች እየታዩ መሻሻሎች ይደረጉበት ጀመር።

አንዱ የ2004 ዓ.ም ስትራቴጂ ሲሆን፤ ይህንን በተመለከተ የትምህርት ሚኒስቴር ጥናት አካሂዷል። እናም ጥናቱ እንደሚያሳየው የ2004 ዓ.ም ስትራቴጂ የአካል ጉዳተኛ ዜጎች መብትን መሠረት ያደረገ ትምህርት



ሊሰጣቸው ይገባል የሚለውን የአካቶ ትምህርትን መሠረታዊ ፍልስፍናን የያዘ ነው። በዚህም አካል ጉዳተኞችን ጉዳት ከሌለባቸው ጋር በጋራ እንዲማሩ የሚደረግበትን የማስተማር ዘዴ ፈጥሯል። በተጨማሪም ከቀለም ትምህርቱ ባሻገር ከማኅበረሰቡ ጋር የሚኖሩበትን ሁኔታ የሚያለማምዳቸውን ዕድል ሰጥቷል። የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በተለያዩ ተጽዕኖዎች የተነሳ ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ሊገድቡ የሚችሉ አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነአዕምሯዊ ወይም የስሜት ህዋሳት እክሎች ይገጥማቸዋል። በመሆኑም በትምህርት አሰጣጡ ውስጥም እኩል አካልጉዳተኝነታቸውን ያገናዘበ የትምህርት አሰጣጥ መተግበር ያስፈልጋልና ይህ እንዲሆንም መስመሩን የከፈተ ነበር።

### በ2004 ዓ.ም ስትራቴጂ ድክመቶች

ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ድረስ የአካቶ ትምህርትን ለመምራትና ለመተግበር የሚያስችል ወጥ የሆነ አደረጃጀት የለውም። የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን የደረጃ እድገት መሰላል የሥራ መደባቸውንና ስምሪታቸውን በግልጽ የሚያሳይ የአሠራር ሥርዓት አልተዘረጋበትም። የተጠያቂነት አሠራር ሥርዓትም የለም። በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ላይ የሚገኙ አስፈጻሚና ፈጻሚዎች የስትራቴጂውን ውጤት አተገባበር ለማሳለጥ የነበራቸው ቁርጠኝነትና ግንዛቤ አናሳነው። የልዩፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮችን በዕቅድ፣ በጀት ፣በክትትል፣ በግምገማና በሪፖርት ውስጥ አካቶ አይሠራም።

በሁሉም የትምህርት እርከኖች ከፍተኛ የሆነ የልዩፍላጎት ትምህርትና የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች እጥረት ነበረበት። በመምህራን ትምህርት ተቋማት በመሰጠት ላይ ያሉት የልዩፍላጎት ትምህርት ኮርሶች ንድፈሃሳብ ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ምሩቃኑ የተግባር ክህሎት ውስንነት ይታይባቸው ነበር። በአካልጉዳተኝነት ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር የተደረገው ጥረት ውስን በመሆኑ በባለድርሻዎችና በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ የተዛባ አመለካከት በስፋት ታይቶበታል።

አንዳንዶች ካልሆኑ በቀር ብዙዎቹ ክልሎች ለአካል ጉዳተኞች የሚሆን በጀት አይመድቡም። ግልፅና አግባብነት ያላቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችም የሉም። በመረጃ ሰብሳቢዎች ክህሎት ማነስና ቸልተኝነት ምክንያት ተዓማኒ መረጃ ማግኘት አለመቻሉ፣ አካል ጉዳተኞች የሚፈልጉትን አገልግሎት አለማግኘታቸው፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የትምህርትና ሥልጠና አገልግሎት የሚያገኙት አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በቁጥር አነስተኛ መሆናቸውም ችግር ነበር። ዕድሉን አግኝተው በመማር ላይ የሚገኙትም ቢሆኑ ለሚያጋጥማቸው የትምህርት መቅሰም ችግር በቂ ድጋፍ አለማግኘታቸው ድክመት እንደነበር ተነስቷል።

የትምህርት ቤቶች ምድረ ግቢና አገልግሎት አሰጣጥ (መፀዳጃቤት፤ ቤተመጻሕፍት፤ የግቢ ውስጥ አቅጣጫ ጠቋሚ ስሌዳ፤ መዝናኛ ስፍራ፤ የስፖርት ማዘውተሪያና መጫወቻ ቦታዎች፣ተዳፋታዊ መተላለፊያ፤ ውሃ መጠጫ ቦታ፤ ወዘተ) ለአካል ጉዳተኛ ዜጎች ተደራሽ አለመሆናቸው፤ የትምህርት ቤቶች የሕንፃ ግንባታ ዲዛይን አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ አለመሆኑም ሌላው ችግር እንደነበር ጥናቱ አስቀምጧል።

የመማሪያ-ማስተማሪያ ቁሳቁሶችና ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለሟላታቸው፤ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችና አጋዥ የቴክኖሎጂ አቅርቦት አለመሟላት፤ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፤ በምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎች እጥረት በመኖሩ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ የትርጉም አገልግሎት ባግባቡ አለማግኘታቸውም ችግር ናቸው ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል ተነስተዋል።

የሥርዓተ-ትምህርቱ ይዘቶች፣ የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች፣ የመማሪያ-ማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና የምዘና ሥርዓት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች እንደ ፍላጎታቸውና ችሎታቸው ተስማሚ አድርጎ አለመተግበርና አካልጉዳተኛ ጎልማሶች ለትምህርት አገልግሎት ተደራሽ አለመሆናቸው እንዲሁም አወንታዊ ድጋፍ አሰጣጡ ሁሉንም የአካል ጉዳተኞች አለማካተቱም እንዲሁ ድክመት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይ ነው።

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የታቃፊ የአዕምሮ ውስንነት ላለባቸው ተማሪዎች የሙያ ስልጠና ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤ በልዩ ትምህርትቤቶችና ልዩ ክፍሎች የሚያስተምሩ የልዩ ፍላጎት መምህራን ሥራው ከሚጠይቀው ጥረት ውስብስብነትና ክብደት አንጻር የማበረታቻ ጥቅማጥቅም አለመኖሩ፤ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የትምህርት ተደራሽነት፣ ተሳትፎና የትምህርት ማጠናቀቅ ለማበረታታት የድጎማ ጥቅማጥቅም አለመኖሩ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ መስጠት አለመቻሉም ሌላው ደካማ ጎን እንደነበረ በጥናቱ ተቀምጧል።

### አዲሱ የትምህርት ሥርዓት ምን ይዞ መጣ?

አዲሱ የትምህርት ስትራቴጂና ሥርዓት በ2004 ዓ.ም የነበሩ ድክመቶችን በሙሉ ያየና ወደ ትግበራ እንዲገባበት ሥርዓት የዘረጋ ሲሆን፤ በጥናቱ እንደተለየውም የልዩፍላጎት/አካቶ ትምህርትን የሚመራ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ አደረጃጀት ይቋቋማል። በየደረጃው ለሚመደቡ ባለሙያዎች የሚያገለግል የሥራ ምዘናና የደረጃ ምደባ አወሳሰን ጥናት ይከናወናል፤ ተግባራዊ ይደረጋል። በየደረጃው ለተመደቡ የሥራ ክፍሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ የሥራ ላይ ስልጠና ይሰጣልም።

በልዩ ትምህርት ቤቶችና በልዩ ክፍሎች የሚማሩ አካልጉዳተኛ ተማሪዎችን ለሚያስተምሩና ለሚደግፉ መምህራንና ርዕሰ መምህራን ልዩ የማበረታቻ ጥቅማ ጥቅም የሚያገኙበትን ሥርዓት ይዘረጋል። ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና ከመሠረተ ማህበረሰብ ተሃድሶ ሠራተኞች ጋር በመተባበር ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ የቤትለቤት ምዝገባና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ይሠራል።

በልዩ ትምህርት ቤቶች፣ በልዩ ክፍሎች፣ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚማሩ አካልጉዳተኛ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ የሚያጋጥቸውን እንቅፋቶች ተቋቁመው በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል የድጎማና ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል። ተስማሚ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በአገሪቱ ሕግ መሠረት ከቀረጥ ነፃ በሆነ አግባብ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል። ተስማሚ የትምህርት ቁሳቁሶችንና አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ለማምረት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በትብብር እንዲሠራ ይሆናልም ተብሏል።

ሌላው በአዲሱ የትምህርት ስትራቴጂ ውስጥ የተካተተው ነገር በቅድመ- አንደኛና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና መምህራን ቋንቋ፣ በብሬል መጻፍና ማንበብ፣ በዳሰሳ ምልክት ቋንቋ እና በመሳሰሉት ስልጠናዎች መስጠት ነው። በተጨማሪም በአካታች የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ተሳትፎን ለማሳደግ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎችን መመደብ፤ ለዚህም የሥራ ምዘናና ደረጃ ምደባ አወሳሰን ጥናት ይደረጋል። ትምህርት ቤቶችን ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች የትምህርት ተሳትፎዎቹና አካታች ማድረግ አንዱ በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት ይካተታል የተባለ ጉዳይ ነው። ለአካል ጉዳተኞች ፈታኝ የሆነው የትምህርት ቤት ዲዛይን ደግሞ ከዚህ መካከል የሚጠቀስ ሲሆን፤ ነባር የትምህርት ቤት ሕንፃዎች ሳይቀሩ ሁለንተናዊ ንድፍ መርሆችን ይከተላሉ ተብሏል። በተጨማሪም በትምህርት ቤቶች ስታንዳርድ መሠረት የትምህርት ቤቶች ምድረ-ግቢና አገልግሎት መስጫዎች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ምቹ እንዲሆኑ ይደረጋል። ለአፈጻጸሙም የተደራሽነት ስታንዳርድ መመሪያ ይዘጋጃል።

የአካል ጉዳተኞችን መሠረት ያደረጉ ግቦች፣ ይዘቶች፣ የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች፣ የመማሪያ-ማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና የምዘና ሥርዓት እንደፍላጎታቸውና ችሎታቸው ተስማሚ ማድረግም አንዱ በአዲሱ ሥርዓት የሚካተት ነው። ከፍተኛ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ካለባቸው ጉዳት አንጻር በቀለም ትምህርት መዝለቅ ለማይችሉት ደረጃ ትምህርት ቤቶች (የመንግሥትና የግል) የሙያ ስልጠና መርሃ-ግብር ይመቻቻል። የፈተና እና ምዘና ሥርዓቱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች እንደ ጉዳታቸውና የትምህርት ፍላጎታቸው ተግባራዊ ይሆን ዘንድ በጥናት ላይ የተመሠረተ ተስማሚና የተለየ የፈተና እና ምዘና (አዎንታዊ ድጋፍን ጨምሮ ሥርዓት መዘርጋት፤ ለዚህም የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንደሚውልም ጥናቱ አመላክቷል።

ሌላው በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት የተካተተው ነገር የነፍስ-ወከፍ የትምህርትመርሃ-ግብር የሚያስፈልጋቸውን አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን በመለየት የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ሥርዓትን መዘርጋት ነው። መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር በትምህርት ሥርዓቱ የተዘጋጁ የተማሪዎች መማሪያ መጻሕፍትን ተደማጭና ለእይታ በሚመች መልክ የሚቀይርና እንደየ ጉዳታቸው ዓይነት የሚያስራጭ፣ የትምህርት ቁሳቁስ የሚያዘጋጅ አገራዊ ማዕከል ማቋቋምም አንዱ ነው።

ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት፣ ወጣቶችና ጎልማሶች ከቤተሰብ ወደትምህርትቤት፣ ከክፍል ወደ ክፍል ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም እንዲሁም ከትምህርትና ስልጠና ሂደት ወደ ሥራ መስክ በሚሸጋገሩበት ወቅት በነበሩበት ቦታ ይደረግላቸው የነበረውን ድጋፍና አጠቃላይ የባህሪ ገጽታ የሚገልጽ ማስረጃ በማዘጋጀት የትስስር ሥርዓት እንዲሁም የአተገባበር መመሪያ ይዘጋጃል። በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ አገልግሎት የሚሰጡ የመለያ፣ የዳሰሳ ማዕከላት እና የሪፈራል ሥርዓት በመዘርጋት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል። በትግበራ ላይ ያለን የክላስተር ትምህርት ቤቶችን ወደ አካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከልነት የመለወጥ ሂደት በማስፋት በክልል/ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮዎች፣ በዞን ትምህርት መምሪያዎች እና በወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች አማካኝነት ተጠናክሮ ይቀጥላልም የሚለው በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት ይተገበራል ከተባለው መካከል ነው።

በመጨረሻ አዲሱ የትምህርት ሥርዓት ለአካል ጉዳተኞች ይዞ የመጣው ነገር የጉድኝት ማዕከላት ትምህርት ቤቶችን በሰለጠነ የሰው ኃይል እና መሠረታዊ የሆኑ ተስማሚ የትምህርት ቁሳቁሶችና ቴክኖሎጂዎች (ብሬይል ወረቀት ስሌትና ስታይለስ፣ ተናጋሪ የሂሳብ ማሽን፣ አባከስ፣ ብሬልታይፕራይተር፣ ተናጋሪ መጻሕፍት፤ ዲጂታል መቅረፀ-ድምፅ፣ ተናጋሪ ሶፍትዌሮች የተጫኑ ኮምፒዩተሮች፣ የምልክት ቋንቋ መጻሕፍት፣ የብሬይል መጻሕፍት፣ የጎላ ጽሑፍ፣ የጽሑፍ ማጉያ) መሣሪያዎች፣ አማራጭና አጋዥ የተግባቦት ዘዴዎች ሌሎችን በማሟላት በማዕከላቱ እና በሳተላይት ትምህርት ቤቶች ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ የሚለውነው። ይህ ሲሆን ግን አተገባበሩ ላይ ከሁሉም አካላት ልዩ ትኩረትን እንደሚሻ በጥናቱ ገልጸዋል። ስለዚህም ለተግባራዊነቱ ሁሉም ይትጋ በማለት ጽሑፋችንን ቋጨን። ሰላም!!

# ወቅታዊ

# ‹‹የሰላም ስምምነቱ ሌሎቹ የአፍሪካ አገራት በአፍሪካ ኅብረት ላይ እምነት እንዲያሳድሩ የሚያደርግ ነው››

**- አቶ አባተ ኪሾ**
**የቀድሞ የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር**



ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

አስቴር ኤልያስ

**ዛሬም በፌዴራል መንግሥቱና በሕወሓት መካከል ግጭት እንዲቀጥል አጥብቀው የሚሹ አካላት አሉ፡፡ ከዚህ ፍላጎታቸው በላይ ኑሯቸውን የመሠረቱት በሕዝብ ደምና አጥንት ላይ በመሆኑ የሚያተርፉትም ከሕዝብ ሰላም ሳይሆን ከግጭት በመሆኑ እንደለመዱት ቀርጦ የመቀጠሉን ክፉ አባዜ ተያይዘውታል፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያ ትናንት የአደዋን ድል በማስመዝገብ የአፍሪካ ኩራት እንደሆነች ሁሉ ዛሬም የሰላም ስምምነቱ በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት አፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ ብላ አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን ለመፍታት ብቁ መሆናቸውን አስመስክራለች፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ልማቷን በማፋጠን ላይ ትገኛለች፡፡ ሰሞኑን በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገውን የሰላም ስምምነት አስመልክተን ከቀድሞው የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አባተ ኪሾ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በፌዴራል መንግሥቱና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ኢትዮጵያ የሄደችበትን ጽኑ አቋም የሚያሳይ ነው የሚሉ አሉ፤ እርስዎ የተገኘውን ውጤት እንዴት ያዩታል?**

**አቶ አባተ፡-** በመጀመሪያ የሰላም ስምምነቱ ለሁሉም እፎይታን የሰጠ ነው፡፡ ምክንያቱም የሰው ሕይወት ከመጥፋት፣ የእናቶችና የሕፃናትን ሮሮ ከመስማት ብሎም ኢኮኖሚው ከመላሸቅ አንጻር ሲታይ እፎይታን የሰጠ ነው፡፡ የዜጎች መፈናቀልም ቢሆን እልባት የሚያገኝበት ስለሆነ ሁሉም ሰው በሚያስብል ደረጃ ስምምነቱን የወሰደው በአዎንታዊ ጎኑ ነው፡፡ ይህም አካሄድ ወሳኝ የሆነና የኢትዮጵያንም ቁርጠኝነት በግላጭ ያሳየ እንዲሁም አርዓያነቷን ያረጋገጠ ጭምር ነው፡፡

ነገር ግን ይህ ነገር መሆን የነበረበት ቀድሞ ነው የሚል እይታ አለኝ፡፡ ብዙ ሕይወት ካለፈ በኋላ እና ብዙ ንብረት ከወደመ በኋላ መሆኑ ትንሽ የሚያሳዝን ነው፡፡ ይህ የሰላም ስምምነት ቀድሞ ቢደረግ ኖሮ ምን ያህል ማትረፍ እንደምንችል ይታወቃል፡፡ እኔ ካላሸነፍኩ የሚል አካል ባይኖርና ጦርም ባይመዝ ኖሮ ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን እናጣም ነበር ብዬ አስባለሁ፡፡

በእኛ በኩል ሰላም እንዲኖር ብዙ ጥረናል፤ እርቅ እንዲወርድ ሽማግሌ በመላክም ብዙ ተደክሞ እንደነበር ይታወሳል፡፡ በተለይ በአመራር ደረጃም ብዙ ተለምኖ ሰንብቷል፤ ነገር ግን በአንድ በኩል ይሰማ እና በሌላ በኩል ቸል ሲባል ይስተዋላል፡፡ ይህን ካለመረዳትም የተነሳ ወደግጭትና ወደጦርነት ተገብቶ ቆይቷል፡፡ ድጋሚ ግን እንዲህ ዓይነት ጥፋት እንዳይመጣ ትልቅ ትምህርት ሊወሰድ ይገባል ብዬ አስባለሁ፡፡ እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ማለቱ መፍትሔ ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲያም ሆኖ በአሁኑ ሰዓት የሰላም ስምምነት ላይ መደረሱ ተጨማሪ ዋጋ ላለመክፈል ትልቁ ጉዳይ ነውና ይህ መሆኑ ትልቅ ደስታን የሚሰጥ ስኬት ነው፡፡

ይህ ተስፋን የሚሰጥ የሰላም ስምምነት ቀጣይ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው ማለቱ ደግሞ ተገቢ ነው፡፡ ቀጣይ ጦርነት እንዳይኖር ግጭት እንዲቆም መደረግ ያለበት ምንድን ነው የሚለውን ማየቱ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ የስምምነት ሰነዱ ወደመሬት እንዲወርድስ ማን ምን ማድረግ ይጠበቅበታል፤ ተግባራዊ ለማድረግ ያለው ቁርጠኝነቱስ ምን ያህል ነው ብለን ጥያቄ ማንሳታችንም የማይቀር ነው፡፡ ነገር ግን በተደረገው የሰላም ስምምነት የተስፋ ምልክት አይተናልና ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ቀሪው ጉዳይ በሒደትና በተቀመጠለት መርሃግብር እንደሚከናወን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሰላም ስምምቱ አፍሪካ የራሷን ችግር በራሷ መፍትሔ መስጠት ይኖርባታል የሚለውን ሀሳብ በተግባር ያሳየ ነው የሚሉ አሉና እዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ አባተ፡-** እውነት ነው፤ አፍሪካ የእርሷን ችግር በእርሷ መፍትሔ አምጭነት መፍታት እንደምትችል አመላክቷል ማለት ይቻላል፡፡ ቀደም ሲልም እኔ በኃላፊነት በነበርኩበት ጊዜ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትን አውቃለሁ፤ በወቅቱ ስምምት የተደረገው አልጀርስ ላይ ነበር፡፡ ቀጥሎ ደግሞ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል ሲደረግ የነበረው የተኩስ ልውውጥ እንዲቆም የሚያስችለው የሰላም ስምምነት በዚሁ በአህጉራችን በደቡብ አፍሪካ ላይ ነው፡፡ የጥይት ድምጽ እንዳይሰማና ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ የሚያደርግ ስምምነት መደረጉም ትልቅ ስኬት ነው፡፡ በእርግጥ በአሁኑ በደቡብ አፍሪካ ላይ የተካሄደው ብቻ ሳይሆን በአልጀርስ ላይም የተካሄደው ስምምነት የአፍሪካ ሚና ነበረው፡፡

በተለይ ደግሞ አሁን በደቡብ አፍሪካ በተካሄደው የሰላም ስምምት ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት በጣም ጽኑ አቋም የነበረው እና አፍሪካም የራሷን ችግር በራሷ መንገድ መፍትሄ መስጠት የሚያስችላት አቋም ላይ መድረሷን አመላካች ነው፡፡ ይህን የአህጉሪቷን መንገድ ደግሞ ሌሎች ሊያከብሩላት ይገባል የሚል ጥያቄ በአቋም ደረጃ በመያዙ ወዲህ ወዲያ የሚገፉ ኃይሎችም ያንን አቋም አምነው ወደጠረጴዛ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ በማድረግ መንገድ ኢትዮጵያ የተጫወተችው ሚና የላቀ ነው፤ ለኢትዮጵያም ትልቅ ኩራት ነው፡፡

ቀደምት የአፍሪካ መሥራችነቷን ክብርን እንዲያሰጣት ያደረገ ስምምነት ነው፡፡ የሰላም ስምምነቱ ሌሎቹ የአፍሪካ አገራት በኅብረቱ ላይ እምነት እንዲያሳድሩ የሚያደርጋቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቀጣይ በአፍሪካ ለሚኖሩ ግጭቶችም ጭምር በኢትዮጵያ አማካይነት መፍትሔ ማስቀመጥ እንደሚቻል ያሳየም ነው፡፡

አድዋ ለጥቁሮቹ የአልደፈርምና የአልገዛም ባይነትን መሠረት ጥሏል፡፡ ይህም የሰላም ስምምነት ማንም እንደፈለገ ጣልቃ ገብቶ እኔ ያልኩትን ብቻ አድርጎ ብሎ እንዳይወስን የሚከለክል ነው፡፡ ስምምነቱ ሌሎች አፍሪካዊ ወንድሞቻችንም አፍሪካ በአፍሪካውያን መፍትሄ ማምጣት ችላለች ብለው እንዲያምኑ አድርጓልና በአንድ በኩል ለአፍሪካ ክብር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አፍሪካውያን የራሳቸውን ችግር በራሳቸው ለመፍታት እንደሚችሉ ማሳያ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ለቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ለሆኑት ለኦሊሴንጎ አባሳንጆ ትልቅ አክብሮት አለኝ፤ በተመሳሳይ ለቀድሞው የኬንያ ፕሬዚዳንት ለኡሁሩ ኬኒያታም እንዲሁ፡፡

ኬንያም ብትሆን በአሁኑ ጊዜ ጥሩ የዴሞክራሲ ተምሳሌት እየሆነች ያለች አገር ናት። በቅርቡም ኡሁሩ ኬኒያታ ስልጣናቸውን ሕዝብ ለመረጠው አካል ማስረከብ የቻሉትና የእኛንም ጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ለመፍታት የተሳተፉ ናቸውና ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

አፍሪካ በሌሎች ለምሳሌ በተባበሩት መንግሥታት፣ በዩናይትድ ኔሽን በቋሚ መቀመጫነትና ድምጽን በድምጽ የመሻር አቅም እንዲኖራትም ይህ ማሳያ ነው፡፡ ከዚህ በላይ መደፈርም ያለብን አይመስለኝም፡፡ አህጉራችን በመታረቅና በማስታረቅ ሥራ ላይ መጠመድና በዚህም ተግባር መገታት የለባትም፤ በዓለም አቀፋም ማኅበረሰብ ዘንድ የውሳኔ አካል በመሆን ድርሻ ሊኖራት ይገባል ባይ ነኝ፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንዳሉት መላ ኢትዮጵያውያን አፍሪካውያን ወንድሞቻችንን ይዘን ተገቢ ቦታ ሊሰጠን ይገባል፡፡ በመሠረቱ ማንም ቢሆን ይህ ለእናንተ ተገቢ ቦታ ነው ብሎ ሊሰጠን አይችልም፡፡ እኛ አፍሪካውያን ራሳችን ቁርጠኞች ሆነን ተገቢ ቦታ ላይ ለመድረስ መጣጣር አለብን፡፡ ይህም ደቡብ አፍሪካ ላይ በተደረሰው የሰላም ስምምነት ተጀምሯል ብዬ አምናለሁ፡፡

በሌላ መልኩ ግን አንድ ቅር የሚለኝ ነገር አለ፡፡ ይኸም እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀደምት ከሚባሉ አገራት መካከል ተጠቃሽ ነን፡፡ መንግሥት ያለን፤ ዴሞክራሲን ለሌሎች ያለማመድን እንዲሁም በርካታ እሴቶች ያሉን አገር ነን፡፡ በመሆኑም የውስጥ ችግራችንን ወንድሞቻችን ወደሆኑት አፍሪከውያንም ድረስ ሳይደርስ እና እነርሱንም ሳያደክም በራሳችን መፍታት እንችል ነበር እላለሁ፡፡ በዚያ ልክ መሥራት አለመቻላችንና ወንድሞቻችንን ከመጥራታችን በፊት በውስጦቻችን ያለውን ችግር በመነጋገር ብንፈታ ኖሮ ያጋጠመን ፈተና አይፈጠርም ነበር፡፡

ስለዚህ በዚህ ጉዳይ እኛም ትምህርት ወስደን አፍሪካውያንን ወንድሞቻችንን ከምናስቸግርበት መውጣት አለብን፡፡ ስለዚህም በዚህ ልክ ይህ የአሁኑ ስምምነት ትምህርት ሊሆነን ይገባል ብዬ አስባለሁ፡፡ እኛ መደማመጥ አለብን፤ እኔ ያልኩት ካልሆነ በሚል በግብታዊነት መጓዙን መተው አለብን፡፡

ጽንፈኝነትን ይዘው አገርን አደጋ ላይ የሚጥሉ አካላት ከዚህ ዓይነት መንገዳቸው መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ክፍተት የሚፈጠረው በእነዚህ አካላት አማካይነት ነው፡፡ ክፍተት ከሌለ ግን ማንም እንዳሻው ሊደፍረን አይችልም፡፡ አንድነታችን በጽኑ መሠረት ላይ የተገነባ ነው፤ አያቶቻችን እና ቅድመ አያቶቻችን የታፈረችንና የተከበረችን አገር ለእኛ አስረክበውናል፡፡ ስለዚህም ይህን ወደኋላ መለስ ብለን ማየት ይኖርብናል፡፡ በመሆኑም የአፍሪካ ወንድሞቻችን ያደረጉት አስተዋጽኦና ችግራችንን በራሳችን አህጉር በሆነችው በአፍሪካ መፍትሔ ይምጣለት ማለታችን እንደተጠበቀ ሆኖ ብዙ ትምህርት ልናገኝበት የሚገባም አካሄድ መሆኑን ልንዘነጋ አይገባም፡፡

# ወቅታዊ

**አዲስ ዘመን፡- የሰላም ስምምነቱ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል ያስፈ ቁስል ሲሽር የሚችለው በምን ዓይነት አግባብ ነው? ወደኋላ በመመለስ የነበረው ቁስል ሳይነካኩ ተግባራዊ ማድረግ የሚገባው እንዴት ነው ይላሉ?**

**አቶ አባተ፡-** በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፤ እውነት ለመናገር ቁስሉን ሳንነካካ ሰላሙን ወደመሬት ማውረድ የምንችለው እውነት ለመናገር አንዱና ትልቁ ምን ያህል የሰው ሕይወት አለፈ? ምን ያህልስ ንብረት ወደመ? ምን ያህል ሰው ተፈናቀለ? ይህስ ነገር ላይደገም ለአንዴና ለመጨረሻ እልባት ማግኘት የሚችል እንዴት ነው? ማኅበረሰባቸው በሰላም ዙሪያ ያለው አስተሳሰብ ምንድን ነው? ልጄ ሞቷል? ወንድሜ ቆስሏል? ኢኮኖሚዬ ተናግቷል? ብሎ የሰላም ስምምነቱ ከተደረገ በኋላ የመቆጨት ስሜት ማስተጋባቱ ስምምነቱ ተግባራዊ እንዳይሆን ከማድረግ የዘለለ ለሰላሙ መስፈን የሚያመጣው ነገር የለውም።

ከስምምነቱ በኋላ ከኅብረተሰቡ የተደመጠው እፎይታ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የመጀመሪያው የጦርነት ሰለባ የሆነውና የሚሆነው ራሱ ኅብረተሰቡ ነውና ነው። የአንዳንዶቻችን የፖለቲከኞች አዕምሮ ውስጥ ያለው ነገር ግን በየሰው ልብ ውስጥ ያለውን ረመጥ በመቆስቆስ ከፍሙ በመሞቅ የራስን ኑሮ ማደላደል የመፈለግ ዓይነት ስሜት ነው። ሰው እንዲጋጭና እንዲፈናቀል ሌሎች ሰበቦችን የምንፈልገው እኛ ፖለቲከኛ ነን ባዮች ነን። ይህ ጎደለብህ፤ እዚህ ላይ ተጨማሪ የለህም፤ አንተኛው አሸነፍክ፤ ያኛው ደግሞ ተሸነፈ እያልን ከበሮ የምንደልቀው ፖለቲከኞች ነን።

ሕዝብ በሰላም ስምምነት ጉዳይ ቁርጠኛ ነው። ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጦርነቱ ይቁም እንጂ ሌላ ፍላጎት የለውም። ጦርነት ሲቆም ሰው አይሞትም፤ ጦርነት ሲቆም ሰው አይፈናቀልም። ኢኮኖሚው አይወድምም። ስለዚህ በሕዝብ ልብ ውስጥ የጦርነቱ መቆም የፈጠረው ስሜት በአንዳንድ ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶቹ አካባቢም ቢፈጠር ሰላሙን በአግባቡ ማጣጣም ይቻላል።

ለሰላም መስፈን አንድ ጠብታ አስተዋጽኦ ላይጨምር በየአህጉራቱ ተሰልፎ ይህ ጎድሎብሃልና መጮህ አለብህ፤ ይህንን አጥተሃልና ጦር መምዘዝ አለብህ ብሎ ለሚያዘው አካል ስፍራ አለመስጠት መልካም ነው። ያለፈን በመነካካትና ያልተፈጠረውን እንደተፈጠረ አድርጎ ማቅረብ የሕዝብ መፈናቀልና ከኑሮው መስተጓጎል ውጪ የሚያመጣው ፋይዳ የለውም። የሰላም ባለቤት ራሱ ሕዝቡ ነው። ይህን የሰላም ስምምነቱንም ተቀብሎታል። ሕዝቡ የሰላም ስምምነቱን በተቀበለው ልክ በየቦታው እና በየደረጃው የሚገኙ መሪዎች ለዚህ ጉዳይ በተለይ ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰዎች ኃላፊነቱን ሊወስዱ ይገባል። ኃላፊነት በጎደለው መንገድ በሠራነው ልክ መልሰን ወደዚያ ወደማንፈልገው ግጭት መግባታችን አይቀርምና ድጋሜ እንዳይከሰት ሕዝቡም ሌላውም በዚያ ልክ መረዳት ይጠበቅበታል። በጦርነት ለዘመናት ብንቆይም እንኳ ጎዶሎቻችንን አንሞላውም። ያለፈውን እያሰብን የወደፊታችንን መልካም ነገር ከማጣት በስተቀር ለሰላም የሚያመጣው አስተዋጽኦ ብዙ ግምት የሚሰጠው አይደለም።

እርግጥ ነው ክቡር ከሆነው ከሰው ሕይወት በተጨማሪ ብዙ መሠረተ ልማቶች ወድመዋል። ለዚህ ሁሉ ውድመት ዋናው ችግር የሰላም አለመኖር ነው። የትኛውም የማኅበረሰብ ክፍል ቢጠየቅ ይህን ጉዳይ በጦርነት አስከብሩልን ብሎ አይናገርም። ወደትግራይ ክልልም ብትሔጂና ይህን ጉዳይ ብትጠይቂ ጦርነቱ ቀጥሎ ውጤቱን ማየት እፈልጋለሁ የሚል ማኅበረሰብ የለም። በጦርነት አሸናፊነት የለም። በተለይ ደግሞ በወንድማማቾች መካከል የሚደረግ ጦርነት በአሸናፊነት ተጠናቀቀ የሚባለው በመነጋገርና ችግሮችን በጋራ መፍታት ሲቻል ብቻ ነው። ምክንያቱም ማንም ምንም ያህል ቢዋጋ አያሸንፍም፤ እንደእርሱ የሚሆን ከሆነ ደግሞ ውጤት አልባ ነው የሚሆነው። መጨረሻችን የሚሆነው ጻጸት ነው። በሰው ኃይልም ሆነ በኢኮኖሚ ባዶ የሚያደርግ ይሆናል። ትርፍ ብሎ ነገር አይኖርም። እንዲያውም ትርፍ ነው የሚባል ነገር ካለ የ20 እና የ50 ዓመት ቂምና ቁርሾ መቁጠር ነው። ቂምና ቁርሾ ይዞ ደግሞ ሰላም ማምጣት የሚቻል አይሆንም።

በተለይ ማሳሰብ የምፈልገው ፖለቲከኞቹ ከአዙሪትና ከጀብደኝነት ስሜት ወጥተው ሕዝባቸው ወደሰላም እንዲመጣ ማድረግ ግዴታ ውስጥ መግባት አለባቸው። አሁንም የውይይቱ ማዕከል መሆን ያለበት ሰላም ነው።

በደቂቃ ውስጥ የፌዴራል መንግሥትና ሕወሓት



መካከል የሰላም ስምምነቱ ሲካሄድ ብዙ ነገር በአንዴ ጸጥ ረጭ ማለቱ ለምን ይመስልሻል፤ ስስ ብልቱ የት ዘንድ እንዳለ ለይተን ማወቅ አለብን። በዚህ ልክ ወደታችኛው እና ወደ ሕዝቡ ወርደን የመፍትሔው አካል መሆን አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንዶች የሰላም ስምምነቱ ዘላቂ ከመሆን አኳያ ስጋት ብጤ ያለባቸው አካላት አሉ፤ ከዚህ አኳያ የተደረሰበት የሰላም ስምምነት ዘላቂ እንዲሆን ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**አቶ አባተ፡-** እውነት ነው የጦርነት ገፈት ቀማሾቹ የጦርነትን አስከፊነት ከማንም በላይ ይረዳሉ ብዬ አምናለሁ። ጦርነት የሚባለው ቃል በራሱ መንፈስን የሚረብሽ ነው። ጦርነት ሁለንተናን የሚረብሽ ድርጊት ነው። ትንሽ ነው ትልቅ ነው በሚል የሚምረው አካል አይኖርም፤ ከሚኖሩባት ጎጆ ያስወጣል፤ ሁሉንም ከየደጁ ያፈናቅላል። የሚያስፈልገውን መሠረተ ልማት ያሳጣል። ከዘመድና ከወገን ያራርቃል፤ ይለያልም።

የሰላም ስምምነት መደረጉ አንድ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ስምምነቱ ወደመሬት የሚወርደው እንዴት ነው? በዛስ ልክ ተገንዝበናል ወይ? የደረሰውን አደጋ ውስጣችንን ረብሾታል ወይ? ለዚህ ነገር ትኩረት ሰጥተን የማንንቀሳቀስ ከሆነ ችግር ነው።

ጦርነት ክብር አይደለም። ለጦርነት ቅስቀሳ የምናደርግ አካላት ልናፍር ይገባል። ወንድም ወንድሙን መግደል ችሎታ ወይም እውቀት አይደለም። ይልቁንም ውርደት ነው። ሰው ምን ይለኛል መባል አለበት። በዕድሜዬ ከደርግ የ17 ዓመት ጦርነት ጀምሮ ሦስት ጦርነትን አይቻለሁ። የኢትዮ-ኤርትራ እና አሁን በሰላም ስምምነት ላይ የተደረሰበትን ጨምሮ በዕድሜዬ ያየኋቸው ናቸው። በጥቅሉ ምንም እንኳ ጊዜው ተከታታይ አይሁን እንጂ ለ22 ዓመት ያህል ኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ነበረች ማለት ይቻላል። ይህ 22 ዓመት የአንድ ትውልድ ዕድሜ ነው። በመሆኑም ይህንን የምወስደው አንድ ትውልድ በሙሉ እንዳጣነው አድርጌ ነው።

ሁልጊዜም ቢሆን አፍሪካውያን እኛን እያስታረቁ መኖር አለባቸው የሚያሰኝም ነገር አለ። ይህ የጦርነት ጉዞ አንድ ቦታ ላይ ሊቆም የግድ ነው። ለዚህ ደግሞ ሁላችንም የየድርሻችንን መወጣት ይጠበቅብናል። አመጸኞች፣ አመጽ ይዛችሁ ወደጫካ የምትገቡ፣ ወይም ደግሞ ጥያቄ ያላችሁ ብትኖሩ ችግርም ሆነ የያዛችሁት ጥያቄ መፈታት የሚቻለው በጠረጴዛ ዙሪያ መሆኑን መረዳት አለባችሁ። ይህን ስታደርጉ የመፍትሔው አካል ትሆናላችሁ።

አሁን የተደረገው የሰላም ስምምነት ችግሮች በጠረጴዛ ዙሪያ በመወያየት እንደሚፈታ ትልቅ ማሳያ የሚሆን ነው። ዛሬም ቢሆን የትኛውም ጥያቄ ቢኖረን ማስመለስና መፍታት የምንችለው በጠረጴዛ ዙሪያ መነጋገር ስንችል ነው። የመንደር አለቃም ቢሆን ጥያቄ ሲኖረው ማስቀደም ያለበት ውይይትን ነው። ይህ አካሄድ ቂምና ቁርሾን አስወግዶ በሰላም ለመኖር የሚያስችል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ አካላት ከሰላም ስምምነቱ በተቃራኒ ለመቆም ሲዳዳቸው ይስተዋላል፤ በተለይ ደግሞ ከሕወሓት በኩል ነን የሚሉ በውጭ አገር ያሉ አካላት የሰላም ስምምነቱን ሲጻረሩ ይታያሉና ለእነዚህ አካላት የሚያስተላልፉት መልዕክት ይኖራል?**

**አቶ አባተ፡-** በስምምነቱ ውስጥ ያሉ መሠረታዊ ነገሮችን በደንብ ካስተዋልን በአንድ አገር ውስጥ ሁለት ሰራዊት ሊኖር አይችልም። አበቃ! አንዱ ቁም ነገር ይህ ነው። በአንድ አገር ውስጥ አንድ መከላከያ ይኖራል፤ እሱም የአገርን ዳር ድንበርም ሆነ ሕልውና ያስጠብቃል።

የክልል መዋቅሮችን ስናይ ግን ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው ሲያተዳድሯቸው ፖሊስ፣ ልዩ ኃይል፣ ሚሊሺያ ብሎም የተመጣጠነ የመሣሪያ አቅም ይኖራቸዋል። ይህ ማለት ኢትዮጵያ ስትመራ የቆየችበት አካሄድ ሲሆን፣ የሚከናወነውም በተቀመጠው ስምምነት መሠረት ነው። ከዚህ ውጪ የሚሆኑና በተለያየ አጋጣሚ የተያዙ መሣሪያዎች መሆን ያለባቸው በአንድ መከላከያ ኃይል በመሆኑ መከላከያ ሊረከበው ይገባል። ምክንያቱም በየመንደሩ መሣሪያ ተበትኖ አገር ሰላም ውሎ ይደር ማለቱ አጠያያቂ ነው የሚሆነው። ይህ በስምምነቱ የተቀመጠው ጉዳይ ለሰላሙ ትልቅ መሠረት የሚሆን ነው።

ውጭ አገር ተቀምጦ ጦርነት ነው አዋጪ ለሚል አካል ጦርነት መፍትሔ አለመሆኑን መናገር እፈልጋለሁ። አዋጪው ጦርነት ነው ብሎ መናገር በራሱ እነርሱን የማይፈጃቸውን ሕዝብን ግን የሚያቃጥል እሳት እንደማቀጣጠል ይቆጠራል። ስለዚህም በተቻለ መጠን አደብ ቢገዙ ጥሩ ነው። ከዚህ በላይ ክቡር የሆነው የሰው ሕይወት መጥፋት፤ ንብረትም መውደም የለበትም። ከዚህ በላይ መዋረድም ተገቢ አይደለም።

አንደኛ ድህነት እንዲጨምር የሚያደርገው ጦርነቱ ነው። ኢትዮጵያ በሁለቱ ዓመት ያጋጠማት ግጭት በራሱ ሊያካክሰው የሚችል የኢኮኖሚ አቅም ከባድ ነው። ድህነት እንዲጠፋ ከፈለግን እና ድሃ እንዳንባል የምንወድ ከሆነ እኛ በምንኖርባት አህጉር በሙሉ ጦርነት መቆም መቻል አለበት። መሄድ ያለብንም ጦርነት የሚቆምበት መንገድን መከተል ነው እንጂ ተጨማሪ ጦርነት እንዲካሄድ መቀስቀስ ግን የሚኖረው ፋይዳ በፍጹም አይታየኝም። ስለዚህ ጦርነቱ እንዲቆም በገባነው ልክ ኃላፊነቱንም እኩል መውሰድ ይኖርብናል። በዙሪያችን ያሉ ጫጫታዎች በጊዜ ሒደት የሚሰክኑ ይሆናሉ። የግንዛቤ ችግሮች ያመጧቸው ጫጫታዎች ሊሆኑ ስለሚችሉም የሰላም ስምምነቱ ወደመሬት ሲወርድ የሚስተካከሉ ይመስሉኛል።

ነገር ግን የባለድርሻ አካላት ሚና ምንድን ነው ከተባለ ስምምነቱ ጊዜ ሳይወስድ ወደ መሬት ማውረድ ነው። በተስማማነው መንገድ መሄድ ከቻልን ከዚህና ከዚያ ማዶ የሚሰማው ጩኸት ይሰክናል። ይህ ጎደለብህ፤ ያንንን ተነፍገሃል፤ በዚህስ ጉዳይ የተሰጠው መልስ… እየተባለ የሚነገረው ሁሉ ስምምነቱ ተግባራዊ ሲደረግ መስተካከል የሚችል ነገር ነው። ቀድሞውኑ ወደጦርነቱ እንድናመራ የማያደርጉን ጉዳዮች ናቸው ወደጦርነት ሲወስዱን የነበረው።

እውነት ለመናገር እኔ በአንድ ወቅት ከሰላም ኮሚሽን ጋር በተያያዘ የትግራይና የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰቦችን ሰብስበን እያነጋገርን ነበር። ጊዜው የሁለት ዓመቱ ጦርነት ከመጀመሩ ከጥቂት ሳምንት በፊት ነበር። በወቅቱ ከሕዝቡ ይሰነዘር የነበረው አስተያየት ስለመሬት ጉዳይ ከመናገራችሁ በፊት አስቀድማችሁ እኛን አግባቡን የሚል ነበር። በወቅቱ ውጥረት ነበርና «አባካችሁ ይህ ነገር አመራሮቻችንን ወዳልተፈለገ ጉዳይ እንዳያስገባቸው እንፈራለን፤ ምክንያቱም መሬትና በመሬት መጠቀም የምንችለው እኛ በሕይወት መኖር ስንችል ነውና እኛ በሌለንበት ስለመሬት ትኩረት መስጠቱ ተገቢ አይደለም» ሲሉን ነበር። ስለዚህ በሕዝቡ ልክ መገንዘብ ያቃተን አካላት ሕዝቡን ወዳልተፈለገ መነሳሳት ለማስገባት ከመታተር ብንታረም መልካም ነው።

በአጠቃላይ በማኅበረሰቡ ውስጥ የጦርነት አባዜ፣ የጦርነት ፍላጎት የለም። በፊትም ቢሆን ማንኛውንም ጥያቄ ተመካክረን ስንፈታ ነበር፤ አሁንም በውይይት መፍታት እንችላለን። ሕዝቡም እያለ ያለው «አባካችሁን ከጦርነት አስወጡን» ነው። ወደጦርነት እያስገቡን ያሉት ፖለቲከኞች ናቸው፤ ከሕዝቡ ዘንድ እንዲህ ዓይነት ነገር የለም። አሁንም ለሰላም መስፈን ቁርጠኝነቱ ከሕዝቡ ዘንድ ስላለ የሚያስፈራ ነገር የለም። ስለዚህም የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት በጦርነት ለተጎዱ አካላት ብሎም በሁለቱም ወገን ላሉ ሰላም ፈላጊዎች እፎይታን እንደሰጠ ይታመናል፤ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ብለው ሲጠባበቁ ለነበረው ለውጭ ጣልቃ ገቦች የሰላም ስምምነቱ ያስተላለፈው መልዕክት ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ አባተ፡-** ጦርነት የማስቀጠል ፍላጎት ያለው አካል አስተሳሰቡ ሰይጣናዊ ነው። ሰይጣናዊ አስተሳሰብን የያዘ ደግሞ ሁሌም ቢሆን ተሸናፊ ነው። ጤናማ የሆነ አመለካከት ያለው አካል በበረታ እና ቀድሞ በተገኘ ቁጥር ጦርነት ናፋቂዎች ያፍራሉ፤ ይዋረዳሉም። እነዚህ ሰላም ጠል አካላት ምናልባት ሰላምን ሊያሳጡን የሚችሉት እኛ በምንከፍተው ቀዳዳ ነውና ይህ እንዳይሆን የእኛ ጽናት መጓደል የለበትም።

ጦርነት ናፋቂዎች ያልተገባ ጥርጣሬ በሕዝቡ ዘንድ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በማስገባት በሕዝብ መካከል አለመተማመን እንዳይኖር ማድረግ ዋና ሥራቸው ነው። ሕዝቡ ብዙ ነገር እንዳጣ በተለያየ እና በሚገባው መንገድ ሊነግሩት ይችላሉ። በተቻላቸው ሁሉ ሊያጋጭ የሚችል ጎዶሎ ነገር በመፈለግና ከተሳካላቸውም ሊያጣላ የሚችል ችግር መዝዘው በማውጣት የእርስ በእርስ ጦርነቱ እንዲቀጥል ይናፍቃሉ። ነገር ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ ምሉዕ የሆነ ነገር የለም። ያንን መረዳቱ ጣልቃ ገቦች የሚገቡበትን ቀዳዳ እንደመድፈን ይቆጠራል። ቀዳዳው ከተዳፈነ በማንም ሕይወት ላይ የመጫወት መብት አይኖራቸውም። ሊያራግቡ የሚችሉበትን ክፍተት ሁሉ መዝጋት ግን ከሁላችንም የሚጠበቅ ጉዳይ ነው።

መማር ያለብን አንድ ነገር አለ፤ በዓለም ላይ ያሉ በርካታ አገሮች ኑሯቸውን የሚኖሩት ያለጦርነት ነው። አሁን የምናያቸው ታላላቅ አገራት ጉዟቸው ልማት ነው፤ አንዴም ሲተኩሱ አይስተዋሉም። አለመግባባት ሳይኖር ቀርቶ ሳይሆን ያጋጠማቸውን ችግር በውይይት ስለሚፈቱ ነው። ዋናው ነገር ጠላት ሊገባና ሊበጠብጠን የሚችለው በእኛ የቁርጠኝነት ማነስ ካልሆነ በስተቀር የትኛውም ነገር በመካከል የሚኖረው የጠበቀ እና በመነጋገር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ከሆነ ጦርነት ናፋቂዎች መቼም ቢሆን ሊሳካላቸው አይችልም። ኢትዮጵያ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጦርነት አቁሜያለሁ ወይ ብላ ራሷን መጠየቅ የሚኖርባት ሲሆን፣ ዜጋውም ስምምነቱ ወደመሬት እንዲወርድ የበኩሉን ሚና መጫወት አለበት። ይህ ከሆነ የጣልቃ ገቦችን መንገድ መዝጋት ብቻ ሳይሆን ዳግም እንዳያስቡት የሚያደርግ ይሆናል። ከዚህ በኋላ ማንንም በጠላትነት አንፈርጅም። አንፈራረጅምም።

**አዲስ ዘመን፡- የሁልጊዜ ተባባሪያችን አቶ አባተ ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ አባተ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## በኮሪያ የዘመተው የአሜሪካዊው ወታደር አጽም ከ72 ዓመታት በኋላ ተገኘ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- በኮሪያ ጦርነት ወቅት ተገድሎ ጠፍቷል የተባለ አንድ የአሜሪካ ወታደር ከ72 ዓመታት በኋላ አጽሙ መለየቱን የአሜሪካ መንግሥት አስታወቀ።

የ27 ዓመቱ ወታደር ቶሚ ቲ ሃንክስ በአውሮፓውያኑ 1950 በሰሜን ኮሪያ አንጁ ከተባለ ስፍራ አቅራቢያ ለመውጣት ሙከራ ሲያደርግ መገደሉ ተነግሯል። ከስድስት ዓመታት በኋላም አስከሬኑ "የማይገኝ" ተብሎ ተወስኖ ነበር።

በጦርነቱ ከተገደሉት መካከል ወደ 7 ሺህ 600 የሚጠጉት እስካሁን የደረሱበት አይታወቅም ሲል የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የመከላከያ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው ሃንክስ በጥቅምት 26 ከአንጁ አቅራቢያ ካለው የቾንግችኦን ወንዝ ምሥራቃዊ ክፍል ለመውጣት ሲሞክር መጥፋቱ ተዘግቧል።

"አስከሬኑ ሊገኝ ካለመቻሉም በላይ የጦር ምርኮኛ ስለመሆኑም ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም" ብሏል በመግለጫው።

በኮሪያ ጦርነት ወቅት የተገደሉትን የአሜሪካ ወታደሮች አጽም የያዙ 55 ሳጥኖችን ሰሜን ኮሪያ ካስረከበች በኋላ ግን የሃንክስን ማንነት ማረጋገጥ ተችሏል።

ይህም ሊሳካ የቻለው በአውሮፓውያኑ 2018 በወቅቱ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ እና በሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን መካከል ከተካሄደ ስብሰባ በኋላ ነው።

የሃንክስን አጽም ለመለየት ሳይንቲስቶች ከአንትሮፖሎጂካል እና ከኢሶቶፕ ትንታኔን በተጨማሪ ሁኔታዊ መረጃዎችን ተጠቅመዋል። አስከሬኑ በአርሊንግተን ብሔራዊ መቃብር እንደሚያርፍም ተነግሯል።

ከ1982 ጀምሮ በኮሪያ ጦርነት የተገደሉ ከ450 በላይ አሜሪካውያን አጽምን በመለየት ለቤተሰቦቻቸው በማስረከብ በሙሉ ወታደራዊ ክብር እንዲቀበሩ ተደርጓል።

ይህ ቁጥር የሰሜን ኮሪያ መንግሥት ከጦርነቱ ማብቂያ በኋላ ባሉት ዓመታት ከ3 ሺህ በላይ አጽም ለአሜሪካ መልሳ አስከሬናቸው ከታወቁት 2 ሺህ አሜሪካውያን በተጨማሪ ነው።

በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች አሁንም የደረሱበት ያልተገኙ በሚል ተመድበዋል። የኮሪያ ጦርነት የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን የተደረገው ነፍስ በላው ግጭት ተደርጎ ይወሰዳል። አሜሪካ ወደ 36 ሺህ የሚጠጉ ወታደሮቿን አጥታበታለች።

## የክሪፕቶከረንሲ ኩባንያ መክሰሩን አወጀ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ግዙፉ የክሪፕቶከረንሲ ልውውጥ ኩባንያ፣ ኤፍቲኤክስ [FTX] መክሰሩን በይፋ አወጀ። ይህን ተከትሎም የኩባንያው መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወጣቱ ቢሊየነር ሳም ባንክማን-ፍራይድ ሥልጣኑን በይፋ ለቋል። የ30 ዓመቱ ሳም በዓለም ላይ ሁለተኛውን ግዙፉን የክሪፕቶከረንሲ ልውውጥ ኩባንያን በበላይነት ሲያስተዳድር ነበር።

ኤፍቲኤክስ በዓለም ላይ ግዙፍ ከሚባሉ የክሪፕቶ ከረንሲ ግብይት ኩባንያዎች አንዱ የነበረ ሲሆን በአንድ ጀንበር እንዳልነበረ ሆኖ ተንኮታኩቷል።

"በጣም ነው የማዝነው፤ እንዲህ እንሆናለን አላልኩም ነበር። የምናገግምበት መንገድ ይኖር ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ" ሲል ጽፏል የክሪፕቶው ንጉሥ ሳም ዓርብ ዕለት በትዊተር ሰሌዳው ላይ። "ነገሩ እኔን ራሱ አስደንግጦኛል" ሲልም አክሏል።

ኤፍቲኤክስ በአንድ ጊዜ እንዲህ ከመንኮታኮቱ በፊት ሳም 'የክሪፕቶ ዋረን በፌት' ተብሎ ይወደስ ነበር። ሃብቱም ወደ 15 ቢሊዮን ዶላር ይገመት ነበር።

ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ሾልከው የወጡ መረጃዎች የክሪፕቶ ግብይት ኩባንያው ኤፍቲኤክስ እና ሌሎች በሳም ተይዘው የነበሩ ኩባንያዎች የፋይናንስ መንገጫገጭ ገጥሟቸው እንደነበረ አሳይተዋል።

ይህ መረጃ ከወጣ በኋላ በርካታ ደንበኞች ክሪፕቶዎቻቸውን ለመመንዘር እሽቅድምድም ውስጥ በመግባታቸው ኩባንያው ኪሳራን በይፋ ለማወጅ ተገዷል። ኤፍቲኤክስ ክሪፕቶን በመሸጥ፣ ዲጂታል ገንዘብን የማለዋወጥ ሥራን የሚሠራ የዲጂታል ግብይት አሳላጭ ኩባንያ ነው።

በትንሽ ቀናት ውስጥ ድንገተኛ የገንዘብ እጥረት የገጠመው ወጣቱ የክሪፕቶ ንጉሥ ሳም፣ በገንዘብ የሚታደገው ፋይናንስ ተቋም ለማግኘት ቢጣጣርም አልሆነለትም። አሁን በርካታ የክሪፕቶ ደንበኞች ዲጂታል ገንዘባቸውን በአንዳች ቁስ ወይም መደበኛ ገንዘብ ለመቀየር ሳይችሉ ቀልጠባቸው ቀርቷል።

አሁን በይፋ ኪሳራን በማወጁ ኩባንያው በፍርድ ቤት ክትትል ስር ሆኖ የተወሰነ ሥራ እንዲቀጥልና ራሱን ከወደቀበት እንዲያነሳ ዕድል ይሰጠዋል። ኤፍቲኤክስ እንዳለው በአሁኑ ወቅት ግብ አድርጎ የተነሳው ሁኔታዎችን በስክነት አጥንቶ ያለውን ሃብት ወደ ገንዘብ ቀይሮ የኩባንያውን ባለድርሻዎች ከውድቀት መታደግ ነው።

ኤፍቲኤክስ ኩባንያ ከ10 እስከ 50 ቢሊዮን ዶላር ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ሃብት እንዳለው ይገመታል። አሁን ቋሚ የኩባንያውን ንብረቶች በመሸጥ ለባለድርሻዎች ገንዘባቸውን በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ ለመመለስ ጥረቱ ተጀምሯል።

ወጣቱ ሳም በአሜሪካ ምርጫ ከፍተኛ የዲሞክራት ፓርቲ ለጋስ በመሆን ስሙ ይወሳል። ይህ ክሪፕቶ ቢዝነስ በሕዝብ ዘንድ እምነት እንዲኖረው ለማስቻልም ከዝነኞቹ ቶም ብሬዲ እና ጊሴል ባንቼን ጋር አብሮ ሠርቷል።

ይሁንና ወጣቱ ሳም ባሉት እህት ኩባንያዎች መካከል፣ በተለይም በኤፍቲኤክስ እና አላሜዳ፣ መካከል የጥቅም ግጭት ሊኖር እንደሚችል ቀድሞም ስጋት የነበራቸው ነበሩ። የኤፍቲኤክስ መንኮታኮት በሌሎችም የክሪፕቶ ከረንሲ ግብይቶች ላይ ጥላውን ጥሏል። ከክሪብቶከረንሲዎች ሁሉ ገናናው ቢትኮይን ለምሳሌ በ20 ከመቶ ዋጋው በዚህ ሳምንት ገበያው አሽቆልቁሎበታል።

አንዳንድ ደንበኞችም የክሪፕቶ ኩባንያዎቻቸው ተመሳሳይ ዕጣ እንዳይደርስባቸው መተማመኛ እንዲሰጡ ከደንበኞቻቸው ጥያቄ እየቀረበባቸው ነው።

የኤፍቲኤክስ የክሪፕቶ ግብይት ኩባንያ ተቀናቃኝ የሆነው ቢናንስ ኩባንያ ሥራ አስፈጻሚ እንደተናገሩት የተቀናቃኞችን መውደቅ የእኛ ድል ተደርጎ መታሰብ የለበትም።

"ደንበኞች እምነት እያጡ ነው። እምነት እያጡ ያሉት ደግሞ በአንድ ኩባንያ ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በዘርፉ ላይ ነው" ብለዋል። የክሪፕቶከረንሲ ኩባንያዎች በባህሪያቸው በቢዝነስ እንዲቀጥሉ በደንበኞች ላይ እምነት እንዲኖር የግድ ይላል።

አሁን በኪሳራ የተንኮታኮተው ኤፍቲኤክስ የክሪፕቶ ግብይት ኩባንያ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ደንበኞች እና 15 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሃብት ነበረው ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

## የቀጠለው የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር

እዮሩስ ተስፋዬ



አቶ ኢብራሂም አሊ ሁሴን የመጡት ከሱማሌ ክልል ነው። አራት የመጀመሪያ ደረጃ የሚማሩ ልጆች አሏቸው። እንደወላጅ የተማሪዎች ምገባ መጀመር ብዙ ነገር እንዳቀለለላቸው ይናገራሉ። ከራሳቸው አልፈው እንደታዘቡት በክልሉ ብዙ አርብቶ አደሮች ያሉበት አካባቢ እንደመሆኑ መጠን ብዙዎች ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ አድርጓቸዋል። ፕሮግራሙ መጀመሩ የተማሪዎች ተሳትፎ እንደጨመረም ይገልጻሉ። በአካባቢው ያሉ ሴት ልጆች የመማር ዕድላቸው ጠባብ፤ ትምህርት የማቋረጥ ዕድላቸው ደግሞ ሠፊ ሲሆን፤ ከዚህ ባስ ሲልም ያለዕድሜ ጋብቻ በስፋት የተንሰራፋበት ነበር። አሁን ግን እነዚህ ችግሮች እጅግ በጣም የተሻሻሉበት ደረጃ ላይ ይገኛል በማለት ያስረዳሉ።

ትምህርታቸውንም እንዳያቋርጡ ብሎም የመውደቅ መጠን መቀነሱን የሚናገሩት አቶ ኢብራሂም፤ እኛ ወላጆችም ልጆቻችን ተጠቃሚ ሆነው ስላየን ምገባው በጣም አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል በማለት ይገልጻሉ። ምገባ በነበረበት እና ባልነበረበት ወቅት ምን እንደሚመስል ሲያነፃፅሩም ልዩነቱ ሰፊ ነው በማለት ነበር የገለጹት። ከዚህ በፊት ልጆቻቸው ቁርስ በልተው ስለማይሄዱ በክፍል ውስጥ የሚሠጠውን ትምህርት ለመከታተል አዳጋች ነበር አሁን ግን ይህ ችግር እንደሌለ ተገንዝበዋል። የመራብ እና የመርሳት ስሜትም አይታይባቸውም። ስለዚህም ምገባው በስፋት ቢቀጥል የሚል ዕምነትም አላቸው።

በአካባቢው የዝናብ እጥረት እንዳለ የሚያነሱት አቶ ኢብራሂም፤ በውሃ እጥረት ምክንያትም የምገባ ፕሮግራም የሚቋረጥበት ወቅት አለ። በመንግሥትም ይሁን መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅት የውሃ ድጋፍ ፕሮግራም ቢካተት የተሻለ እንደሆነ ሃሳባቸውን ለግሰዋል። ስለሆነም ፕሮግራሙ ቀጣይነት ቢኖረው የተሻለ እንደሆነ በመጠቆም፤ ይህ ካልሆነ ግን ከዚህ ቀደም ምገባ ባልነበረበት ወቅት የሚታዩት የተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ያለማድረግ፣ መጠነ ማቋረጥ፣ መጠነ መድገም እና ሌሎች ችግሮች መከሰታቸው የማይቀር እንደሆነ በማንሳት ሁሉም ድጋፍ አድርጎ በተሻለ መንገድ ቢቀጥል ጥሩ እንደሚሆን ይገልጻሉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘም ባለፉት ሁለት አመታት በግሎባል ፓርትነርሺፕ ፎር ኤጁኬሽን ድጋፍ ተግባራዊ ሲሆን የነበረው ሁሉን አቀፍ አገር በቀልና አካታች የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮጀክት በስኬት መጠናቀቁን ባሳለፍነው ሳምንት ተናግረዋል።

በምገባው ከሁለት መቶ ሺ በላይ ተማሪዎችን ተደራሽ የሚያደርግ ሁሉን አቀፍ አገር በቀልና አካታች የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮጀክት ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን፤ ፕሮጀክቱ በፈረንጆቹ ከታኅሣሥ 1 ቀን 2020 እስከ መስከረም 30 ቀን 2022 ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል።

የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፋንታ ማንደፍሮ ፕሮጀክቱ በስኬት እንዲጠናቀቅ አስተዋጽኦ ላበረከቱ በየደረጃው ላሉ አካላት ምስጋናቸውን ያቀረቡ ሲሆን፤ በአንዳንድ አካባቢዎች ተማሪዎች በቂ ምግብ ሳያገኙ ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡበት፤ ከትምህርት ቤት የሚቀሩበት፤ ወደ ትምህርት ቤት የመጡትም በሚገባ ትምህርታቸውን የማይከታተሉበት ሁኔታ እንደነበረም አውስተዋል። ይህንንም ከግንዛቤ በማስገባት ትምህርት ሚኒስቴር አገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ማዕቀፍና የመተግበሪያ ስትራቴጂ ቀርጾ እስከ 2030 ዓ.ም በአገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መርሃ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ እየሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

ይህንንም ከግንዛቤ በማስገባት ትምህርት ሚኒስቴር አገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ማዕቀፍና የመተግበሪያ ስትራቴጂ ቀርጾ እስከ 2030 ዓ.ም በአገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መርሃ-ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ እየሠራ መሆኑንም ይገልጻሉ።

ግሎባል ፓርትነር ሺፕ ፎር ኤጁኬሽን (ጂፒኢ) ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከዓለም አቀፉ ሕፃናት አድን ድርጅት እና ከክልላዊ አጋር ተቋማት ጋር በመሆን ሲተገበር የቆየው ሁሉን አቀፍ አገር በቀልና አካታች የትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብር ፕሮጀክት በስኬት መጠናቀቁ በመግለጽ፤ በስድስት ክልሎች በተመረጡ 578 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ምገባ አገልግሎት እና ሌሎች ተያያዥ ድጋፎችን ለማስቀጠል የሚያስችል ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ አፅድቋል።

የግሎባል ፓርትነርሺፕ ፎር ኢጁኬሽን ተወካይ የሆኑት ዶክተር ሰበረታ ድሃር እንደገለጹት፤ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ተጠቃሚ ካደረጋቸው የትምህርት ቤቶች ብዛት እና የተማሪ ብዛት አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙ ከእቅድ በላይ ነው። በአሁኑ ሰዓትም በግጭት ምክንያት ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ውስጥ በሚገኙ ሕፃናት ላይ ያተኮረ 209 ሺ700 ተማሪዎችን ተደራሽ የሚያደርግ አዲስ የአንድ አመት ፕሮጀክትም ወደ ተግባር መግባቱንም ተናግረዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ኬንያዊቷ የማራቶን ኮከብ በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ እንግዳ ትሆናለች

ብርሃን ፈይሳ

ዘንድሮ ለ22ኛ ጊዜ የሚካሄደው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ብቻ ይቀሩታል። በየዓመቱ ከ10 በላይ ውድድሮችን የሚያካሂደው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ፤ የውድድር ዕድልን ከመፍጠር ባለፈ ታዋቂ አትሌቶችን፣ የውጭ ዜጎችንና ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት እየሳበ ይገኛል። ይህ የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር ከስፖርታዊ ኩነትነቱ ባሻገር የሀገርን መልካም ገጽታ ከመገንባት አንጻር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተም ነው።

በአፍሪካ በትልቅነቱ ቀዳሚ የሆነውና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳጅ ከሆኑ ምርጥ 10 የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድሮች አንዱ የሆነው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የጎዳና ላይ ሩጫ ማህበር አባልም ነው። በ10ሺ ተሳታፊዎች የተጀመረው ይህ ውድድር በአሁኑ ወቅት 40ሺ ተሳታፊዎችን ለማግኘት ችሏል። ይህ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚካሄዱ ትልልቅ የማራቶንና ሌሎች የጎዳና ላይ ውድድሮች ጋር ተፎካካሪ አድርጎታል። ይህም ኢትዮጵያውያን ታዋቂ አትሌቶች እንዲሁም የሌሎች አገራት ዝነኛ ሯጮች በተጋባዥነት በውድድሩ ላይ እንዲካፈሉ አስችሏል። በዚህም ምክንያት ውድድሩ ይበልጥ ትኩረት እያገኘ ከመምጣቱ ባለፈ በስፖርት ቱሪዝምን ከማስፋፋት አንጻር ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ውድድሩ ሲካሄድ የክብር እንግዳ በመሆን ኬንያዊቷ አትሌት ፔሬስ ጄፕቺርቺር አዲስ አበባ እንደምትገኝ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አሳውቋል። የ29 አመቷ ፔሬስ እአአ በ2021 የኒውዮርክ ማራቶንን እና የቶኪዮ ኦሊምፒክ የማራቶን ቻምፒዮን የሆነች አትሌት ናት። በዚህ ዓመት ደግሞ በግሩም ብቃት የቦስተን ማራቶንን አሸንፋለች። ፔሬስ እአአ የ2016 እና የ2020 የሁለት ጊዜ የዓለም ግማሽ ማራቶን አሸናፊም ናት፤ ፈጣን የማራቶን ሰዓቷ የሆነውን 2 ሰዓት ከ17 ደቂቃ ከ16 ሰከንድም ከሁለት ዓመት በፊት ነበር በቫሌንሲያ ማራቶን ያስመዘገበችው።

አትሌቷ ከታዋቂ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ጋርም በመፎካከር የምትታወቅ ሲሆን፤ አብራቸው በውድድር ላይ ከተሳተፈቻቸው አትሌቶች ውስጥ ያለምዘርፍ የኋላው፤ ደጊቱ አዝመራው፤ ነፃነት ጉደታ እና ዘይነባ ይመር ተጠቃሽ ናቸው። ወደ ኢትዮጵያ ስትመጣ የመጀመሪያዋ የሚሆነው ፔሬስ ውድድሩ ከመካሄዱ አንድ ቀን አስቀድማ ከባለቤቷ እና ልጇ ጋር በመምጣት እስከ ውድድሩ ቀን የምትቆይም ይሆናል።

ከፔሬስ ጄፕቺርቺር ባለፈ ከኬንያ በዘንድሮው ውድድር ለመሳተፍ ከኬንያ የሚመጡ አትሌቶች መኖራቸውንም ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ከእነዚህም መካከል ከአትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ ጋር እአአ በ1993 የስቱትጋርት የዓለም ቻምፒዮና ላይ ታሪካዊ የ10ሺ ሜትር ውድድር ያደረገው ኬንያዊው አትሌት ሞሰስ ታኑይም የሚገኝ ይሆናል። ሞሰስ ታኑይ የኤልዶሬት ከተማ ማራቶን ውድድር ዋና አዘጋጅ መሆኑ ይታወቃል። በተጨማሪም ከተለያዩ የኬንያ መገናኛ ብዙሃን የሚመጡ ጋዜጠኞችም እንደሚኖሩ ይጠበቃል።



ኬንያዊቷ የኦሊምፒክ ሻምፒዮን ከነ ቤተሰቧ በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ላይ ትገኛለች፤

በአካል በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ተገኝተው ከሚሮጡት ባለፈም ባሉበት አገር ሆነው በኢንተርኔት አማካይነት በሩጫው ላይ የሚሳተፉ የውጭ አገር ሯጮች መኖራቸውም አገርን በበጎ ከማስተዋወቅ ረገድ የሚኖረው ድርሻ ቀላል የሚባል አይደለም። ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ለአትሌቶች የውድድር መድረክን የሚፈጥር ከመሆኑ ባለፈ በርካታ አትሌቶች ከዚህ ውድድር በመነሳት በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ሊሆኑ ችለዋል። ታዋቂና በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ የሆኑ እንደ እነ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ገብረእግዚአብሔር ገብረማርያም፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣... የመሳሰሉ አትሌቶችም ከዚህ ቀደም በውድድሩ ተካፍለዋል።

ከጊዜ ወደጊዜ በዚህ ውድድር ላይ በርካታ አትሌቶች ተካፋይ እየሆኑ ሲሆን፤ ቁጥሩን ከመቀነስና ጥራቱን ከመጠበቅ አንጻር አስቀድሞ የማጣሪያ ውድድር ተካሂዷል። ለተሳታፊዎችም በተለያዩ ጊዜያት የልምምድና የስልጠና መርሃ ግብሮች ተካሂደዋል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር በስኬት የተጠናቀቀው ሦስተኛው የሳይበር ደህንነት ወር

ደበል ካሳ

“የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ለአገር ሉዓላዊነት” በሚል መሪ ሃሳብ ከጥቅምት 1 እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ሦስተኛው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር ተከብሯል። በመሪ ሃሳቡ ላይ እንደተቀመጠው የዘንድሮው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር በተለየ ሁኔታ ለሀገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሰጠም ነበር። ዓቢይ አጀንዳ ሆኖ የተመረጠውን የሀገር ሉዓላዊነትን የማስጠበቅ ጉዳይ ማሳካት ይቻል ዘንድም አራት ዋና ዋና የትኩረት መስኮችንም በግብ ማስፈጸሚያነት አስቀምጦ በአራት ሳምንታት ተከፋፍለው በሚቀርቡ ልዩ ልዩ መርሐ ግብሮች የትግበራ ጊዜውን ጠብቆ እየተካሄደ ይገኛል። የትኩረት መስኮቹም አገራዊ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊናን ማሻሻል፣ የተቋማት የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትን መቀነስ፣ በሳይበር ደህንነት ዘርፍ የሰው ሃብት ልማትን ማሻሻልና የግሉን ዘርፍ ለሳይበር ደህንነት መጠበቅ የሚኖረውን ሚና ማሳደግ የሚሉ ናቸው።

በዚህ አግባብ ወሩን ሙሉ እየተከበረ በሚገኘው የዘንድሮው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር በየሳምንቱ በተጠቀሱት የትኩረት መስኮች ላይ ኮንፍረንሶችና ዓውደ ርዕዮች በማዘጋጀትና የተለያዩ ጭብጦችን ማስተላለፍ በሚያስችሉ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫና የንቃተ ሕሊና መፍጠሪያ መንገዶችን በመጠቀም መርሐ ግብሮቹ ተተግብረዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በወሩ ውስጥ ሦስት ትልልቅ ኮንፍረንሶችን ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት ሁሉም የተካሄዱ ሲሆን የሦስተኛው ሳምንት ባለተራ የሰው ሃብት ልማትን የሚመለከተው የትኩረት መስክ ነበር።

በዚህም “የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችል የሰው ኃይል እንዴት ማልማት ይቻላል” በሚል ርዕስ ላይ የተዘጋጀ ኮንፍረንስ በስካይ ላይት ሆቴል ተካሂዷል። ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ የግል ተቋማት፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ዓለም አቀፍ ተቋማት የኮንፍረንሱ ተሳታፊ በሆኑበት በዚህ ኮንፍረንስ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናትና ከግሉ ዘርፍ የመጡ አካላት መልዕክት አስተላልፈውበታል። በርዕስ ጉዳዩ ላይ ያተኮረ ጥናታዊ ጽሑፍ በባለሙያ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

ከእነዚህ ዓብይ አጀንዳ ማስፈጸሚያ መርሐ ግብሮች መካከል ሌላኛው ደግሞ በአራተኛው ሳምንት ላይ የተካሄደው የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ የሕግ አውጭ አካላት ሚና ምን መሆን አለበት በሚለው ላይ የተካሄደው መርሐ ግብር ነው። በዚህም እንደ ሀገር የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ ማዘጋጀት የሳይበር ጥቃትንና ወንጀልን ለመከላከልና የሀገርን ብሔራዊ ደህንነትና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር መሆኑ መግባባት ላይ ተደርሶበታል። ኢትዮጵያም ለሳይበር ጥቃት ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችልና ዘመኑን የሚመጥን የተሻሻለ የሳይበር ደህንነት ረቂቅ ፖሊሲ ባለፈው ዓመት ማዘጋጀቷ ተጠቅሷል።

በፖሊሲው ውስጥም ተቋማት ተቋማዊ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በራሳቸው መንገድ የሳይበር ጥቃትን እንዲከላከሉ የሚያስችል አሠራር መካተቱን ይታወሳል። ህጎችን ማውጣት ብቻ ሳይሆን የሚወጡ ሕጎችን በአግባቡ መተግበርም ግድ ይላል።

በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር ያረጋገጡትም ይህንኑ ነው። አፈ ጉባኤው በመልዕክታቸው የሀገርን ብሔራዊ ደህንነትና ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ የሚወጡ ሕጎች ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ የህግ አውጭ አካላት፤ የሕዝብ ተወካዮችና ፌዴሬሽን ምክር ቤቶች በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ ተናግረዋል። ለዚህም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከታተሏቸውና የሚቆጣጠሯቸው ተቋማት የሳይበር ደህንነት ጉዳይን ዋነኛ የትኩረት መስካቸውና ስትራቴጂክ ተቋማዊ ጉዳያቸው አድርገው መምራት የሚገባቸው መሆኑንም አመላክተዋል። ለተፈጻሚነቱም የሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ አካላት ከሕግ አውጭው ጋር በጋራ ተቀናጅተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

በመጨረሻም ሦስተኛው ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር በስኬት መጠናቀቁ ተገልጿል። ወሩ በስኬት መጠናቀቁን አስመልክቶም የእውቅናና የምስጋና መርሐ ግብር ተካሂዷል። በእውቅናና የምስጋና መርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ እንደገለጹት፤ ለመርሐ ግብሩ መሳካት ቁልፉ ጉዳይ በመደመር እሳቤ ከተለያዩ ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት ተችሏል።

በዚህም የሳይበር ደህንነት ጉዳይን የጋራ ኃላፊነት እንደሆነ በመገንዘብ በሦስተኛው የሳይበር ደህንነት ወር ላይ በስትራቴጂክ አጋርነት፣ በአጋርነት እንዲሁም በተለያየ መልኩ አስተዋጽዖ ላደረጉ ተቋማት እና ግለሰቦች በአስተዳደሩ ሥም ላቅ ያለ ምስጋናቸውን አቶ ሰለሞን አቅርበዋል።

በሦስተኛው የሳይበር ደህንነት ወር ከተካሄዱ አጠቃላይ መርሐ ግብሮች ውስጥ ኢመደአ 30 በመቶውን ድርሻ ብቻ እንደወሰደ የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ቀሪውን 70 በመቶ ድርሻ በዘርፉ የተሠማሩ የግልና የመንግሥት ተቋማት በተለያየ መልኩ፤ ዓውደ ርዕይ በማቅረብ፣ የፓናል ውይይቶች ላይ በመሳተፍ እንዲሁም መርሐ ግብሩን በፋይናንስ በመደገፍ ከፍተኛውን ድርሻ እንደወሰዱ አብራርተዋል።

ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ጉዳይ የሁሉም ተቋማትና ባለድርሻ አካላት የጋራ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን በሦስተኛው የሳይበር ደህንነት ወር ላይ የታየው የቅንጅትና የትብብር ሥራ በቀጣይም ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው ዋና ዳይሬክተሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ አቢሲኒያ ባንክ እና የኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ ሲሆኑ አዋሽ ባንክ፣ ዳሸን ባንክ፣ ዳን ኢነርጂስ፣ ቼክ ፖይንት፣ ዴሊቨር አይሲቲ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ብርሃን ባንክ፣ አይፒ ኮም ቴክኖሎጂስ ትሬዲንግ፣ አትላስ ኮምፒዩተር ቴክኖሎጂና ሁዋዊ ኢትዮጵያ ሦስተኛውን የሳይበር ደህንነት ወር በስትራቴጂክ አጋርነት ደግፈዋል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ